# ኅብረተሰብ ሳይንስ

## 5ኛ ክፍል

## የተማሪ መጽሐፍ


**አዘጋጅ:-**

ብርሃኑ ለሜሶ

**አርታኢ:-**

ወንድማገኝ ገብረሕይወት

**ገምጋሚዎች:-**

ዘሳለም አሳጋው

ዘሪሁን ጌታቸው

ደታገሱ አጥናፉ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

## ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው:: የኘሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትቭ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው::

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የተማሪ መጽሀፍና የመምህር መምሪያ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፍቸውን ሰጥተዋል:: በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::

© በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

1ኛ እትም፣ 2003 ዓ.ም

ISBN 978-99944-2-082-7

**የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 5613**
**ዱባይ፣**
**የተባበሩት የአረብ ኤሜሬት**

**ከኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 100767**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል::

ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል::

የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዲራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል::

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል:: ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን::

# ማውጫ

ገፅ

## ምዕራፍ አንድ፡- የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት መገኛና የሕዝቦች አሠፋፈር


1.1 የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትና መገኛቸው ........................................................ 1

1.2 የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ሕዝቦች ታሪክና አሰፋፈር ................................ 5

1.3 የኢትዮጵያ አንድነትና ዘመናዊነት ........................................................ 17

1.4 የሕዝብ አሰፋፈርና የባህል ልዩነት እንዲፈጠር ጉልህ ሚና ያላቸው ምክንያቶች ........................................................23

የቁልፍ ቃላት ፍቺ ........................................................ 28

ማጠቃለያ ........................................................29

የክለሳ ጥያቄዎች ........................................................ 30

ፍተሻ ........................................................32


## ምዕራፍ ሁለት፡- መሬትና እና አካባቢዋ


2.1 መገኛችን........................................................33

2.2 የመሬት ቅርጽ፣ እንቅስቃሴዋና ውጤቶቹ ........................................................36

2.3 የወቅቶች መፈራረቅ በእርሻና በከብት እርባታ ላይ ያለው ተፅዕኖ...............................42

የቁልፍ ቃላት ፍቺ ........................................................ 46

ማጠቃለያ ........................................................47

የክለሳ ጥያቄዎች ........................................................ 48

ፍተሻ........................................................ 50

## ምዕራፍ ሦስት፡- አካባቢያችን

3.1 ዋና ዋና የእፅዋት ዓይነቶችና የዱር እንስሳት .......... 51
3.2 የዱር እንስሳትና እፅዋት የሚሰጡት ጥቅም .......... 62
3.3 ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በእፅዋትና በዱር እንስሳት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተፅዕኖ .......... 65
3.4 የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ .......... 67

የቁልፍ ቃላት ፍቺ .......... 71
ማጠቃለያ .......... 72
የክለሳ ጥያቄዎች .......... 73
ፍተሻ .......... 75

## ምዕራፍ አራት፡- ሕዝባዊ ጉዳዮች

4.1 ሕዝብ ነክ ጉዳዮች .......... 76
4.2 ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና አሉታዊ ተፅዕኖዎቹ .......... 81
4.3 መልካም አስተዳደር፣ የሕፃናት መብትና ደኅንነት .......... 83

የቁልፍ ቃላት ፍቺ .......... 91
ማጠቃለያ .......... 92
የክለሳ ጥያቄዎች .......... 93
ፍተሻ .......... 95

**ምዕራፍ አንድ**

# የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት መገኛና የሕዝቦች አሠፋፈር

*ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ውጤቶች*

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦**

- *የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን ስምና አንፃራዊ መገኛቸውን ትገልፃላችሁ፡፡*
- *በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የነበሩ ጥንታዊ መንግሥታትን ትጠቅሳላችሁ፡፡*
- *በኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወኑ ታሪካዊና ፓለቲካዊ ክንዋኔዎችን (ስኬቶችን) ትጠቅሳላችሁ፡፡*
- *የዘመናዊነት ዋና ዋና ክንዋኔዎች ባድንቆት ትገልፃላችሁ፡፡*
- *በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥረው የነበሩ ጥንታዊ መንግሥታትና ዋና ዋና ስኬታማ ክንዋኔዎቻቸውን ታብራራላችሁ፡፡*
- *በከፍተኛና ዝቅተኛ ሥፍራዎች በሚኖሩ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የአሰፋፈር የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ልዩነት መንስኤዎችን ትለያላችሁ፡፡*

## 1.1 የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትና መገኛቸው

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የአፍሪካ ቀንድ መገኛን ትገልጻላችሁ፡፡
- ሰሳጨ መገኛን (ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ) በመጠቀም የአፍሪካ ቀንድ መገኛን ትገልፃላችሁ፡፡
- በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ሀገራት ስምን ትጠቅሳላችሁ፡፡
- የአፍሪካን ካርታ በመጠቀም የኢትዮጵያን አንፃራዊ መገኛ ታሣያላችሁ፡፡
- ሰሳጨ (cardinal) መገኛን (ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ) አቅጣጫዎችን በመጠቀም የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዋና ዋና ከተሞችን ትገልፃላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- አንፃራዊ መገኛ
- የአፍሪካ ቀንድ

አራተኛ ክፍል በነበራችሁ ጊዜ ስለኢትዮጵያ ሕዝቦች ተምራችኋል፡፡ አሁን በአምስተኛ ክፍል ደግሞ ስለ ኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ መገኛ፣ ስለ ሕዝቦችና አሠፋፈራቸው ትማራላችሁ፡፡

## ◈ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት አንፃራዊ መገኛ

- *አንፃራዊ መገኛ ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ?*

አንፃራዊ መገኛ ማለት የአንድን ሥፍራ ወይም ነገር መገኛ በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች ነገሮች ለምሳሌ ተራሮችና ወንዞች ከመሳሰሉት ጋር በማነጻፀር የሚያመለክት ነው፡፡ በከተሞች አካባቢ ትላልቅ ሕንፃዎችን፣ መንገዶችን፣ ድልድዮችን በማነጻፀሪያነት መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ አንፃራዊ መገኛን በመጠቀም የአንድን ሥፍራ ወይም ሰፈር መገኛ መግለጽ በጣም ቀላል ይሆናል፡፡

**አንፃራዊ መገኛ የአገርን፣ የክልልን ወይም የአህጉርን መገኛ ከየብስ፣ ከውኃ አካላት ወይም ከአጎራባች አገሮች ጋር በማነጻፀር ይገለፃል፡፡ አንፃራዊ መገኛ ከዐበይት አቅጣጫዎች አንፃርም ሊገለጽ ይችላል፡፡ ዐበይት አቅጣጫዎች ሰሜን፣ ምሥራቅ፣ ደቡብና ምዕራብ ይባላሉ፡፡ የዐበይት አቅጣጫዎች ንዑሳን ክፍሎችንም በመጠቀም አንፃራዊ መገኛን መግለጽ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ደቡብ ምሥራቅ ወይም ሰሜን ምዕራብ በማለት መግለጽ ይቻላል፡፡ አንፃራዊ መገኛን ለመለየት የማነጻፀሪያ ነጥቦች እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡**

ተማሪዎች የምትኖሩበትን የአፍሪካ ክፍል አንፃራዊ መገኛ ታውቃላችሁን? ትክክለኛውን መገኛ ግለጹ፡፡ ተማሪዎች የምትኖሩበት የአፍሪካ ክፍል አንፃራዊ መገኛ ስያሜ የአፍሪካ ቀንድ ይባላል፡፡ ለምን ይመስላችኋል?

ይህ አካባቢ የአፍሪካ ቀንድ የሚለውን ስያሜ ያገኘው በተፈጥሮ ካለው ቅርጽ አኳያ ነው፡፡ በምስል 1.1 እንደምትመለከቱት የአካባቢው ቅርጽ ልክ ቀንድ ይመስላል፡፡ በዚህም የአፍሪካ ቀንድ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡



*ምስል 1.1 ወደ ሕንድ ውቅያኖስ የገባውን የአፍሪካ ቀንድ ክፍል የሚያሳይ የሳተላይት ፎቶግራፍ*


**የአፍሪካ ቀንድ በአፍሪካ አህጉር በየትኛው አካባቢ ይገኛል?**

የአፍሪካ ቀንድ የሚገኘው በምሥራቃዊ አፍሪካ ነው:: ይህ ክፍል የአህጉሩ ምሥራቃዊ ጫፍ አካል ነው:: የአፍሪካ ቀንድ የሾለ ቅርጽ ይዞ ወደ አረብ ባሕር ይገባል (ምስል1.1 ተመልከቱ):: በሰሜን ምሥራቅ ከቀይ ባሕርና ከኤደን ባሕረ ሰላጤ ጋር ይዋሰናል:: ከዚሁ ሥፍራ በስተደቡብ ምሥራቅ ደግሞ የሕንድ ውቅያኖስ ይገኛል::

የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ኩታ ገጠም ናቸው:: ሶማሊያ የምትገኝበት ሥፍራ ወደ ሕንድ ውቅያኖስ የገባ ነው:: ይህ የሶማሊያ ክፍል የኤደን ባሕረ ሰላጤንና ቀይ ባሕርን ከሕንድ ውቅያኖስ ይለያል:: የዚህም ሥፍራ ቅርጽ ቀንድ ይመስላል:: ስለዚህ የአፍሪካ ቀንድ የሚለው ስያሜ የተገኘው ከዚህ ቅርጹ ነው ማለት ይቻላል::

## ◈ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት

- የሚከተለውን ካርታ በጥሞና በመመልከት የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን መዘርዘር ትችላላችሁን?




*ምስል 1.2 የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትና መዲናዎቻቸው*

የአፍሪካ ቀንድ አራት ሀገራትን ያካትታል። የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት የሚባሉት ኢትዮጵያ፣ ሶማሊያ፣ ጅቡቲና ኤርትራ ናቸው።

*ሰንጠረዥ 1.1 የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ስፋት፣ ዋና ከተሞቻቸውና ዋና ከተሞቻቸው ከአዲስ አበባ ያላቸው ርቀት*

| የአፍሪካ ቀንድ ሀገሬት | ስፋት በካሬ ኪ.ሜ | ዋና ከተማ | ዋና ከተሞች ከአዲስ አበባ ያላቸው ርቀት በኪ.ሜ |
|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያ | 1,106,000 | አዲስ አበባ | - |
| ሶማሊያ | 637,657 | ሞቃድሾ | 1070 |
| ኤርትራ | 117,400 | አሥመራ | 1080 |
| ጅቡቲ | 23,200 | ጅቡቲ | 782 |

- **የአፍሪካን ቀንድ የሚያዋስኑ ሀገራት እነማን ናቸው?**

ከአፍሪካ ቀንድ ጋር የሚዋሰኑ ሁለት ሀገራት አሉ። እነዚህም ኬንያና ሱዳን ናቸው። ሱዳን የአፍሪካን ቀንድ በስተምዕራብ የሚያዋስን ሲሆን፣ኬንያ ደግሞ ከአፍሪካ ቀንድ በስተደቡብ ይገኛል።

## የክለሳ ጥያቄዎች1.1

**ክንውን**

***ሀ. በዕውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- አንፃራዊ መገኛ ምን ማለት ነው?
- አንፃራዊ መገኛን ማወቅ ለምን ይጠቅማል?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- የአፍሪካን ንድፍ ካርታ ሳሉ።
- በካርታችሁ ላይ የአፍሪካን ቀንድ አመልክቱ።
  ቀይ ባሕርን፣ የአረብ ባሕርን፣ የኤደን ባሕረ ሰላጤንና የሕንድ ውቅያኖስንም አካቱ።

የአፍሪካን ቀንድ ሀገራት በስፋታቸው ቅደም ተከተል በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ላይ አስፍሩ።

1ኛ ____________________

2ኛ ____________________

3ኛ ____________________

4ኛ ____________________

- የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በትክክለኛ መረጃዎች ሙሉ።

| የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት | ዋና ከተሞቻቸው |
|---|---|
| | አሥመራ |
| ጅቡቲ | |
| | አዲስ አበባ |
| ሶማሊያ | |

## 1.2 የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ሕዝቦች ታሪክና አሰፋፈር

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙትን ዋና ዋና የቅሪተ አካላትና ቅሪተ ቁስ መገኛዎችን ትለያላችሁ::
- የቅሪተ አካላት ግኝቶችን የጊዜ ቅደም ተከተልና ጥቅማቸውን ለይታችሁ ትናገራላችሁ::
- በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋና ሀይማኖቶችን አመጣጥና ሽፋንን ትገልፃላችሁ::
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ያለው የሃይማኖት መቻቻል የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው መሆኑን በመገንዘብ አድናቆታችሁን ትገልፃላችሁ::
- ኢትዮጵያ የብዙ እምነት ተከታይ ሀገር መሆኗን በመገንዘብ ትገልፃላችሁ::
- ስጥንታዊ የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ መንግሥታት ያላችሁን አድናቆት ትገልፃላችሁ::
- ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥታት ታሪካዊና ፓለቲካዊ ክንዋኔዎች ትለያላችሁ::

**ቁልፍ ቃላት**


- ሥልጣኔ
- ቅሪተ አካል
- ቅሪተ ቁስ

### ◈ የሰው ልጅ ዘር፣የቅሪተ አካልና ቅሪተ ቁስ መገኛዎች በኢትዮጵያና በኬንያ

### 1. የሰው ልጅ ዘር መገኛ

- ተማሪዎች የሰው ልጅ ዘር መገኛ የት እንደሆነ ግለጹ::

አህጉራችን አፍሪካ በተለይም በአፍሪካ ቀንድ ኢትዮጵያና ኬንያ የሰው ልጅ ዘር መገኛ መሆናቸውን የተለያዩ የቅሪተ አካላት ግኝቶች ይጠቁማሉ:: ይህ ጥቆማ በተለያዩ ግኝቶች የተደገፈ ነው:: የቅሪተ አካላትና የቅሪተ ቁስ ተመራማሪዎች (Archeologists) ይህንን በተገቢ ሁኔታ ያስረዳሉ:: ተማሪዎች የምታውቁት የቅሪተ አካላትን ስም ለመዘርዘር ሞክሩ:: የተለያዩ ተመራማሪዎች የተለያዩ ቅሪተ አካላትን አግኝተዋል:: ለምሳሌ የኢትዮጵያዊው የቅሪተ አካላትና ቅሪተ ቁስ ተመራማሪ ግኝት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እስኪ ቀጥሎ ያለውን ውስን ጥናት አንብቡ::



ምስል 1.3 ጥንታዊ ሰዎች

ምስል 1.3 በጥሞና ከተመለከታችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ::

- በምስል 1.3 ላይ የሚታየው ጥንታዊ ሰው በእጁ የያዘው ምንድን ነው?
- ለምን ተግባር ይጠቀምበት ነበር?

## ውስን ጥናት

ዶክተር ዮሐንስ ዘረሰናይ ኢትዮጵያዊ የቅሪተ አካላትና ቅሪተ ቁስ ተመራማሪ (archeologist) ናቸው። ዲኪካ ከሚባል ሥፍራ የጥንታዊ ሴት ቅሪተ አካል ቆፍረው ያወጡ ጠቢብ ናቸው። የቅሪተ አካሏ ስምም ሰላም የሚል መጠሪያ ተሰጥቷታል። የሰላም ቅሪተ አካል የተገኘው በ1998 (እ.ኤ.አ በ2006 ዓ.ም) ነበር። ሰላም ከ3,300,000 ዓመታት በፊት የኖረች ሕጻን ሴት ልጅ ነበረች። በሕጻንነት ዕድሜ የሞተች ቢሆንም ሰላም ድንቅነሽ ከመፈጠሯ ከ120,000 ዓመታት በፊት የኖረች ናት። (ሰንጠረዥ 1.2 ተመልከቱ)።



ምስል 1.4 ዶ/ር ዮሐንስ ዘረሰናይ

### 2. የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች

- የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎችን ታውቃላችሁ?
- በቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች ምን ዓይነት ተግባራት ይከናወናሉ?

የጥንታዊ ሰው ቅሪተ አካላት ተቆፍረው የሚገኙባቸው ቦታዎች የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች በመባል ይታወቃሉ። አርዲ፣ ኢዳልቱ፣ ድንቅነሽ(Lucy) እና ሰላም የጥንታዊ ሰዎች ቅሪተ አካላት ናቸው። እነዚህ ማስረጃዎች ከተለያዩ የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች በቁፋሮ የተገኙ ናቸው።



ምስል 1.5 ተመራማሪዎች በቅሪተ አካል ፍለጋ ላይ

### ሀ. የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች በኢትዮጵያ

- ድንቅነሽ እና ሰላም የት አካባቢ እንደተገኙ ታውቃላችሁ?

በኢትዮጵያ አያሌ የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች አሉ፡፡ እነዚህ ቦታዎች የሚገኙት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ነው፡፡ እጅግ ታዋቂ የሆኑ የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች የሚገኙት በሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተለይም በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፡፡ አርዲ፣ ኢዳልቱ፣ ድንቅነሽ (Lucy) ሰላም በመባል የሚታወቁት ቅሪተ አካላት በቁፋሮ የተገኙት ከአፋር ክልል ነው፡፡ የቅሪተ አካላት ዕድሜና የተገኙበት ዘመን የተለያየ ነው፡፡ ቅሪተ አካላቱ የተገኙባቸው ሥፍራዎችና ዕድሜያቸው ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ የተካተቱ ስለሆነ መረጃዎቹን በጥሞና ተመልከቱ፡፡

*ሰንጠረዥ 1.2 ከአፋር የተለያዩ ስፍራዎች በቁፋሮ የተገኙ ቅሪተ አካላትና እድሜያቸው፡፡*

| የቅሪተ አካል ስም | የቅሪተ አካል መገኛ ሥፍራ | ዕድሜ | የተገኘበት ዘመን |
|---|---|---|---|
| አርዲ | አራሚስ | 4,400,000 | 1986 (እ.አ.አ 1994) ዓ.ም |
| ኢዳልቱ | ሄርቶ | 160,000 | 1995 (እ.አ.አ 2003) ዓ.ም |
| ድንቅነሽ (Lucy) | ሐዳር | 3,180,000 | 1966 (እ.አ.አ 1974) ዓ.ም |
| ሰላም | ዲኪካ | 3,300,000 | 1998 (እ.አ.አ 2006) ዓ.ም |

በሰንጠረዥ 1.2 የተመለከቱ ቅሪተ አካላት የተገኙት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ ቢሆንም፣ በሌሎችም የሀገራችን ክልሎች የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን መልካ ቁንጡሬ በመባል የሚታወቅ የቅሪተ አካል መገኛ ሥፍራ አለ፡፡ ይህ ሥፍራ ከአዲስ አበባ ወደ ቡታጅራ በሚወስደው መንገድ 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥትም ሌሎች የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች አሉ፡፡ ኬንያ ድንበር አካባቢ ሌሎች የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡

### ለ. የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች በኬንያ

በኬንያ የተለያዩ አካባቢዎች የጥንታዊ ሰው ቅሪተ አካልና ቅሪተ ቁስ መገኛ ሥፍራዎች አሉ፡፡ ነገር ግን በርካታ ቅሪተ አካልና ቅሪተ ቁስ የተገኘበት ታዋቂ ሥፍራ ከቱርካና (ሩዶልፍ) ሐይቅ ዳርቻ ይገኛል፡፡ ኮቢ ፎራ ይባላል፡፡ ቱርካና በሐይቁ ዳርቻ የሠፈረ ማኅበረሰብ መጠሪያ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ ከ1930ዎቹ ጀምሮ አራት የአንድ ቤተሰብ ምሁራን በምርምር ላይ ተሰማርተው በርካታ ቅሪተ አካልና ቅሪተ ቁስ አሰባስበዋል፡፡ እነርሱም ሉዊ ሊኪና ባለቤቱ ሜሪ ሊኪ፣ እንደዚሁም ልጃቸው ሪቻርድ ሊኪና ባለቤቱ ሚቭ ሊኪ ናቸው፡፡ በኮቢ ፎራ ከተገኙ በርካታ የጥንታዊ ሰው ቅሪተ አካልና ዕድሜ ጠገብ የድንጋይ መሣሪያዎች መካከል በ1987 (እ.አ.አ 1995) ዓ.ም በሚቭ ሊኪ የተገኘው ቅሪተ አካል ተጠቃሽ ነው፡፡ በኮቢ ፎራ የተገኘው የጥንታዊ ሰው ቅሪተ አካል ዕድሜ ከ3.2 — 3.5 ሚሊዮን የሚገመት ሲሆን አውስትራሎፒተከስ አናመንስስ የሚል ሳይንሳዊ መጠሪያ ተሰጥቶታል፡፡ አናመንስስ "አናም" ከሚለው ስያሜ ከቱርካና ቋንቋ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ሐይቅ ማለት ነው፡፡

ከላይ ከተመለከቱት መረጃዎች ኢትዮጵያና ኬንያ በአፍሪካ ቀንድ ቀዳሚ የቅሪተ አካላት መገኛ ሀገራት መሆናቸውን ያሳያሉ፡፡ ይህም ኢትዮጵያን ከአፍሪካ ቀንድ ልዩ ያደርጋታል፡፡ ኢትዮጵያ የጥንታዊ ሰዎች ቀደምት መኖሪያ አካባቢ እንደነበረች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች የሚገኙ ሕዝቦች

ቀደምት መነሻ ኢትዮጵያ እንደነበረ ታውቋል:: በአካባቢያችሁ የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች ካሉ በአካል ተገኝታችሁ ለመጎብኘትና ለእነዚህ ታሪካዊ ቅርሶች ጥበቃና ልማት የበኩላችሁን ጥረት አድርጉ::

## ◈ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች አመጣጥ በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት

### 1. ክርስትና

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ሃይማኖቶች የትኞቹ ናቸው?
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ሃይማኖቶች እንዴት እንደመጡ አስረዱ::

የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ330 ዓመተ ምሕረት አካባቢ ነበር:: ይህን ሃይማኖት በማስተማር ያስፋፉት አባ ፍሬምናጦስ በመባል ይታወቃሉ:: በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው ቤተ ክርስቲያን አክሱም ጽዮን ማርያም ይባላል:: ክርስትናን በኢትዮጵያ የተቀበለ የመጀመሪያው የአክሱም ንጉሥ ኢዛና ነበር:: አባ ፍሬምናጦስ ደግሞ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ነበሩ:: ፍሬምናጦስ የጵጵስና ማዕረግ ሲቀበሉ ስማቸው ተቀይሮ አቡነ ሰላማ ተብሏል:: ከዚህ በኋላ የክርስትና ሃይማኖት ወደ ሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ቀስ በቀስ ሊስፋፋ ችሏል::

- የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ክርስቲያኖች በመባል ይታወቃሉ::
- የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ደግሞ ሙስሊሞች ይባላሉ::

### 2. እስልምና

- የእስልምና ሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አፍሪካ ቀንድ ሀገራት እንዴት መጣ?

የእስልምና ሃይማኖት የተመሠረተው በደቡብ አረቢያ ነበር:: የሃይማኖቱም መሥራች ነቢዩ መሐመድ ነበሩ:: ይሁን እንጂ በወቅቱ የነበሩት የመካ መሪዎች ሃይማኖቱን ስላልተቀበሉት የመጀመሪያዎቹን የሃይማኖቱን ተከታዮች ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ አሰቃይተዋቸዋል:: ይህን በውል የተገነዘቡት ነቢዩ መሐመድ ጥቂት ተከታዮቻቸውን ከጥቃቱ ለማዳን ወደ ኢትዮጵያ ልከዋቸዋል:: ኢትዮጵያ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ወደ መካ እስከተመለሱበት ጊዜ ድረስ ከኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ተከታዮች ጋር በደስታና በተድላ ኖረዋል:: የእስልምና ሃይማኖትም በኢትዮጵያ የተስፋፋው ከሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ነው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖቶች ተከታዮች በኢትዮጵያ በሰላም መኖራቸው ይታወቃል:: በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች አብረው በሰላም የሚኖሩባት ሀገር ናት::

ስለዚህ በሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል ተከባብሮና ተፈቃቅሮ የመኖር ባህል መሠረት የጣለው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው:: አሁን ባለንበት ዘመንም የሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታዮች ይከባበራሉ፤ በፍቅር አብረው ይኖራሉ፣ በበዓላት ይገባበዛሉ፣ የእንኳን አደረሳችሁ የምኞት መግለጫ መልዕክቶች ይለዋወጣሉ:: በችግርና በደስታ ወቅት ይረዳዳሉ:: በአገራቸው የሚነሣ ጠላትን በአንድነት ይመክታሉ:: ለሀገራቸው ዕድገትና ብልጽግና የጋራ ራዕይ ሰንቀው በአንድነት ይሠራሉ:: ይህም ኢትዮጵያ የብዙ ሃይማኖት ተከታዮች በአንድነት የሚኖሩባት ሀገር መሆኗን ያሳያል:: ይህ የአኗኗር ሥርዓት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሠናይ ባህል መገለጫ በመሆኑ ማክበርና አጠናክሮ መቀጠል በጣም አስፈላጊ ነው::

## የክለሳ ጥያቄዎች 1.2

**ክንውን ሀ**


***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- በኢትዮጵያ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች መካከል ሰፍኖ የቆየው የወንድማማችነትና በሰላም አብሮ የመኖር ግንኙነት ያስገኘው ጠቀሜታ ምንድን ነው?
- የሃይማኖቶች መቻቻል ለምን ያስፈልጋል?
- በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል እንዲጎለብት የእናንተ አስተዋጽዖ ምን መሆን አለበት?
- ኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ልዩነታቸው ኢትዮጵያዊ አንድነታቸውን ሳያጠፋባቸው፣ ኢትዮጵያዊ አንድነታቸው ሃይማኖታዊ ልዩነታቸውን ሳያጠፋባቸው ልዩነትን በአንድነት፣ አንድነትን በልዩነት እንዴት አቻችለው እንደኖሩ ተወያዩበት፡፡
- የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች ሲባል ምን ማለት ነው?
- ቅሪተ አካላት ምንድን ናቸው?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- በአፍሪካ ቀንድ ኢትዮጵያን ልዩ የሚያደርጓትን ነገሮች ዘርዝራችሁ በመጻፍ በክፍላችሁ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለጥፉ::
- የሌሎች ቡድኖችን ሥራዎች በማጥናት በክፍል ውስጥ በሚደረገው ውይይት ላይ በንቃት ተሳተፉ::
- በሠንጠረዥ 1.2 የቀረቡትን ቅሪተ አካላት በዕድሜ ቅደም ተከተል ከትልቅ ወደ ትንሽ አስቀምጡ፡
- ከዕድሜ አንጻር ለዘመናዊ ሰው ቅርበት ያለው የትኛው ቅሪተ አካል ነው?

## ◈ጥንታዊ የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት መንግሥታት




*ምስል 1.6 የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥታት*

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ መንግሥት አስቀድሞ ከተመሠረተባቸው ጥቂት አገሮች መካከል አንዷ ናት:: በጥንት ጊዜ በኢትዮጵያ አያሌ መንግሥታት ነበሩ::

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የነበሩ ጥንታዊ መንግሥታትን ዘርዝሩ::
- ጥንታዊ መንግሥታት የነበሩበትን አካባቢ ግለጹ::

## 1. ፑንት

ፑንት በኢትዮጵያ እንዲሁም በአፍሪካ ቀንድ የተመሰረተ ቀደምት መንግሥት ነበር:: ይህ መንግሥት ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት በክልሉ ተመሥርቶ እንደነበር ታውቋል:: የፑንት መንግስት ዳር ድንበር የአሁኖቹን የአፍሪካ ቀንድ አገሮች ያጠቃልል ነበር:: ፑንት ከጥንታዊ ግብጻውያን ጋር የንግድ ግንኙነት ነበረው:: በዚህም ምክንያት የግብጽ የንግድ መርከቦች በተደጋጋሚ ወደ ፑንት ይመላለሱ ነበር:: ዕጣንና ከርቤም ከፑንት ይገዙ ነበር:: ጥንታዊ ግብጻውያን ሁለቱን የእጣን ዓይነቶች ለአምልኮ ሥርዓታቸው ይጠቀሙባቸው ነበር:: በቤተ መቅደሶቻቸውም እነዚሁኑ የእጣን ዓይነቶች ያጨሱ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ::

## 2.ዳኣማት

- የዳኣማት መንግሥት መቀመጫው የት ነበር?

ዳኣማት ከ2,500 ዓመታት በፊት በሰሜናዊ ኢትዮጵያ የነበረ መንግስት ነው:: የዳኣማት ማዕከል የነበረበት ሥፍራ ከዛሬዋ አክሱም ከተማ በስተደቡብ ነበር:: የዳኣማት መንግስት ከደቡብ አረቢያ ነዋሪዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበረው:: የዳኣማት ንጉሥ መጠሪያ ሙካሪብ ይባል ነበር:: ይህ መጠሪያ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ማዕረግ ነበር:: የደቡብ አረቢያ መሪዎችም ይህንኑ የማዕረግ ስያሜ ይጠቀሙበት ነበር:: በዚህም በሁለቱ ክልሎች መካከል የጠበቀ ግንኙነት እንደነበር ማወቅ ይቻላል::

## 3.አክሱም

- የአክሱም መንግሥት መገኛ የት ነበር?
- ስለ አክሱም ምን ምን ነገሮች ታውቃላችሁ?

አክሱም በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ ከሚገኙ ከተሞች አንዷ ናት:: አክሱም በአንድ ወቅት የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ አካባቢዎች መዲና ነበረች:: በቀድሞ የታሪክ ወቅት ጥንታዊ መንግሥቱም ሆነ ዋና ከተማው አክሱም በመባል ይታወቁ ነበር:: ከዚህ በታች ያለውን ሐውልት ተመልከቱ:: ይህ ሐውልት የጥንቱን አክሱም ዘመን ሥልጣኔን ይወክላል::



*ምስል 1.7 የአክሱም ሐውልት*

*በሥዕሉ ላይ ከሚታየው የአክሱም ሐውልት ጋር ተመሳሳይ የነበረ አንድ ሐውልት ቆሞ ከነበረበት ሥፍራ ከዛሬ ሰባ ዓመታት በፊት ተነቅሎ ወደ ሌላ ሀገር ተወስዶ ነበር:: ይሁንና በ1997 ዓ.ም ወደ ሀገሩ ተመልሶ በቀድሞ ሥፍራው እንዲቆም ተደርጓል:: አስደናቂ ተግባር አይመስላችሁምን?*

1. ስለመሆኑ ሐውልቱ ተወስዶ የነበረው ወደ የትኛዋ ሀገር ነው?
2. ያች ሀገር በዚያን ዘመን ከኢትዮጵያ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ነበራት?
3. ሐውልቱን ከቆመበት ሥፍራ አስነቅሎ ወደዚያች ሀገር ያስወሰደው ማነው?
4. ሐውልቱ ወደዚያች ሀገር የተወሰደው ለምን ዓላማ ነበር?
5. በመጨረሻ ሐውልቱ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ለማድረግ የተቻለው እንዴት ነው?

**ፋሽስት ጣሊያን ሀገራችንን በወረረበት ወቅት በሙሶሎኒ ትዕዛዝ የአክሱም ሐውልት ከቆመበት ተነቅሎ ወደ ሮም ተወስዶ ከረዥም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ ድርድር በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሊመለስ ችሏል::**

አክሱም እንደ መንግሥት የተቋቋመው በ150 ዓመተ ዓለም ነበር:: በዚያን ዘመን የአክሱም ግዛት የአሁኖቹን የትግራይ፣ የአማራ፣ የአፋር፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥታትንና የኤርትራን ደቡባዊ ክፍል ያጠቃልል ነበር::

የአክሱማውያን ምጣኔ ሀብት የተመሠረተው በግብርና ላይ ነበር:: በኋላ ግን ንግድ ዋነኛ የአክሱማውያን መሪዎች የገቢ ምንጭ ሊሆን ችሏል:: በቀይ ባሕር ላይ ጥንታዊዋ የአዱሊስ ወደብ ዋነኛዋ የንግድ ማዕከል ነበረች::

በወቅቱ የአክሱማውያን ማኅበረሰብ ገበሬዎችን፣ የመሬት ከበርቴዎችን፣ ነጋዴዎችንና ባሪያዎችን ያካተተ ነበር:: አክሱማውያን ከፍተኛ የቴክኖሎጂ አቅም ነበራቸው:: በዚህም የተነሣ መርከቦች፣ አብያተ መንግሥታት፣ ቤተ መቅደሶችና ሐውልቶች መገንባት ችለው ነበር:: ሐውልቶቹ የተቀረጹት ከተላልቅ ቋጥኞች ነበር:: የአክሱማውያን ሐውልቶች በአሁኑ ወቅት በአክሱም ከተማ ቆመው ይታያሉ:: ሐውልቶቹ ለሀገራችን በቱሪስት መስህብነት ያገለግላሉ::

በታሪክ ሂደት ውስጥ የአክሱም መንግሥት ከስምንተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አንስቶ ሊዳከም ችሏል:: ለአክሱም መንግሥት መዳከም የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ:: ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል አንዱ የአረብ ሙስሊሞች መነሣትና በቀይ ባሕር ንግድ ላይ ተፎካካሪ ሆኖ መገኘት ነበር:: በዚህ ፉክክር ወቅት አረቦች የአዱሊስን ወደብ አወደሙ:: ስለዚህ አክሱማውያን ከንግድ ሲያገኙ የነበረውን ገቢ በማጣታቸው ኃይላቸው ተዳከመ:: ከውስጥም ተቀናቃኞች ተነሥተው ነበር:: እነርሱም የቤጃ አርብቶ አደሮች ነበሩ:: የቤጃ አርብቶ አደሮች በአክሱም መንግሥት ላይ ወረራ ማካሄድ ችለው ነበር:: በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሣ የአክሱም መንግሥት ተዳክሟል:: ይሁን እንጂ ይህ የተዳከመው የአክሱም መንግሥት በኢትዮጵያ አቆጣጠር እስከ 1142 ዓመተ ምሕረት ድረስ መቆየት ችሏል:: የመጨረሻ የአክሱም ንጉሥ የነበረው ድል ነአድ ቀስ በቀስ እየተጠናከረ በመጣ ገዥ መደብ ከሥልጣን ተወግዷል:: የአክሱም ሥርወ መንግሥትም ሥልጣኑን ለቋል::

## 4. ዛግዌ

- የዛግዌ መንግሥት መቀመጫ የት ነበር?
- የዛግዌ መንግሥትን ከቀደሙት መንግሥታት ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድን ነው?

የአክሱምን የመጨረሻ ንጉሥ ከሥልጣኑ ያስወገደው የገዥ መደብ ከአገው ሕዝቦች የተነሣ ነበር :: አገዎች የኩሽ ቤተሰብ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች ናቸው:: በወቅቱ የተጠናከረው ገዥ መደብ ዛግዌ የተሰኘ ሥርወ መንግሥት አቋቋመ:: የዚህ መንግሥት ዋና ከተማም አደፋ ትባል ነበር:: አደፋ በሰሜን ወሎ ቡግና ወረዳ የምትገኝ ከተማ ነበረች:: አደፋ በኋላ ሮሃ ቀጥሎም ላሊበላ የሚል ስያሜ ተሰጥቷታል:: ላሊበላ የሚለውን ስያሜ ያገኘችው ላሊበላ በመባል ከሚታወቀው ዝነኛ የዛጉዌ ንጉሥ ስያሜ ነበር::

እንደ አክሱም ሁሉ የዛግዌ ምጣኔ ሀብትም የተመሠረተው በግብርና ላይ ነበር:: በወቅቱ የዛግዌ ማኅበረሰብ አባላት በአብዛኛው የመሬት ከበርቴዎችና ገበሬዎች ነበሩ:: በሃይማኖትም ረገድ የዛግዌ ማኅበረሰብ የክርስትና፣ የእስልምና፣ የአይሁድና የልማዳዊ እምነቶች ተከታይ ነበር:: የዛግዌ ገዢዎች ከዓለም የክርስቲያንና ሙስሊም መንግሥታት ጋር በወዳጅነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ነበራቸው:: በዛግዌ ዘመነ መንግሥት በአውሮፓ ክርስቲያኖችና በመካከለኛ ምሥራቅ ሙስሊሞች መካከል ከፍተኛ ደም ያፈሰሰ ጦርነት ተካሂዶ ነበር:: ይሁንና የዛግዌ ገዢዎች ክርስቲያን ቢሆኑም የዚህ ጦርነት ተካፋይ አልነበሩም:: ከዚያ ይልቅ ከሁለቱም ወገኖች ጋር ወዳጅነት መሥርተው ነበር:: በዚህም ምክንያት ሙስሊም የነበረው የኢየሩሳሌም ገዥ ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያ የሚሆን መሬት መስጠቱ ይታወቃል:: ይህ ድርጊት በዚያን ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በሰላም አብረው መኖራቸውን የሚያመላክት ተጨማሪ ማስረጃ ነው::

የዛግዌ ገዥዎች አብዛኛውን ጊዜያቸውን ለሃይማኖት አገልግሎት ያውሉ ነበር:: በዚህም ምክንያት በወቅቱ ድንቅ ውቅር አብያተ ክርስቲያን መገንባት ችለዋል:: የታነጹት አብያተ ክርስቲያን በቀድሞ ሥፍራቸው ቆመው ይገኛሉ:: ልክ እንደ አክሱም ሐውልቶች ሁሉ የዛግዌ አብያተ ክርስቲያንም ከቋጥኝ አለት ተፈለፍለው የታነጹ ናቸው:: በዚህ የተነሣም ሰዎች ውቅር አብያተ ክርስቲያን ብለው ይጠሯቸዋል፡፡ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የላቀ ድርሻ ካላቸው የቱሪስት መስህቦች ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛሉ:: (ምስል 1.8 ተመልከቱ)::

- በሥዕሉ ስለሚታየው ቤተ ክርስቲያን ምን ታውቃላችሁ?
- በቤተ ክርስቲያኑና በአክሱም ሐውልት መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?



ምስል 1.8 የላሊበላ ውቅር ቤተ ክርስቲያን

## ◈ የሰሎሞናዊያን ሥርወ መንግሥት

የዛግዌ ሥርወ መንግሥት የስልጣን ዘመን ያበቃው በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1262 ዓ.ም ነበር:: ለዛግዌ ሥርወ መንግሥት መውደቅ ምክንያት የሆነው ‹‹የሰሎሞናዊ›› ገዥ መደብ መጠናከር ነበር:: ‹‹የሰሎሞናዊ›› ገዥ መደብ የዛግዌን መንግሥት በማስ ወገድ የመንግሥት ስልጣን ባለቤት ሆኗል:: አዲሶቹ መሪዎች ሥርወ መንግሥታቸውን ‹‹የሰሎሞናዊ›› ሥርወ መንግሥት ብለው ሰይመውታል:: ይህ በዚያን ጊዜ የነበረው መንግሥት በጥቅሉ የክርስቲያን መንግሥት በመባል ይታወቅ ነበር:: በመጀመሪያ የዚህ መንግሥት ማዕከል ደቡብ ወሎ ላይ ተመሥርቶ ነበር:: በኋላ ግን በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ወደሚገኘው ሸዋ ተዛውሯል::

በታሪክ እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ መካከለኛው ዘመን በክርስቲያኖችና በሙስሊም ሡልጣኔት መካከል ረዥም ጊዜ የወሰደ ጦርነት ተካሂዶ ነበር:: የግጭቱ መንሥኤ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን የፖለቲካ ሥልጣንና ንግድን በቁጥጥር ሥር ለማዋል የተደረገ ፉክክር ነበር:: ይህ ጦርነት ለክርስቲያኑ መንግሥት ቀስ በቀስ እየተዳከመ መምጣት ምክንያት ሆኗል:: በዚህም የተነሣ የክርስቲያኑ መንግሥት ማዕከሉን ከአባይ ወንዝ በስተሰሜን አዛውሯል:: በዚህም ምክንያት ጎንደር ዋና ከተማ ሆና ነበር:: የክርስቲያኑ መንግሥትም የጎንደር መንግሥት በሚል ስያሜ ይታወቃል:: በዚያን ወቅት የነበሩት ብዙዎቹ የጎንደር ነገሥታት በቤተ መንግሥትነት የሚያገለግሉ ሕንፃዎች መገንባት ችለዋል:: በአሁኑ ወቅት ሕንጻዎቹ በጎንደር ታዋቂ የቱሪስት መስህቦች ናቸው::(ምስል 1.9 ተመልከቱ)::



ምስል 1.9 የጎንደር አብያተ መንግሥታት

## 5. የሙስሊም ሡልጣኔቶች

- በኢትዮጵያ የሙስሊም ሡልጣኔቶች መቀመጫ የት ነበረ?

በቀድሞ ጊዜ የዘይላ ወደብ የኢትዮጵያ ዋና የንግድ ማዕከል እንደነበረች ይታወቃል:: በአጠቃላይ ዘይላ እስልምና ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ እንዲስፋፋ ምክንያት ሆና ነበር:: ከ10ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ወደ መሐል ኢትዮጵያ በሚያስገቡት የንግድ መስመሮች ላይ የሙስሊም ሡልጣኔቶች መቋቋም ችለዋል:: የእነዚህ መንግሥታት መሪዎች ሱልጣን ይባሉ ነበር:: አዲስ የተመሠረቱት የሙስሊም መንግሥታትም ሡልጣን ከሚለው ከመሪያቸው ማዕረግ በመነሣት ሡልጣኔቶች ይባሉ ነበር:: በ10ኛውና በ16ኛው ክፍለ ዘመናት መካከል በኢትዮጵያ በርካታ የሙስሊም ሡልጣኔቶች ነበሩ:: ከሙስሊም ሡልጣኔቶች በጣም የታወቁት ሀዲያ፣ ኢፋት፣ ባሌ፣ ዳዋሮ፣ ዱራ፣ አዳልና ሸዋ ነበሩ:: ከሁሉም ሙስሊም ሡልጣኔት የኢፋት ሡልጣኔት በጣም ጠንካራ ነበር:: የኢፋት ሡልጣኔት መሥራች ኡመር ወላስማ ይባላል:: ይህ ሡልጣን በራሱ ስም የሚጠራ የወላስማ ሥርወ መንግሥትን አቋቁሟል:: ከ14ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የወላስማ መሪዎች ማዕከላቸውን ወደ ምሥራቃዊ ኢትዮጵያ አዛውረዋል:: በአዲሱ ማዕከል የታዋቂው የአዳል ሡልጣኔት መሪዎች ሆነዋል:: ሐረር የአዳል ወላስማ መሪዎች የፖለቲካ ማዕከል ነበረች::

በ16ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ኢማም አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ (አህመድ ግራኝ) የአዳል መሪነቱን ቦታ ወስዷል:: ሐረርንም ማዕከሉ አድርጓል:: ከ1521 እስከ 1535ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1529-1543) ኢማም አህመድ የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት መሪ ሆኖ ነበር:: ከእርሱ የሥልጣን ዘመን በኋላ በሐረር ዙሪያ ግንብ ሊገነባ ችሏል:: የሐረርን ከተማ ከጠላት ለመከላከል በኢሚር ኑር ሙጃሂድ አማካይነት የሐረር ግንብ ተገንብቷል:: አሁንም ግንቡ በጥንታዊቷ ሐረር ከተማ ዙሪያ ይገኛል:: ይህ ግንብ በአሁኑ ጊዜ የጀጎል ግንብ በመባል ይታወቃል::

በ17ኛው ክፍለ ዘመን በቀድሞው የአዳል ግዛት አዲስ መንግሥት ብቅ አለ:: ይህ መንግሥት የሐረር ኤሚሬት ይባል ነበር:: የዚህ መንግሥት መሥራች ኤሚር አሊ ኢብን ዳውድ ነበር:: ይህ መሪ የሐረሪ ሕዝብ የገኘ መደብ አባል ነበር:: የሐረሪ ሕዝብ የኢትዮጵያ የሴም ቤተሰብ ቋንቋ ተናጋሪ ነው:: የመጨረሻው የሐረር መሪ ኤሚር አብዱላሂ ነበር:: በመጨረሻ በ1887 ዓ.ም የሐረር ኤሚሬት የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ አካል ሆኗል::



ምስል 1.10 ኢሚር አብዱላሂ

## 6. የዳሞት መንግሥት

- ዳሞት በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ሥፍራዎች በየትኛው የኢትዮጵያ አካባቢ ይገኙ ነበር?
- በአሁኑ ጊዜ ዳሞት የሚል መጠሪያ ያላቸውን ጥቂት ሥፍራዎች ጥቀሱ::

ዳሞት ከጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥታት አንዱ ሲሆን ከአክሱም መንግሥት ዘመን አንሥቶ የነበረ ነው:: የተመሠረተው ከዓባይ ወንዝ በስተደቡብ በኩል ነበር:: ሞቶለሚ በ13ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ስመ ጥር የዳሞት ገዥ ነበር:: በአሁኑ ወቅት በወላይታ ዞን ዳሞት ዳሌ የሚባል ወረዳ አለ:: በዚያው ወረዳ ደግሞ ዳሞት በመባል የሚታወቅ ኮረብታ ይገኛል:: ይህ ሥፍራ የጥንታዊው ዳሞት ግዛት አካል ነበር:: በ14ኛው ምዕተ ዓመት ዳሞት በክርስቲያኖች በወረራ በመያዙ ሕልውናው አክትሟል::

## 7. የወላይታ መንግሥት

- **የወላይታ መንግሥት የተመሠረተው በየትኛው አካባቢ ነበር?**

ከዳሞት መንግሥት ውድቀት በኋላ የወላይታ መንግሥት ብቅ አለ:: የወላይታ መንግሥት መሥራች ሞተለሚ የተባለው የዳሞት ገዥ ነበር:: የወላይታ ገዥዎች የሁለት ሥርወ መንግሥታት አባላት ነበሩ:: የመጀመሪያው የወላይታ ገዥ ሥርወ መንግሥት ወላይታ ማላ በመባል ይታወቅ ነበር:: ከ15ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ደግሞ ትግሬ በመባል የሚታወቅ ሥርወ መንግሥት በቦታው ተተክቷል:: የዚህ ሥርወ መንግሥት መሥራቾች የሰሜን ኢትዮጵያ ሠፋሪዎች ነበሩ::

የወላይታ መሪዎች ካዎ በመባል የሚታወቅ የተከበረ ማዕረግ ነበራቸው:: ትርጉሙም ንጉሥ ማለት ነው:: የወላይታ መንግሥት ምጣኔ ሀብት የተመሠረተው በግብርና ላይ ነበር:: በወቅቱ የሚመረቱት ሰብሎች እንሰት፣ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ቡና፣ ትምባሆና ጥጥ ነበሩ:: ከዚህ በተጨማሪም ወላይታ ከአጎራባች መንግሥታትና ሕዝቦች ጋር የንግድ ግኑኝነት ነበረው:: የመጨረሻው የወላይታ ንጉሥ ካዎ ጦና ነበር:: በ1886 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1894) በተደረገው ጦርነት የወላይታ መንግሥት በመሸነፉ የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ግዛት አካል ሆኗል::



*ምስል 1.11 ካዎ ጦና*

## 8. የኢናርያ መንግሥት

- **የኢናርያ መንግሥት የተመሠረተው በየትኛው የኢትዮጵያ አካባቢ ነበር?**
- **የኢናርያ መንግሥት የሚታወቀው በምን ነበር?**

በመካከለኛው ዘመን በኢትዮጵያ ከነበሩት መንግሥታት አንዱ ኢናርያ ነበር:: ይህ መንግሥት ከጎጀብ ወንዝ በስተሰሜን ምሥራቅ ይገኝ ነበር:: በዚህ ዘመን ኢናርያ የታወቀ የወርቅ ንግድ ማዕከል ነበር:: በ18ኛው ክፍለ ዘመን ሊሙ በመባል የሚታወቅ የኦሮሞ ጎሳ ኢናርያን ያዘ:: ይህ ጎሳ ሊሙ ኢናርያ የሚባል የኦሮሞ መንግሥት አቋቋመ:: የዚህ መንግስት መዲና ሰቃ ነበረች:: በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሰቃ በኢትዮጵያ ለተዘረጋው የረዥም ርቀት ንግድ ማዕከል ሆና አገለገለች:: ሊሙ ሰቃ በአሁኑ ጊዜ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከሚገኙት ከተሞች አንዷ ናት::

## 9. የከፋ መንግሥት

- **የከፋ መንግሥት መገኛ የት ነበር?**

ከፋ በመካከለኛው ዘመን ከጎጀብ ወንዝ በስተደቡብ በኢትዮጵያ ከነበሩት መንግሥታት አንዱ ነበር:: የከፋ መንግሥት ሕዝብ ከፊቾ በመባል ይታወቃል:: አሁንም ሆነ ቀድሞ የከፊቾ ሕዝብ መኖሪያ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ነው:: ከፊቾዎች የኢትዮጵያ ኦሞቲክ ቤተሰብ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች ናቸው:: በወቅቱ የከፋ ምጣኔ ሀብት የተመሠረተው በግብርና ላይ ነበር:: አካባቢው ለኢትዮጵያ መካከለኛው ዘመን የረዥም ርቀት ንግድ የአብዛኛዎቹ ሸቀጦች ምንጭም ነበር:: የንግድ ሸቀጦቹ ወርቅ፣ ቡናና ዝባድ ነበሩ:: ይህ አካባቢ የቡና ተክል መገኛ በመሆን ይታወቃል:: ኮፊ (Coffee) የሚለውን የእንግሊዝኛ መጠሪያ ለቡና የተሰጠውም የቡና ተክል ከተገኘበት ከፋ ከሚለው ስያሜ እንደሆነ ይነገራል::



*ምስል 1.12 ታቶ ጋኪ ሼሬቾ*

ከዚህም በላይ ከፋ በኢትዮጵያ መካከለኛው ዘመን ከነበሩት መንግሥታት ጠንካራው ነበር፡፡ በመከላከያ ኃይሉም የታወቀ ነበር፡፡

የከፋ መሪዎች ታቶ የሚባል መጠሪያ ነበራቸው፡፡ በዚህ የመሪዎች መጠሪያ የታወቀው የመጨረሻው የከፋ መሪ ታቶ ጋኪ ሼሬቾ ነበር፡፡ የከፋ መንግሥት በ1889 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1897) በነበረው ጦርነት በመሸነፉ የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ አካል ሊሆን ችሏል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 1.2

**ክንውን ለ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- በአክሱም ሐውልቶችና በዛግዌ ወቅር አብያተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ልዩነትና ተመሳሳይነት ግለፁ፡፡
- ኢትዮጵያውያን ከአክሱም ሐውልትና ከዛግዌ ውቅር አብያተ ክርስቲያን የሚያገኙአቸውን ጥቅሞች ዘርዝሩ፡፡
- የአክሱም ሐውልትና የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን ያላቸውን ፓለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ፋይዳዎች አስረዱ፡፡
- የጀጐል ግንብ በማን ዘመንና ለምንስ ተገነባ?
- በዓለም ላይ ከፋ በሚለው ስያሜ መነሻነት የሚታወቀው ሰብል በኢትዮጵያ ውስጥ ምን ተብሎ ይጠራል?
- ይህ ሰብል በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት ውስጥ ያለው ድርሻ ምን ያህል ነው?
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት የመጀመሪያው መንግሥት ማን በመባል ይታወቃል?
- የከፋ፣ የወላይታና የሐረር ኤሚሬት የመጨረሻ ገዥዎች ስም ተናገሩ፡፡
- ለአክሱም መንግሥት መውደቅ ምክንያቶቹ ምን ነበሩ?
- በኢትዮጵያ የሙስሊም መንግሥታት ሡልጣኔት ተብለው የሚጠሩት ለምን ነበር?
- በኢትዮጵያ በመካከለኛው ዘመን የወላይታና ከፋ መንግሥታት ዋነኛዎቹ መተዳደሪያዎች የትኞቹ የሥራ መስኮች ነበሩ?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- የኢትዮጵያን ንድፍ ካርታ በመሳል የሚከተሉትን አሥፍሩ፡፡
  - → ወንዞች፡- ጎጀብ፣ ዓባይ፣ ጊቤ፣ አዋሽና ኦሞ፡፡
  - → ሐይቆች፡- ጣና፣ አባያና ዝዋይ፡፡
  - → ጥንታዊና የመካከለኛ ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥታት አክሱም ዛግዌ፣ ወላይታ፣ የሐረር ኤሚሬት፡፡

ስለሚከተሉት ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥታት ዘገባ አጠናቅሩ፡፡

- አክሱም - የሐረር ኤሚሬት
- ዛግዌ - ኢፋት

## ◈ታሪካዊና ፖለቲካዊ ክንዋኔዎች

ቀደም ሲል በቀረቡት ንዑሳን ርዕሶች ስለኢትዮጵያና ስለ አፍሪካ ቀንድ አካባቢዎች ሕዝቦችና መንግሥታት የተማራችሁትን ታስታውሳላችሁ። እነዚህ ሕዝቦችና መንግሥታት በተለያዩ ጊዜያት በአካባቢው የነበሩ ናቸው። እያንዳንዱ ሕዝብና መንግሥት ጠቃሚ ተግባራት ማከናወናቸው ይታወቃል። ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥታትና ሕዝቦች የሚከተሉትን ታሪካዊና ፓለቲካዊ ዕሴቶች ፈጥረዋል።

### 1. ፑንት እና ዳኣማት

- ከጥንታዊ ግብጽና ደቡብ አረቢያ ጋር የንግድ ግንኙነት ነበራቸው።
- ሁለቱም መንግሥታት ነገሥታት ነበሩአቸው።
- የዳኣማት ነገሥታት መጠሪያ ሙካሪብ በመባል ይታወቃል።

### 2. አክሱም

- ጠንካራ ነገሥታት ነበሩት።ለምሳሌ በ4ኛው ክፍለ ዘመን የአክሱም ንጉሥ የነበረው ኢዛና የሜሮይን መንግሥት አስወግዷል።
- ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስትናን የመንግሥቱ ሃይማኖት አድርጓል።
- ከጥንታውያን ግሪኮችና ሮማውያን ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበረው።
- የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ሳንቲሞች በመቅረጽ ተጠቅሟል።
- አብያተ መንግሥታት፣ ቤተ መቅደሶችና ሐውልቶች ገንብቷል።
- ግዛቱን እስከ አሁኗ ሱዳን ድረስ አስፋፍቶ ነበር፤ ደቡብ አረቢያንም የገዛ ነበር።

### 3.ዛግዌ

- በወቅቱ ከነበሩት የክርስትናና የሙስሊም መንግሥታት ጋር ሰላማዊ ግንኙነት ነበረው።
- አያሌ ውቅር አብያተ ክርስቲያን ገንብቷል።

### 4.የጎንደር መንግሥት

- አብያተ መንግሥታትን አንጿል
- አብያተ ክርስቲያን ገንብቷል።

### 5. ሐረር

- በሐረር ከተማ ዙሪያ የድንጋይ ግንብ ገንብቷል።
- በመካከለኛው ዘመን ሐረር በኢትዮጵያ ዝነኛ የሙስሊም ባህል ማዕከል እንድትሆን አድርጓል።

### 6. ኦሮሞ

- በጥንት ዘመን ገዳ የተሰኘ አስተዳደራዊ ሥርዓት የነበራቸው የኢትዮጵያ ሕዝቦች የትኞቹ ናቸው?

በኦሮሞ ኅብረተሰብ የሕዝብ አስተዳደር በገዳ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ነበር። በኦሮሞ የገዳ ሥርዓት በየስምንት ዓመቱ ከሚካሄድ ምርጫ በኋላ የሥልጣን ሽግግር ይደረግ ነበር። ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ግን በአንዳንድ የኦሮሞ ጐሣዎች ዘንድ በተለይም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የገዳ ሥርዓት መለወጥ ጀምሮ ነበር። በዚህ አካባቢ ሰባት የኦሮሞ መንግሥታት ተመሥርተው ነበር። ሁለቱ መንግሥታት የተመሠረቱት በወለጋ ነበር። እነዚህ መንግሥታት ሌቃ ቄለምና ሌቃ ነቀምቴ በመባል ይታወቃሉ። የተቀሩት አምስቱ በጊቤ ወንዝ አካባቢ ተመሥርተው ነበር። እነዚህ መንግሥታት ሊሙ ኢናርያ፣ ጂማ፣ ጌራ፣ ጎማና ጉማ ይባሉ ነበር። እነዚህ የተለያዩ መንግሥታት ከ1878 ዓ.ም (እ.ኤ.አ ከ1886) ጀምሮ የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ አካል ሆነዋል። በሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚኖሩ የኦሮሞ ጎሣዎች በገዳ ሥርዓት አስተዳደር ሥር መኖር ቀጥለው ነበር። ይሁን እንጂ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ ሁሉም ጎሣዎች የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ አካል ሆነዋል።

### 7. ሲዳማና ጌዴኦ

በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል የሚገኙ የኩሽ ቤተሰብ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች ናቸው፡፡ የኦሮሞ ገዳ ሥርዓትን የመሰለ የአስተዳደር ሥርዓት ነበራቸው፡፡ የሲዳማ የአስተዳደር ሥርዓት ሉዋ ይባል ነበር፡፡ የጌዴኦ አስተዳደር ሥርዓት ግን እንደ ኦሮሞው ገዳ በመባል ይታወቅ ነበር፡፡

### 8. ኮንሶ

ኮንሶዎች በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል የሚገኙ የኩሽ ቤተሰብ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ናቸው፡፡ ኮንሶዎች በዘር ሐረግ ላይ በተመሠረተ መስፈርት ለሥልጣን የሚበቁ ገዢዎች ነበሯቸው፡፡ ኮንሶዎች በእርሻ እርከን ሥራ ባሕላዊ እውቀታቸው ይታወቃሉ፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች 1.2**

**ክንውን ሐ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- አራቱ የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥታት ቅርሶች ሕያው ትሩፋቶች ምንድን ናቸው?
  - አክሱም - የጎንደር መንግሥት
  - ዛጉዌ - የሐረር ኤሚሬት
- የእነዚህን ቅርሶች ወቅታዊ ሁኔታ ግለፁ፡፡
- በዓለም አቀፍ የቅርስ ሀብትነት ተመዝግበዋል?ከሆነስ ይህ ምን ማለት ነው?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- የኢትዮጵያን የቅርስ ማዕከልነት የሚያሳዩ የስጦታ ካርዶችና ምስሎች አሰባስቡ፡፡
- በክፍላችሁ ማዕዘን ላይ የማሳያ ሥፍራ አዘጋጁ፡፡
  ለክፍላችሁ ተማሪዎች እንደሚከተለው ዘገባ አቅርቡ፡፡
  - ስለ ኢትዮጵያ ቅርሶች ፋይዳ
  - የቅርሶችን ደኅንነት በመጠበቅ ረገድ የወጣቶች ሚና
- ቡድን መሥርታችሁ የአክሱም፣ የዛግዌ፣ የጎንደር፣ የሐረር፣ የኮንሶና የኦሮሞ ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥታትና ሕዝቦች የሥራ ውጤቶችን በመመዝገብ የአጠናቀራችሁትን ዘገባ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## 1.3. የኢትዮጵያ አንድነትና ዘመናዊነት

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

*ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-*

- የኢትዮጵያውያን ልበ ሙሉነትና አንድነት ለአድዋ ድል የነበረውን ጠቀሜታ ታብራራላችሁ፡፡
- በኢትዮጵያ ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ መጀመር ስላበረከተው አስተዋፅኦ ትወያያላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ዘመናዊነት
- አንድነት

## ◈ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ለአድዋ ድል የነበረው ጠቀሜታ

### የአንድነት አስፈላጊነት

- የኢትዮጵያ ውሕደት ተግባራዊ የሆነው እንዴት ነበር?
- የኢትዮጵያ ውሕደት ስነጻነቷ መጠበቅ ምን ፋይዳ ነበረው?

አሥራ ዘጠነኛውና ሃያኛው ክፍለ ዘመናት በኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ልዩ ሥፍራ አላቸው:: በእነዚህ ዘመናት በኢትዮጵያ ውስጥ ሦስት ዐበይት ሁኔታዎች ተከስተዋል::

### ሀ. የኢትዮጵያ ውሕደት

ኢትዮጵያን የማዋሐድ ሂደት የተጠናቀቀው በ19ኛ ምዕተ ዓመት ማብቂያ ላይ ነው:: በዚህም የተነሣ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ አካባቢ የነበሩ የተለያዩ መንግሥታትና ሕዝቦች በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር ተጠቃለዋል:: ይህ አንድነታቸው ወራሪዎችን ድል በመንሣት ረገድ የላቀ አስተዋጽዖ ነበረው:: ኢትዮጵያውያን ይህን ድል እንዴት መቀዳጀት እንደቻሉ ታውቃላችሁ? የዚህን ጥያቄ ምላሽ ቀጥሎ ታገኛላችሁ::

### ለ. በውጭ ወራሪዎች ላይ የተገኘ ድል

የአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የአፍሪካ ሕዝቦች በአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ሥር የወደቁበት ነበር:: ኢትዮጵያ ግን በአፍሪካ ብቸኛ ነጻ ሀገር ነበረች:: ይህ ሊሆን የቻለው ኢትዮጵያውያን የጣሊያን ቅኝ ገዢዎችን በአድዋ ጦርነት ላይ ድል በመንሣታቸው ነበር:: የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም (እ.ኤ.አ መጋቢት 1 ቀን 1896) በጣሊያንና በኢትዮጵያ መካከል በአድዋ ከተማ አቅራቢያ ላይ ጦርነት ተካሄዶ ነበር:: በዚህ ጦርነት የጣሊያንን ወራሪዎች ለመዋጋት ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ተካፋይ ሆነዋል::

**የአድዋ ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት መደምደም ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ኅብረት የላቀ አስተዋጾ ነበረው:: የአድዋ ድል ጥቁሮች በነጮች ላይ የተቀዳጁት የመጀመሪያው ድል ነበር:: ይህም ድል ኢትዮጵያ በሌሎች የአፍሪካ ሕዝቦች ዘንድ የነበራትን ክብር ከፍ አድርጓል:: በዚህ የተነሣ አያሌ አፍሪካውያን ኢትዮጵያን የነጻነት ተምሳሌት አድርገው መመልከት ችለዋል:: ይህ ደግሞ የአፍሪካ ኅብረትና ሌሎች የዓለምአቀፋዊና አኅጉራዊ ድርጅቶች ጽ/ቤቶች በኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ላይ እንዲመሠረቱ ዐቢይ ምክንያት ሆኗል::**

ስለዚህ እንደ ኢትዮጵያዊነታችሁና እንደ አፍሪካዊነታችሁ አያት ቅድመ አያቶቻችሁ በተቀዳጁት ድል ልትኩሩ ይገባችኋል:: እናንተም ይህንኑ ፈለግ በመከተል ሀገራችሁን ከማንኛውም ጥቃት ለመከላከል ራሳችሁን ማዘጋጀት ይኖርባችኋል::

### ሐ. በኢትዮጵያ የዘመናዊነት አጀማመር

- ዘመናዊነት ምን ማለት ነው?
- በመንደራችሁ ምን ዓይነት ዘመናዊ ተቋማት ይገኛሉ?

በ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ የተለያዩ ዘመናዊ ተቋማት ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል:: እነዚህ ተቋማት ኢትዮጵያን ወደ ዘመናዊነት መርተዋል::

በኢትዮጵያ ዘመናዊነት ረዥም ጊዜ የወሰደ ሂደት ነበር፡፡ ዘመናዊነት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ጀምሮ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ዘልቋል፡፡ ዘመናዊነት በኅብረተሰብ ውስጥ ለውጥ ማምጣት ማለት ነው፡፡ በዘመናዊ ተቋማት መከሰት ምክንያት ለውጦቹ በተለያዩ መንገዶች ይፈጸማሉ፡፡ በመነሻነት ተቋማቱ እንዲታወቁ የተደረጉት በአብዛኛው በትላልቅ ከተሞች ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በእነዚህ ከተሞች በተለይም በዋና ከተማው ዘመናዊነት ላለመቀበል ጠንከር ያሉ ተቃውሞዎች ተከስተው ነበር፡፡ ይሁንና ቀስ በቀስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአዳዲሶቹ ተቋማት መጠቀምና የራሱ ማድረግ ችሏል፡፡ ከለውጦቹ መካከል፡-

- የትላልቅና ትናንሽ ከተሞች ዕድገት፡-
- የትምህርትና የትምህርት ቤቶች መስፋፋት፡-
- ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙ ሰዎች ብቅ ማለት፡-
- የመገናኛና የመጓጓዣ አገልግሎቶች መስፋፋት፡-
- የሰዎች ከቦታ ቦታ መዘዋወርና የሃሳቦች መንሸራሸር ዕድገት፡-
- የግል ንጽሕና አያያዝና የጤና አጠባበቅ መስፋፋትና
- ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት መመሥረት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

## የመጀመሪያዎቹ ዋና ዋና ዘመናዊ ተቋማት በኢትዮጵያ

### 1. ብሔራዊ የመገበያያ ገንዘብ

የመገበያያ ገንዘብ ለንግድ ሥራ እንቅስቃሴና ለክፍያ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የመገበያያ ገንዘብ የሉዓላዊነት ምልክትም ነው፡፡ አጼ ምኒልክ የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ የመገበያያ ገንዘብ በ1894 ዓ.ም በይፋ አሳትመዋል፡፡ ይህ ብሔራዊ የመገበያያ ገንዘብ ከማሪያ ቴሬዛ የመገበያያ ገንዘብ ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡ ይህ ገንዘብ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው ጣሊያን ሀገር ነበር፡፡ ከጣልያን ጋር በተፈጠረው ግጭት የተነሣ የገንዘብ ኅትመቱ ወደ ፈረንሳይ ዋና ከተማ ወደ ፓሪስ ተዛውሯል፡፡

### 2. የባቡር ሐዲድ ግንባታ

የባቡር መንገድ ዘመናዊ የመጓጓዣ አውታር ነው፡፡ የባቡር ሐዲድ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የታወቀው በ1886 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1894) ነበር፡፡ አዲስ አበባን ከጅቡቲ ጋር በባቡር መስመር ለማገናኘት ከአንድ የፈረንሳይ ኩባንያ ጋር የስምምነት ውል ተፈርሟል፡፡ የሐዲድ መስመሩ ግንባታ የተጀመረው በ1891 (እ.ኤ.አ በ1898) ነበር፡፡ በ1910 (እ.ኤ.አ በ1917) የሐዲድ መስመሩ አዲስ አበባ ደርሷል፡፡



ምስል 1.13 የባቡር ሐዲድ

## 3. ስልክና ቴሌግራም

የስልክና የቴሌግራም በኢትዮጵያ መታወቅ በአዲስ አበባ እና በጅቡቲ መካከል የተዘረጋው የሐዲድ መስመር ውጤት ነው:: የስልክና የቴሌግራም መስመሮቹ የተዘረጉት በሐዲድ መስመሩ ላይ በሚሠሩ ባለሙያዎች አማካይነት ነው::

## 4. የፖስታ አገልግሎት

በ1886 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1894) አጼ ምኒልክ የፖስታ ቴምብሮች እንዲታተሙ አዘው ነበር:: በዚህ ምክንያት የፖስታ ቴምብሮቹ በፓሪስ ከተማ ታትመዋል:: ይህም በመሆኑ ኢትዮጵያ በ1900 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1908) የዓለም አቀፍ ፖስታ አገልግሎት ኅብረት አባል እንድትሆን ተፈቅዶላታል:: ይህ ወቅት እውነተኛ የፖስታ አገልግሎት በኢትዮጵያ የተጀመረበት ወቅት ነበር::

## 5. ባንክ

የገንዘብ ዝውውርና የንግድ እንቅስቃሴዎች የባንክ አገልግሎት ይፈልጋሉ:: እነዚህን እንቅስቃሴዎች ለማቀላጠፍ በ1897 (እ.ኤ.አ በ1905) የአቢሲኒያ ባንክ በመባል የሚታወቀው የመጀመሪያው ባንክ በኢትዮጵያ ሊቋቋም ችሏል:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ይህ ባንክ የኢትዮጵያን የመገበያያ ገንዘብ የወረቀት ገንዘብን ጨምሮ ማቅረብ ችሏል:: የመጀመሪያው የወረቀት ገንዘብ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው በ1907 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1914 እና በ1915) ዓመታት ላይ ነበር::

## 6. ዘመናዊ ትምህርት ቤት

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዘመናዊ ትምህርት ቤት የዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ነበር:: ይህ ትምህርት ቤት በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ በሚባለው ሥፍራ ይገኛል:: የዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተቋቋመው በ1900 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1908) ነው::




*ምስል 1.14 ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት*

## 7. ሆስፒታል

የመጀመሪያው የመንግሥት ሆስፒታል የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ነው::ይህ ሆስፒታል የተቋቋመው በ1902 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1910) ነበር::



ምስል 1.15 የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል

## 8. ማተሚያ ቤት

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ማተሚያ ቤት የተቋቋመው በ1903 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1911) ነበር:: ይህ ማተሚያ ቤት አእምሮ በመባል ይታወቅ የነበረውን የአገሪቱን የመጀመሪያ ጋዜጣ ያትም ነበር:: የጋዜጣ ኅትመት ደግሞ አንዱ የዘመናዊነት መገለጫ ነበር::

## 9. ዘመናዊ ሆቴል

በ1899 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1907) እቴጌ ጣይቱ የመጀመሪያውን ሆቴል አቋቋሙ:: ያን ጊዜ ሆቴሉ እቴጌ ሆቴል በመባል ይታወቅ ነበር:: ይህ ሆቴል አሁን ፒያሳ ውስጥ ይገኛል:: በአሁኑ ጊዜ ሆቴሉ እቴጌ ጣይቱ ሆቴል በመባል ይታወቃል::



ምስል 1.16 እቴጌ ጣይቱ ሆቴል

## 10. የቧንቧ ውኃ

ከተሞች የንጹሕ ውኃ አቅርቦት ይፈልጋሉ፡፡ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የቧንቧ ውኃ ከእንጦጦ ተራራ አራት ኪሎ ወደሚገኘው የዳግማዊ ምኒልክ ቤተ መንግሥት እንዲደርስ ተደርጎ ነበር፡፡

## 11. የግድግዳ ሰዓት ጥቅም ላይ ማዋል

በዚሁ ጊዜ ትልቅ የግድግዳ ሰዓት ከቤተ መንግሥቱ ሕንጻዎች በአንዱ ላይ ተንጠልጥሎ ነበር፡፡ ይህ የግድግዳ ሰዓት ከርቀት ይታይ ነበር፡፡ የዚህ ሰዓት በዚያ ቦታ መገኘትና ከርቀት መነበብ ዜጎች ሥራቸውን ሰዓት በማክበር እንዲያከናውኑ ታስቦ ነበር፡፡ ይህም ሌላው የዘመናዊነት መገለጫ ነበር፡፡

## 12. የኤሌክትሪክ አገልግሎት

ኤሌክትሪክ የብርሃንና የኃይል ምንጭ የሆነ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጠት የተጀመረው በ1923 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ 1930) ነበር፡፡ መጀመሪያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኝ የተደረገው ታላቁ የምኒልክ ቤተ መንግሥት ነበር፡፡ ይህ የሆነው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓተ ንግሥ በተከናወነበት ወቅት ነበር፡፡

## 13. ዘመናዊ የመከላከያ ሠራዊት

ዘመናዊ የመከላከያ ሠራዊት በተሳካ ሁኔታ የተመሠረተው በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነበር፡፡ በ1923 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1930) በውጭ አገር ሰዎች ዘመናዊ ሠራዊት የማሠልጠን ሥራ ተጀምሮ ነበር፡፡ ሥልጠናውን መጀመሪያ የሰጡት ለቤተ መንግሥቱ የክብር ዘብ ነበር፡፡ በ1928 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1934) ዘመናዊ የሠራዊት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት በሆለታ ተቋቋሟል፡፡

ከላይ የቀረበው ዝርዝር በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በሃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ዘመናዊ ተቋማትን ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሂደት በሃያኛው ክፍለ ዘመንም ሳያቋርጥ ቀጥሏል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች 1.3

**ክንውን**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- የአድዋ ድል መታሰቢያ በሀገራችን ለምን በየዓመቱ ይከበራል?
- ጣልያን ኢትዮጵያን ለምን ወረረች?
- ኢትዮጵያውያን በጣሊያን ላይ ድል እንዲቀዳጁ አስተዋጾ ያደረገው ምክንያት ምን ነበር?
- የአድዋ ድል ለኢትዮጵያና ለመላው አፍሪካ ያለው ቁምነገር ምንድን ነው?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- በምትኖሩባቸው መንደሮች ወይም ከተሞች ወይም ገጠር አካባቢዎች ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ ወይም ጤና ጣቢያ፣ የቧንቧ ውሀ፣ ሆቴል፣ ማተሚያ ቤት፣ ባንክ፣ ስልክና ፖስታ ቤት መቼ እንደተቋቋሙ በማጥናት ውጤታችሁን ለክፍል ውይይት አቅርቡ፡፡
- በአካባቢያችሁ ስለአንድነት አስፈላጊነት የሚነገሩ ተረትና ምሳሌዎች በመሰብሰብ የክፍላችሁ ተማሪዎች እንዲወያዩባቸው አድርጉ፡፡
- የአድዋን ድል ታላቅነት አስመልክቶ ከስምንት እስከ አስር ስንኞች ያለው ግጥም ጻፉ፡፡

# 1.4 የሕዝብ አሰፋፈርና የባህል ልዩነት እንዲፈጠር ጉልህ ሚና ያላቸው ምክንያቶች

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የሕዝብ አሰፋፈር ልዩነት እንዲፈጠር ጉልህ ሚና ያላቸውን ምክንያቶች ትጠቅሳላችሁ፡፡
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሕዝብ አሰፋፈር ከአኗኗር ዘይቤ ጋር ያለውን ግንኙነት ታብራራላችሁ፡፡
- በኢትዮጵያ በከተማና በገጠር፣ በከፍተኛና በዝቅተኛ ሥፍራዎች በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል ያለውን የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ተመሳሳይነትና ልዩነት ትገልፃላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ሠፈራ
- ባህል
- ከተማ
- ገጠር

## ◈ የሕዝብ አሰፋፈር ልዩነት

- የአካባቢያችሁ ሕዝብ አሰፋፈር የተጠጋጋ ወይስ የተበታተነ ነው?
- የሕዝቡ ኑሮ የተመሠረተው በእርሻ ወይስ በከብት እርቢነት ነው?
- በሕዝብ አሰፋፈርና በምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ላይ ልዩነት የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

የሕዝብ አሰፋፈር በሁሉም አካባቢዎች ተመሳሳይ አይደለም፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች ሕዝብ ተጠጋግቶ ይኖራል፡፡ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ ተበታትኖ ይኖራል፡፡ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴም እንደዚሁ ከቦታ ወደ ቦታ የተለያየ ነው፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች በእርሻ ላይ የተመሠረተ አኗኗር ሲታይ በሌሎች ደግሞ በከብት እርቢነት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ የእነዚህ ልዩነቶች መንስኤ ምንድን ነው?



*ምስል 1.17 በከፍተኛ አካባቢ የሚታይ የሕዝብ አሰፋፈር*

ምስል 1.17 ከፍተኛ አካባቢዎች የሕዝብ አሰፋፈር ያለውን ገጽታ ያሳያል፡፡ ከምስሉ እንደሚታየው በከፍተኛ አካባቢዎች የሕዝብ አሰፋፈር የተጠጋጋ ነው፡፡



*ምስል 1.18 በዝቅተኛ አካባቢ የሚታይ የሕዝብ አሰፋፈር*

በዝቅተኛ አካባቢዎች የሚታይ የሕዝብ አሰፋፈር የተበታተነ ነው፡፡ በከፍተኛና በዝቅተኛ አካባቢዎች ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴም የተለያየ ነው፡፡ በከፍተኛ አካባቢዎች የሕዝብ ኑሮ በአብዛኛው በእርሻና በከብት እርቢነት የተመሠረተ ነው፡፡ በዝቅተኛ አካባቢዎች ደግሞ የከብት እርባታ ምጣኔ ሀብት በስፋት ይታያል፡፡ ይህን ርዕስ ጉዳይ ቀጥሎ በስፋት ትማራላችሁ፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች 1.4**

**ክንውን ሀ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

1. በከፍተኛና በዝቅተኛ አካባቢዎች መካከል ያለው የሕዝብ አሰፋፈር ልዩነት ምንድን ነው?
2. በከፍተኛና በዝቅተኛ አካባቢዎች በስፋት የሚታይ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ የትኛው ነው?
3. አካባቢያችሁ ከየትኛው ይመደባል? የአካባቢያችሁን ሕዝብ አሰፋፈርና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ እያነጻጸራችሁ ለክፍላችሁ ተማሪዎች አስረዱ፡፡

## ◈ የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ልዩነት

በከፍተኛና በዝቅተኛ አካባቢዎች መካከል ያለው ልዩነት በአሰፋፈርና በምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ሌሎች በርካታ ልዩነቶችም አሏቸው፡፡ ዋና ዋናዎቹ የአመጋገብ፣ የአለባበስና የአኗኗር ልዩነቶች ናቸው፡፡

### በባህልና በአኗኗር ዘይቤ ልዩነት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች

የሕዝብ አሰፋፈር በአየር ንብረት፣ በተፈጥሮ ሀብትና በመሬት አቀማመጥ መለያየት የተነሣ ሊለያይ ይችላል፡፡ ልዩነቱ እንዴት እንደሚፈጠር በዝርዝር እንመልከት፡፡

### 1. የአየር ንብረት

የአየር ንብረት በአንድ አካባቢ ለብዙ ጊዜ የሚታይ የአየር ሁኔታ ነው፡፡ ከአየር ንብረት ይዘቶች ዋነኞቹ የሙቀትና ቅዝቃዜ መጠንና የዝናብ ሥርጭት ናቸው፡፡ የአየር ንብረት በአንድ አካባቢ የሚስተዋልን የሕዝብ አሰፋፈር ሊወስን ይችላል፡፡ መለስተኛ ሙቀትና የተሰተካከለ የዝናብ ሥርጭት ያላቸው አካባቢዎች ለሰዎች ኑሮ ተመራጭ ናቸው፡፡ ምክንያቱም አካባቢዎቹ ለጤና ምቹ ከመሆናቸውም በላይ የተሰተካከለ የዝናብ ሥርጭት ስላላቸው ለእርሻ ሥራና ለከብት እርባታ ተስማሚ ናቸው፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች የተነሣ ብዙ ሰዎች በአካባቢው ለመኖር ይመርጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ የአካባቢው መሬት እንዲጣበብ ስለሚያደርግ የሕዝቡ አሰፋፈር የተጠጋጋ ይሆናል፡፡ ከፍተኛ ሙቀትና አነስተኛ የዝናብ መጠን ያላቸው አካባቢዎች ደግሞ ለኑሮ ተመራጭ ባለመሆናቸው ብዙ ሕዝብ አይሠፍርባቸውም፡፡ ስለዚህ የሕዝቡ አሰፋፈር የተበታተነ ነው፡፡ በእነዚህ ቦታዎች የከብት እርባታ በስፋት ይካሄዳል፡፡

### 2. የተፈጥሮ ሀብት

የሕዝብ አሰፋፈር ከተፈጥሮ ሀብት መኖርና ያለመኖር ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ውኃ ለመኖር ወሳኝ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ሰፍረው የሚታዩት በወንዝ ዳርና ውኃ በቅርበት በሚገኝባቸው አካባቢዎች ነው፡፡ ለም አፈር ሌላው የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡ ኑሮው በእርሻ ላይ የተመሠረተ ሕዝብ በአብዛኛው ሰፍሮ የሚታየው ለም አፈርና የተስተካከለ የዝናብ ሥርጭት ባላቸው አካባቢዎች ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሰዎች በአካባቢው እንዲኖሩ ስለሚስባቸው በአካባቢው የተጠጋጋ የሕዝብ አሰፋፈር ሊያስከትል ይችላል፡፡ በተቃራኒው በቂ የውሃ አቅርቦትና ለም አፈር የሌለባቸው አካባቢዎች ደግሞ የተበታተነ የሕዝብ አሰፋፈር ይኖራቸዋል፡፡

### 3. መልክዓ ምድር

መልክዓ ምድር ማለት በመሬት ላይ የሚገኙ እንደ ተራራ፣ ኮረብታ፣ አምባ ምድር፣ ሜዳና ሸለቆ የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል የመሬት ገጽታ ነው፡፡ ይህ የመሬት ገጽታ በሰዎች የአኗኗር ዘይቤ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ከሁሉም የመሬት ገጽታዎች መካከል አምባ ምድሮች ለኑሮ ተመራጭ ናቸው፡፡ የዚህ ዓይነት አካባቢዎች መካከለኛ ከፍታ ሲኖራቸው መለስተኛ ሙቀትና የተሰስተካከለ የዝናብ ሥርጭት አላቸው፡፡ እነዚህ አካባቢዎች ለጤና ምቹ ከመሆናቸውም በላይ ለም አፈርና ወንዞች የመሳሰሉ የተፈጥሮ ሀብቶች በስፋት አላቸው፡፡ ስለዚህም ለኑሮ ተመራጭ ናቸው፡፡

#### ሀ) ከፍተኛ ሥፍራዎች

ከፍተኛ ሥፍራዎች ለደህንነት ተመራጭ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ጠላትን በቀላሉ ለመከላከል ያስችላሉ፡፡ ስለዚህ ሰዎች በከፍተኛ አካባቢዎች ተጠጋግተው ይኖራሉ፡፡ በዚህ የተነሣም የሕዝብ አሰፋፈር የተጠጋጋ ይሆናል፡፡

#### ለ) ዝቅተኛ ሥፍራዎች

ዝቅተኛ አካባቢዎች በአመዛኙ ሜዳና ሸለቆዎች የበዛባቸው ናቸው፡፡ እነዚህ አካባቢዎች ከፍተኛ ሙቀት ሲኖራቸው የተስተካከለ የዝናብ ሥርጭት የላቸውም፡፡ በተጨማሪም ውኃና ለም አፈር የመሳሰሉ የተፈጥሮ ሀብቶች እጥረትም ይታይባቸዋል፡፡ እነዚህ አካባቢዎች ለአጭር ጊዜ ብቻ ዘንቦ በሚያባራ መለስተኛ ዝናብ ሊበቅሉ የሚችሉ ሣርና እጽዋት ስለሚኖራቸው ለከብት እርባታ እንጂ ለእርሻ ሥራ አይሆኑም፡፡ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በዝቅተኛ ሥፍራዎች የተሞላ ነው፡፡ የአካባቢው ሕዝብ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴም በአመዛኙ በከብት እርባታ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በዝቅተኛና በከፍተኛ አካባቢዎች የሚኖሩ ሕዝቦች የተለያየ አለባበስ አላቸው፡፡ ከፍተኛ አካባቢዎች ቅዝቃዜ ስላላቸው ሰዎች ሙቀት ሰጭ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ ዝቅተኛ አካባቢዎች ደግሞ ከፍተኛ ሙቀት ስላላቸው ገላን ለመሸፈን ያህል ቀለል ያለ ልብስ ይለበሳል፡፡ የአካባቢው የቤት አሠራርም ሙቀትን

ለመከላከል በሚያስችል መልኩ ይገነባል፡፡ በከፍተኛና ዝቅተኛ አካባቢዎች የሚበቅሉ ሰብሎችና የሚረቡ እንስሳት የተለያዩ በመሆናቸው ሁለቱ አካባቢዎች የተለያየ አመጋገብ ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ በከፍተኛና ዝቅተኛ አካባቢ ሕዝቦች መካከል የባህል ልዩነት ይታያል፡፡ ባህል ምንድን ነው?

ባህል የአንድ ሕዝብ የአኗኗር ዘይቤ ነው፡፡ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴን ጨምሮ የቤት አሠራር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ የሐዘንና የደስታ አገላለጽ ሁኔታዎችና የሙዚቃ፣ መሣሪያዎች በአጠቃላይ የሕዝብ ባህል እና የማንነት መገለጫዎች ይባላሉ፡፡

## ◈የሕዝብ አሰፋፈር ሁኔታ በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ጠረፋማ አካባቢዎች በዝቅተኛ ሥፍራዎች የተሸፈኑ ናቸው፡፡ በዚህ የተነሣ የሕዝቡ አሰፋፈር የተበታተነ ነው፡፡ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴም በከብት እርባታ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የመካከለኛው የኢትዮጵያ መሬት በአምባ ምድሮችና በከፍተኛ አካባቢዎች የተሸፈነ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ ብዙ ሕዝብ ለጤና ለእርሻ፣ ለከብት እርባታና ለደኅንነትም ምቹ በሆነ ሥፍራ ተከማችቶ ይኖራል፡፡ ስለዚህም በአምባ ምድሮች የሕዝቡ አሰፋፈር የተጠጋጋ ይሆናል፡፡

በከፍተኛም ሆነ በዝቅተኛ አካባቢዎች ሁለት ዓይነት ማኅበረሰብ ሊኖር ይችላል፡፡ እነርሱም የከተማና የገጠር ሕዝብ ናቸው፡፡



ምስል 1.19 የከተማ አካባቢ የሕዝብ አሰፋፈር

ይህን ምስል ከምስል 1.17 ጋር አነጻጽሩት የከተማና የገጠር ሕዝብ አሰፋፈር ልዩነቶችን ያመለክታሉ፡፡

### 1. የገጠር ሕዝብ አሰፋፈር

ይህ ዓይነቱ የሕዝብ አሰፋፈር ሥርዓት በግብርና ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የሕዝቦቹ አሰፋፈር ሁኔታ የተጠጋጋ፣ የተበታተነ ወይም የተራራቀ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡

በገጠራቱ ኢትዮጵያ በርካታ መንደሮችን እናስተውላለን፡፡ እነዚህ መንደሮች የተቀራረቡ ወይም የተራራቁ የሳር ክዳን ያላቸው ጎጆ ቤቶች ናቸው፡፡ (ምስል 1.17 ና 1.18 ተመልከቱ)፡፡ የገጠር ሕዝብ አሠፋፈሮች ጊዚያዊና ቋሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ጊዜያዊ የገጠር አሰፋፈር የሚተገበረው ከቦታ ወደ ቦታ በሚዘዋወሩ አርብቶ አደሮች ነው፡፡

አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ አርብቶ አደሮች በአንድ አካባቢ ለተወሰነ ጊዜ ይቆዩና ወደ ሌላ አካባቢ ይጓዛሉ:: የእንቅስቃሴዎቻቸው መንስኤዎች ምቹ ያልሆነ አየር ንብረት፣ የተፈጥሮ ሀብት (የግጦሽ ሥፍራና የውኃ) እጦት ናቸው:: በሌላ መልኩ በአንድ ሥፍራ በቋሚነት የሚታይ የሕዝብ አሰፋፈር በዘላቂነት የሚተገበሩ የግብርና ሥራዎች በአካባቢው መኖራቸውን ያመለክታል:: በዚህ ዓይነቱ አሰፋፈር ሰዎች በዘላቂነት ላልተወሰነ ጊዜ በአንድ አካባቢ ይኖራሉ:: ሰፋሪዎቹ በአካባቢው መሬትና ልዩ ልዩ ንብረቶች ይኖሯቸዋል::

## 2. የከተማ ሕዝብ አሰፋፈር

የከተማ አሰፋፈሮች ግብርና ነክ ያልሆኑ ምጣኔ ሀብታዊ ተግባራት ውጤት ናቸው:: እነዚህ ተግባራት ንግድን፣ ፀጉር ማስተካከልን፣ ፀጉር መሥራትን፣ የእንጨትና የብረት ሥራ እንዲሁም ልዩ ልዩ አስተዳደራዊ ሥራዎች ማከናወንን ያጠቃልላሉ:: በከተማዎች አካባቢ እንደ ትምህርት ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ ሆስፒታሎች፣ ፍርድ ቤቶች የመሳሰሉ ማኅበራዊ ተቋማት ይገኛሉ:: እነዚህ ተቋማት ለከተማው ኗሪ በቅርበት አገልግሎት ይሰጡታል:: በገጠር ግን ይህ ሁኔታ አይኖርም:: በከተማ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ በንግድና በኢንዱስትሪ ላይ የተመሠረተ ነው:: የገጠሩ ግን በእርሻና ከብት እርባታ ላይ የተመሠረተ ነው:: በተጨማሪም የከተማ ሕዝብ የቤት አሰራር፣ የአኗኗር ዘይቤው የእርስ በርስ ግንኙቱ ከገጠሩ ይለያል:: በዚህ የተነሣ በሁለቱ ማኅበረሰብ መካከል የባህል ልዩነት ይታያል::

### የክለሳ ጥያቄዎች 1.44

**ክንውን ለ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- የዝቅተኛና የከፍተኛ አካባቢ ሕዝቦች የኑሮ ሁኔታ መለያየት ዋነኛ ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ግለጹ::
- በኢትዮጵያ በከተማና በገጠር ነዋሪዎች መካከል ያለውን የአኗኗር ሥርዓት ልዩነት አነጻጽሩ::
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዓበይት የሕዝብ መተዳደሪያ እንቅስቃሴዎችን ጥቀሱ::
- የሕዝቦች አሰፋፈርና የኑሮ ሁኔታ ከቦታ ቦታ ለምን ይለያያል?
- ባህሎች ከቦታ ቦታ ለምን ይለያያሉ?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- ከሚከተሉት ሕዝቦች ከሠፈሩባቸው አካባቢዎች አንዱን በመምረጥ ከዚህ በታች በተሰጠው መመሪያ መሠረት ጥናት አካሂዱ

  - በከፍተኛ ሥፍራ የሚገኝ ገጠር
  - በዝቅተኛ ሥፍራ የሚገኝ ገጠር
  - በከፍተኛ ሥፍራ የሚገኝ ከተማ
  - በዝቅተኛ ሥፍራ የሚገኝ ከተማ

***መመሪያ***

- መረጃዎችን ከሚከተሉት የተከረተ ነጥቦች አኳያ አሰባስቡ::
  - በአካባቢያችሁ የሚበቅሉ ዋና ዋና ሰብሎችን በተመለከተ
  - አርብቶ አደሮች ስለሚያረቡአቸው እንስሳት በተመለከተ
  - ለንግድ የሚውል ዋነኛ የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የእንስሳት እርባታ ውጤቶች በተመለከተ
  - ለቤት ግንባታ የሚውሉ ቁሳቁስን በተመለከተ
- በአካባቢያችሁ የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሃይማኖቶችን በተመለከተ መረጃ በማሰባሰብ ለክፍል ውይይት የሚሆን ዘገባ አጠናቅሩ::

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

***ቅሪተ ቁስ፡-*** ከዘመናት በፊት በተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሠራሽ ምክንያት ተቀብረው የነበሩና በቁፋሮ የወጡ የተለያዩ መሣሪያዎችና የመገልገያ ቁሳቁሶች።

***ቅሪተ አካል፡-*** ከዘመናት በፊት ሞተው ወይም በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ የተቀበሩና በቁፋሮ የሚወጡ የእንስሳትና ተክሎች ቀሪ አካል።

***ባህል፡-*** የአንድ ሕዝብ የአመጋገብ፣ የአለባበስና የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴና አጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤ መገለጫ።

***አንፃራዊ መገኛ፡-*** በአካባቢ ከሚገኙ ተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሠራሽ ነገሮች ጋር በማነፃፀር የሚገለጽ የአንድ ነገር መገኛ።

***ከተማ፡-*** ከግብርና በስተቀር በሌሎች ሙያዎች የሚተዳደሩ በርካታ ሰዎች በተጠጋጉ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩበት፣ ድርጅቶችና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚገኙበት ቦታ፣ ሰፈራ፣ አካባቢ።

***ገጠር፡-*** ከከተማ ውጭ የሆነ ቦታ፣ ባላገር።

***የቅሪተ አካል መገኛ ሥፍራ፡-*** ጥንታዊ ቅሪተ አካላት ተቀብረው የሚገኙበት ወይም ተቆፍረው የሚወጡበት ሥፍራዎች ናቸው።

# ማጠቃለያ

- የአፍሪካ ቀንድ በአህጉሩ ምሥራቃዊ ጫፍ የሚገኝ ክልል ነው፡፡ በሰሜን ምሥራቅ ከኤደን ባሕረ ሰላጤና ቀይ ባሕር፣ በደቡብ ምሥራቅ ደግሞ ከሕንድ ውቅያኖስ ጋር ይዋሰናል፡፡ ክልሉ አራት አገሮች አሉት፡፡ እነርሱም ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ፣ ኤርትራና ሶማሊያ ናቸው፡፡
- የአፍሪካ ቀንድ የጥንታዊ ሰው መገኛ ሥፍራ ነው፡፡ ለዚህ ማረጋገጫው ከኢትዮጵያና ከኬንያ በቁፋሮ የተገኙ የጥንታዊ ሰው ቅሪተ አካላት ናቸው፡፡
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በርካታ ጥንታዊ መንግሥታት ነበሩ፡፡ ዋናዋናዎቹ ፑንት፣ ዳኣማት፣ አክሱም፣ ዛግዌ፣ የሙስሊም ሱልጣኔት፣ ዳሞት፣ ወላይታ፣ ኢናርያ የመሳሰሉ ናቸው፡፡ ለየት ያለ አስተዳደር የነበራቸው እንደ ኦሮሞ፣ ሲዳማና ኮንሶ የመሳሰሉ ሕዝቦች ናቸው፡፡
- ቀደምት የኢትዮጵያ መንግሥታት ሕዝቦች በርካታ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ስኬቶች አሉአቸው፡፡ ብዙዎቹ ከውጭው ዓለም ጋር የንግድ ትስስር ነበራቸው፡፡ የራሳቸው መሪዎችም ነበራቸው፡፡ መሪዎቹ ንጉሥ የሚባሉና ለየት ያለ ማዕረግ የነበራቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ የዳኣማት ነገሥታት ሙካሪብ የሚል ማዕረግ ነበራቸው፡፡ እነዚህ መንግሥታት አብያተ ክርስቲያንን መስጊዶችንና ቤተመንግሥታትን ገንብተዋል፡፡
- የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአንድ መንግሥት ሥር የተጠቃለሉት በ19ኛ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ነበር፡፡ ሌሎች የአፍሪካ ሕዝቦች በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር የወደቁ ሲሆን ኢትዮጵያ ግን ነፃነትዋን ጠብቃ የኖረች ብቸኛ አገር ናት፡፡
- የሕዝብ አሰፋፈር ከቦታ ወደ ቦታ ይለያያል፡፡ በከፍተኛ ቦታዎች የተጠጋጋ አሰፋፈር ሲታይ በዝቅተኛ አካባቢዎች ደግሞ የተበታተነ አሰፋፈር ይታያል፡፡ በሁለቱ አካባቢዎች መካከል የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ፣ የአመጋገብና የአለባበስ ልዩነትም ይታያል፡፡
- የአሰፋፈር ልዩነት አብዛኛውን ጊዜ የሚከሰተው እንደ አየር ንብረት፣ የተፈጥሮ ሀብት መኖርና የመከላከያ ብቃት በመሳሰሉ ምክንያቶች ነው፡፡ በገጠር አካባቢና በከተሞች አካባቢ የተለያየ ባህል ሊስፋፋ ይችላል፡፡ ባህል በአጠቃላይ የአንድ ማኅበረሰብ የአመጋገብ፣ የአለባበስና የአኗኗር ዘይቤ ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# የክለሳ ጥያቄዎች

## ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ::

1. ኬንያ ከአፍሪካ ቀንድ በስተምዕራብ ትገኛለች::
2. ከአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ኢትዮጵያ በስፋት ትልቋ ናት::
3. አክሱም በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ቀደምት መንግሥት ነበረች::
4. የዛግዌ መንግሥት በውቅር አብያተ ክርስቲያን እጅግ የታወቀ ነው::
5. ከፋ ጥንታዊ ዳሞትን የተካ መንግሥት ነበር::

## ለ. በ «ለ»ሥር የቀረቡትን መግለጫዎች «ሀ» ሥር ከቀረቡት ስያሜዎች ጋር አዛምዱ::

| | ሀ | ለ |
|---|---|---|
| ________ | 1. ሉዋ | ሀ. የመገበያያ ገንዘብ |
| ________ | 2. ገጠር | ለ. የግብርና ምጣኔ ሀብት |
| ________ | 3. እቴጌ ጣይቱ | ሐ. የወላይታ ነገሥታት ማዕረግ |
| ________ | 4. ታቶ | መ. የኢንዱስትሪ ምጣኔ ሀብት |
| ________ | 5. ሱልጣኔቶች | ሠ. የመጀመሪያው ዘመናዊ ሆቴል |
| ________ | 6. ካዎ | ረ. የኦሮሞ የአስተዳደር ሥርዓት |
| ________ | 7. ገዳ | ሰ. የሙስሊም ገዥዎች የወል ስም |
| | | ሸ. የከፊቾ ነገሥታት ማዕረግ |
| | | ቀ. የዳኣማት ገዥ |
| | | በ. የመጀመሪያው ሆስፒታል |
| | | ተ. የሲዳማ የአስተዳደር ሥርዓት |

## ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኞዎቹን መልሶች በመምረጥ ፊደላቱን በተተዉት ክፍት ቦታዎች ላይ አስፍሩ::

__________1. በአፍሪካ ቀንድ በስፋት ትንሿ ሀገር:-

ሀ. ሶማሊያ ለ. ኤርትራ ሐ. ኢትዮጵያ መ. ጅቡቲ

__________2. የጥንታዊ ሰው የቅርብ ጊዜ ቅሪተ አካል የትኛው ነው?

ሀ. ሰላም ለ. ኢዳልቱ ሐ. አርዲ መ. ሉሲ

__________3. በኢትዮጵያ ጠንካራ የሙስሊም ሱልጣኔት የነበረው:-

ሀ. ኢፋት ለ. ደዋሮ ሐ. ባሊ መ. ሐዲያ

_____ 4. የአፍሪካ ቀንድ አገሮችን በሙሉ በግዛቱ ሥር አጠቃሎ የነበረው መንግሥት የቱ ነው?
ሀ. ዳሞት ለ. ዳሜት ሐ.ፑንት መ. ዛግዌ

_____ 5. ከ18ኛው ምዕተ ዓመት በኋላ ለእስልምና መስፋፋት እንደ ዋነኛ መተላለፊያ የነበረው፦
ሀ. ዘይላ ለ. በርበራ ሐ. አዱሊስ መ. ዳህላክ

_____ 6. ጀጎል በመባል የሚታወቀው የግንብ አጥር ዙሪያውን የተገነባለት ከተማ፦
ሀ. ጎንደር ለ. አክሱም ሐ. ሰቃ መ. ሐረር

_____ 7. በ18ኛው ክፍለ ዘመን የሲሙ ኦሮሞዎች በቁጥጥራቸው ሥር አውለውት የነበረው የመካከለኛው ዘመን መንግሥት፦
ሀ. ዳሞት ለ. ኢናርያ ሐ. ባሊ መ. አዳል

_____ 8. ትግሬ በመባል የሚታወቀው ሥርወ መንግሥት የነበረው መንግሥት የቱ ነበር?
ሀ. ወላይታ ለ. ከፋ ሐ. ጌራ መ. ጎማ

_____ 9. በግብርና የእርከን ሥራን ተግባራዊ በማድረግ የሚታወቅ ሕዝብ፦
ሀ. ቡርጂ ለ. ኮንሶ ሐ.ጌዴኦ መ. ሲዳማ

_____ 10. ከሚከተሉት መካከል በወለጋ አካባቢ ተመሥርቶ የነበረው የኦሮሞ መንግሥት የትኛው ነው?
ሀ. ሊሙ ኢናርያ ለ. ጅማ ሐ. ሌቃ ነቀምቴ መ. ጌራ

## መ. የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በተስማሚው ቃላት ወይም ሐረጋት አሟሉ።

1. ለሕዝብ አሰፋፈር መለያየት ዋና ዋና ምክንያቶች _____, _____ እና _____ ናቸው።
2. የሰላም ቅሪት አካል የተገኘው _____ ከተሰኘ ሥፍራ ነው።
3. በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው ባንክ _____ ይባላል።
4. ከታሪክ አንፃር በአሥራ ዘጠነኛና በሀያኛው ክፍለ ዘመናት በኢትዮጵያ የተከናወኑ ዐበይት ተግባራት _____ _____, _____ እና _____ ናቸው።

## ሠ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶች ስጡ

1. ሙካሪብ ምንድነው?
2. በአሥራ ዘጠነኛና በሀያኛው ክፍለ ዘመናት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ ዘመናዊ ተቋማት ሦስቱን ተናገሩ።
3. የአድዋ ድል ፋይዳዎችን ግለጹ።
4. የሚከተሉትን ሰዎች ለዩ?
   ሀ. ኢሚር አብዱላሂ
   ለ. ኢሚር ኑር ሙጃሂድ
   ሐ. ኢማም አህመድ
   መ. ኡመር ወላስማ
   ሠ. ጦና
   ረ. ጋኪ ሼሬቾ
   ሰ. ኢሚር አሊ ኢብን ዳውድ
5. እስልምና ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደተስፋፋ ግለጹ።
6. የቅሪተ አካላት መገኛ ሥፍራዎች በኢትዮጵያ በየትኛው አካባቢ ይገኛሉ?
7. የኢትዮጵያን ቅርሶች እንዴት ከጥፋት መጠበቅ ይቻላል?

## ረ. የቡድን ሥራ

- የከፍተኛና የዝቅተኛ አካባቢዎች አሰፋፈርን በመለየት፣
  - በምጣኔ ሀብት ያላቸውን ልዩነቶች፣
  - የሕዝብ አሰፋፈር ሥርጭታቸውን፣
- በገጠርና በከተማ የሚኖሩ ሰዎች ያላቸውን የባህል ልዩነት በዘገባ አቅርቡ።

## ፍተሻ

*የምታውቋቸውን ክንውኖች በመለየት በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን (✓) ምልክት አኑሩ፡፡*

1. የአፍሪካ ቀንድ መገኛን እገልፃለሁ፡፡ ☐
2. ሰላጤ መገኛን (ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ምሥራቅ) በመጠቀም የአፍሪካ ቀንድ መገኛን እገልፃለሁ፡፡ ☐
3. በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ሀገራት ስምን እጠቅሳለሁ፡፡ ☐
4. የአፍሪካን ካርታ በመጠቀም የኢትዮጵያን አንፃራዊ መገኛ አሳያለሁ፡፡ ☐
5. ሰላጤ(Cardinal) መገኛን (ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ) አቅጣጫዎችን በመጠቀም የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ዋና ዋና ከተሞችን እገልፃለሁ፡፡ ☐
6. በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙትን ዋና ዋና የቅሪተ አካላትና ቅሪተ ቁስ መገኛዎችን እለያለሁ፡፡ ☐
7. የቅሪተ አካላት ግኝቶችን ቅደም ተከተልና ጥቅማቸውን እናገራለሁ፡፡ ☐
8. በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋና ሀይማኖቶችን አመጣጥና ሽፋን እገልፃለሁ፡፡ ☐
9. በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ያለው የሃይማኖት መቻቻል የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው መሆኑን በመገንዘብ አድናቆቴን እገልፃለሁ፡፡ ☐
10. ኢትዮጵያ የብዙ እምነት ተከታይ ሀገር መሆኗን በመገንዘብ እገልፃለሁ፡፡ ☐
11. ለጥንታዊ የኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ መንግሥታት ያለኝን አድናቆት እገልጻለሁ፡፡ ☐
12. ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥታት ታሪካዊና ፓለቲካዊ ክንዋኔዎች እለያለሁ፡፡ ☐
13. የኢትዮጵያውያን ልበ ሙሉነትና አንድነት ለአድዋ ድል የነበረውን ጠቀሜታ አብራራለሁ፡፡ ☐
14. በኢትዮጵያ ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ መጀመር ስላበረከተው አስተዋፅኦ አስረዳለሁ፡፡ ☐
15. በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የሕዝብ አሰፋፈር ልዩነት እንዲፈጠር ጉልህ ሚና ያላቸውን ምክንያቶች እጠቅሳለሁ፡፡ ☐
16. በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሕዝብ አሰፋፈር ከአኗኗር ዘይቤ ጋር ያለውን ግንኙነት አብራራለሁ፡፡ ☐
17. በኢትዮጵያ በከተማና በገጠር፣ በከፍተኛና ዝቅተኛ ሥፍራዎች በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል ያለውን የባህልና የአኗኗር ዘይቤ ተመሳሳይነትና ልዩነት እገልፃለሁ፡፡ ☐

# ምዕራፍ ሁለት

# መሬትና አካባቢዋ

*ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች*

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- በትምህርት ቤታችሁ ዙሪያ ያሉትን ነገሮች የሚያሳይ ካርታ ደረጃ በደረጃ ታዘጋጃላችሁ (ትስላላችሁ)፡፡
- የመሬት መሽከርከር የሚያመጣውን ውጤት (ለውጥ) ታብራራላችሁ፡፡

## 2.1 መገኛችን

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የካርታን ጠቀሜታ ታብራራላችሁ፡፡
- የንድፍ ካርታ እንዴት እንደሚዘጋጅና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ትገልጻላችሁ፡፡
- የትምህርት ቤታችሁን መገኛ የሚያሳይ ንድፍ ካርታ ታዘጋጃላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ካርታ
- መስፈርት
- ንድፍ ካርታ
- አቅጣጫ

### ◈ አቅጣጫንና መገኛን ለማሳየት ንድፍ ካርታ መጠቀም

- መገኛ ምንድን ነው?
- የመንደራችሁን፣ የከተማችሁን ወይም የክፍለ - ከተማችሁን ወይም የክልላችሁን መገኛ ሥፍራ ማብራራት ትችላላችሁ?
- ታዋቂ ነገሮችን መሠረት በማድረግ የትምህርት ቤታችሁን መገኛ ሥፍራ ተናገሩ፡፡
- ካርታ በመጠቀም መገኛን እንዴት ማሳየት ትችላላችሁ?
- ንድፍ ካርታ ከካርታ የሚለየው በምንድን ነው?

በምዕራፍ አንድ የአፍሪካ ቀንድን አንፃራዊ መገኛ ለይታችሁ አውቃችኋል፡፡ መገኛ ማለት አንድ ነገር ወይም ግለሰብ ከሌሎች ነገሮች አንጻር የሚገኝበት አቅጣጫ ነው፡፡ አንድ ነገር የሚገኝበት ሥፍራ ማለትም ይሆናል፡፡

ካርታ በመሬት ላይ የሚገኙ ነገሮችን ዝርግ በሆነ ወረቀት ላይ በመስፈርት አማካይነት ተመጥነው የሚታዩበት ሥዕላዊ መግለጫ ነው፡፡ ካርታ በሠለጠኑ ሰዎች ዘመናዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም ይዘጋጃል፡፡ ካርታ መገኛንና አቅጣጫን ለማሳየት ይረዳል፡፡

መገኛን በምድር ላይ ወይም በካርታ ወይም በንድፍ ካርታ ላይ ማሳየት ይቻላል፡፡ መገኛን በካርታ ወይም በንድፍ ካርታ ላይ ለማሳየት የፈለግን እንደሆነ በቅድሚያ ለማሳየት የፈለግነውን ነገር ወይም ነገሮች አቅጣጫን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ አንድን ነገር በካርታ ወይም በንድፍ ካርታ ላይ ለማሳየት የፈለግን እንደሆነ የዚያን ነገር ግዝፈት መስፈርት ተጠቅመን መቀነስ አለብን፡፡ ስለዚህ መስፈርት /scale/ በመለኪያ አማካኝነት የሚታወቅ የካርታ ላይ ርቀት እና የምድር ላይ ርቀት ንጽጽር ወይም ጥመርታ (ratio) ነው፡፡


መስፈርት፡- 1 ሴ.ሜ ለ 1 ኪ.ሜ

ይህ መስፈርት አንድ ሴንቲ ሜትር ለአንድ ኪሎ ሜትር ተብሎ ይነበባል፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? በካርታ ላይ የተመለከተው አንድ ሴንቲ ሜትር ርቀት በምድር ላይ የአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ይወክላል ማለት ነው፡፡

### አቅጣጫ ምንድን ነው?

አንድ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ግለሰብ ወይም ነገር የያዘው የፍሰት መስመር አቅጣጫ ይባላል፡፡ አንድ ግለሰብ ወይም ነገር ፊቱ የዞረበት ነጥብ ወይም ትይዩ አቅጣጫ ማለት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ምስል 2.1 ተመልከቱ፡፡ በካርታ ወይም በንድፍ ካርታ ላይ አቅጣጫ ለማሳየት በምስል 2.1 በተመለከተው መልክ ወደ ሰሜን አመልካች ቀስት ይሳላል፡፡

- በምሥል 2.1 የተመለከቱትን የሰውና የመኪና እንቅስቃሴ አቅጣጫ ተናገሩ፡፡
- ሰውየው ከመኪናው አንጻር በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?





*ምስል 2.1 በእንቅስቃሴ ላይ ያለን ነገር አቅጣጫ መለየት*

## ◈ ተራ ንድፍ ካርታ ማዘጋጀት

- **ንድፍ ካርታ ምንድን ነው?**

ንድፍ ካርታ መስፈርት ተጠቅሞ በተሰባሰበ መረጃ አማካኝነት የተሣለ የአንድ ውሱን ሥፍራ ንድፍ (plan) ነው። ንድፍ ካርታ ያለ መሣሪያ በእጅ የሚሣል ነው። በፎቶ ኮፒ ከተራባ ካርታ በእጅት የተሻለ ነው። ምክንያቱም ለማሳየት የተፈለጉ ነገሮችን ብቻ በዝርዝር ማስፈር ስለሚያስችል ነው። ንድፍ ካርታ በእርሳስ ተሥሎ በስክሪኖቶ በጥንቃቄ የተብራራ መሆን አለበት። በንድፍ ካርታ ላይ አቅጣጫና መስፈርት የመሳሰሉ መረጃዎች መቅረብ አለባቸው። እንደዚሁም ለንድፍ ካርታው ተስማሚ የሆነ ርዕስ መስጠትና የንድፍ ካርታው ጠርዝ በዝርግ ወረቀት መሐል ላይ ተከቦ መታየት አለበት። እንደ አስፈላጊነቱም ቅልመቶችንና የጎዳግ መረጃዎችን መጨመር ይቻላል።
ከዚያም በሁሉም የወረቀታችን ጐን ላይ የንድፉን መጠን ለመወሰን የሚያስችል ጠርዝ እናዘጋጃለን። የንድፍ ወረቀት አንዴ ከተወሰነ የንድፍ ካርታውን ቁመትና ስፋት ማስፈር ቀላል ነው። ንድፍ ካርታ የምናዘጋጅበትን ዝርግ ወረቀት መጠኑን መወሰን አስፈላጊ የሚሆነው ንድፍ ካርታው ቀላል፣ ተነባቢ፣ ጠቃሚና የተወሰነ መጠን ያለው ለማድረግ ሲባል ነው። የመማሪያ ክፍላችሁ ንድፍ ካርታ በር እና መስኮትን በሁለት ነጥቦች መካከል በሚተው ክፍተት ማሳየት ይቻላል። በምስል 2.2 የቀረበውን ንድፍ ካርታ ተመልከቱ። የተወሰነ መጠን ይዞ በወረቀቱ መሐል ላይ በግልፅ ተቀምጦ ይታያል።




*ምስል 2.2 የመማሪያ ክፍል ንድፍ ካርታ*

**የክለሳ ጥያቄዎች 2.1**

**ክንውን**

***ሀ. በዕውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

**ምስል 2.2 በጥንቃቄ ከተመለከታችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ስጡ።**

- በንድፍ ካርታ ላይ መስፈር የሚገባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
- ንድፍ ካርታ የሚሳልበትን የወረቀት መጠን ግለጹ።
- የአንድን ንድፍ ካርታ ቁመትና ስፋት መወሰን የሚቻለው እንዴት ነው?
- አቅጣጫ ምንድን ነው?

*ለ. የሚሠሩ ተግባራት*

I.

- የመማሪያ ክፍላችሁን ጐንና የትይዩ ቋሚ መስመሮችን በመለካት መስፈርቱን የጠበቀ ክፍል ሣሉ፡፡
- የክፍሉን በርና መስኮቶች ተገቢ በሆነ ሥፍራቸው ላይ አኑሩአቸው፡፡
- የመማሪያ ክፍሉን ዴስኮች መኖር በሚገባቸው ሥፍራ ላይ በሥዕል አመልክቱ፡፡
- የሰሜን አቅጣጫ አመላካች የሆነ ቀስት ሣሉ፡፡

II.

- ስለ መንደራችሁ መረጃ አሰባስቡ፡፡
- የመንደራችሁን ንድፍ ካርታ ሣሉ፡፡
- በንድፍ ካርታው ላይ መንገዶች፣ ወንዞችና ዋና ዋና ሕንጻዎችን አስፈሩበት፡፡

## 2.2 የመሬት ቅርጽ፣ እንቅስቃሴዋና ውጤቶቹ

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ➢ የመሬትን ቅርፅና እንቅስቃሴ አይነቶችን ትለያላችሁ
- ➢ የመሬት እንቅስቃሴ የሚያመጣውን ለውጥ(ውጤት) ታብራራላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ቅርጽ
- ዞሪት
- ሽክርክሪት
- ወቅት
- ምሕዋር
- ንፍቀ ክበብ

### ◈ የመሬት ቅርጽ

- ቅርጽ ምንድን ነው?
- በአካባቢያችሁ የሚታዩ የተለያዩ ቅርጾችን ዘርዝሩ፡፡
- የመሬት ቅርጽ ምን ይመስላል?
- የመሬትን ቅርጽ ሊያሳይ የሚችል ነገር መጥቀስ ትችላላችሁን?

የመሬት ቅርጽ ለዘመናት የተረጋገጠ ምላሽ ሳያገኝ የቆየ ጉዳይ ነበር፡፡ ነገር ግን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከአንደኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ መሬት የሉል ቅርጽ (ሞላላ) እንዳላት የሚገልጸው ሀሳብ ተቀባይነት አግኝቶአል፡፡ ከዚህ አንጻር ሰዎች ለሁለት ሺ ዓመታት ያህል ክብ ቅርጽ ባላት መሬት ላይ እየኖሩ መሆናቸውን ያውቁ ነበር፡፡ የምንኖርባት መሬት በሕዋ ውስጥ ከሚገኙ ዓለማት አንዷ ናት፡፡ መሬት ፍጹም ሉል ክብ አይደለችም፡፡ ሞላላ ሉል መሳይ ቅርጽ አላት፡፡ ሉል የመሬትን ቅርጽ የሚወክል ጥሩ ሞዴል ነው፡፡ በምስል 2.3 የቀረበው ሉል እንደሚያሳየን መሬት ሞላላ ሉል መሳይ ቅርጽ አላት፡፡



*ምስል 2.3 የመሬትን ቅርጽ የሚወክል ሉል*

1. በሥዕሉ የሚታየውን ሉል ተመልከቱ፡፡ ምን ዓይነት ቅርጽ አለው?
2. በሉሉ ላይ ተሥሎ የሚታየው ምንድን ነው?

**የክለሳ ጥያቄዎች 2.2**

**ክንውን ሀ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- በመሬት ቅርጽ እና በሉል መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
- የመሬትን ቅርጽ ለመረዳት ከማስቻል አንጻር ሉል ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?
- አንድን ነገር ወይም ገጽታ በሉል ላይ እንዴት ማሳየት ይቻላል?


***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- ለሥራ የሚያስፈልጋችሁን ሉል እና የእጅ ባትሪ አዘጋጁ፡፡ ከዚያም የእጅ ባትሪው ከምሥራቅ በኩል ወደ ሉሉ እንዲበራ ይደረግ፡፡ ከዚያም ሉሉን በዛቢያው ላይ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ባትሪው ወደሚበራበት አቅጣጫ አሽከርክሩት፡፡
  - መሬትን በሚወክለው ሉል በከፊል አካሉ ላይ የሚረጨው የባትሪ ብርሃን ምን ግንዛቤ ይሰጣችኋል?
  - ሉሉን በዛቢያው ላይ ወደ ባትሪው ብርሃን አቅጣጫ ስታሽከረክሩት ከሚታየው ብርሃን አንጻር በመሬት ላይ የሚፈራረቁት ቀንና ሌሊትን እንዴት ማስረዳት ትችላላችሁ?
- ሉል ማዘጋጀት ትችላላችሁን ወደ ትምህርት ቤታችሁ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል በመሄድ ሉል ለማዘጋጀት እንዴት እንደሚቻል ጠይቁና የራሳችሁን ሉል አዘጋጁ፡፡

## ◈ የመሬት ዛቢያ

- ዛቢያ ምንድን ነው?
- ስለ ዛቢያ ምን ግምት አላችሁ? ምን ይመስላል?
- በጠረጴዛ ላይ ሳንቲም በፍጥነት እንዲሽከረከር አድረጋችሁ ታውቃላችሁን? ምላሻችሁ አዎ ከሆነ እየተሽከረከረ ባለው ሳንቲም መሐል ላይ ምን ይታያችኋል? ሳንቲሟ መሐል ላይ ቋሚ ነገር ተገን አድርጋ የምትሽከረከር አይመስላችሁምን?

የመሬት ዛቢያ ከሰሜን ዋልታ እስከ ደቡብ ዋልታ በመሬት ውስጥ ለውስጥ የሚዘልቅ በሐሳብ የተሣለ መስመር ነው፡፡ መሬት የምትሽከረከረው በዚህ በሐሳብ በተሣለ ዛቢያ ላይ ነው (ምስል 2.4 ተመልከቱ)፡፡ በሥዕሉ ላይ እንደሚታየው የመሬት ዛቢያ ቀጥ ብሎ የሚታይ ቋሚ አይደለም፡፡ ይልቁንም ወደ አንድ ወገን ዘመም ብሎ ይታያል፡፡ ዝመቱ ያጋደለበት አንግል መጠን 23°30´ (23½°) ነው፡፡





*ምስል 2.4 የመሬት ዛቢያ*

## ◈ የመሬት እንቅስቃሴና ውጤት

- እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነው?
- መሬት እንዴት ትንቀሳቀሳለች?
- የመሬት እንቅስቃሴ ምን ዓይነት ውጤቶች ያስከትላል?

**እንቅስቃሴ ማለት በአንድ መስመር ላይ የተለያየ ሥፍራ ይዞ መታየት ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በመስመሩ ላይ በአግድም፣ በዓምድ ወይም ዘመም ብሎ በአንድ በተወሰነ አቅጣጫ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መታየት ማለት ነው፡፡**





*ምስል 2.5 የተለያዩ እንቅስቃሴዎችና ዛቢያዎቻቸው*

ምስል 2.5 እንደሚያመለክተው አንድ ሰው ወይም ነገር በያዘው ቦታ ላይ ሆኖ ወይም ቦታ እየለቀቀ ሲሽከረከር የራሱ የሽክርክሪት አቅጣጫ ይኖረዋል፡፡ ከዚህም በላይ ተሽከርካሪው ነገር አቅጣጫውን ጠብቆ የራሱ ዛቢያም ይኖረዋል፡፡ በሚሽከረከርበት ጊዜም በዛቢያ ላይ ይጠቀማል፡፡ በሥዕሉ ላይ እንደተመለከተው ተሽከርካሪዋ ሴት ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ስትሽከረከር ትታያለች፡፡ የመሬት ምስልን የሚያሳየው ሉል ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ መሽከርከሩ በቀስት ተመልክቷል፡፡ የግንድ ቁራጩ ደግሞ ከሰሜን አቅጣጫ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሲንካባለል ይታያል፡፡ እያንዳንዱ የሚሽከረከር ዓምዳዊ ወይንም አግድማዊ ዛቢያ አለው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም የሚሽከረከር ነገር በመሃሉ የሚያልፍ ዛቢያ አለው ማለት ነው፡፡

በሕዋ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ነገር ይንቀሳቀሳል፡፡ የማይንቀሳቀስ ምንም ዓይነት ነገር የለም፡፡ እንደዚሁም መኖሪያችን የሆነችው መሬትም እንቅስቃሴ ታደርጋለች፡፡ በተጨባጭ የሚታዩ እንቅስቃሴዎችዋ በዛቢያዋ ላይ የምታደርገው ሽክርክሪት እና በፀሐይ ዙሪያ የምታደርገው ዙሪት ነው፡፡ ተመሳሳይ በሆነ ወቅት ላይ የሚፈፀሙ እነዚህ ሁለት እንቅስቃሴዎች ለቀንና ሌሊት መከሰትና ለወቅቶች መፈራረቅ ወሳኝ ናቸው፡፡ መሬት አንድ የተወሰነ አቅጣጫና መስመር ተከትላ በፀሐይ ዙሪያ ያለ ማቋረጥ ትዞራለች፡፡ መሬት በፀሐይ ዙሪያ የምትዞርበት በሐሳብ የተሣለ መስመር ምሕዋር ይባላል፡፡ የምሕዋር ቅርጽ ሞላላ ክብ ነው፡፡ የመሬት ምሕዋር ቅርጽ ሞላላ በመሆኑ መሬት በፀሐይ ዙሪያ በምትዞርበት ወቅት በተለያዩ የምሕዋሩ አካባቢ ላይ ከፀሐይ የሚኖራት ርቀት የተለያየ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ መሬት ሁለት ዓይነት እንቅስቃሴዎች ታደርጋለች፡፡ እነርሱም ዙሪትና ሽክርክሪት ብለን የምንጠራቸው ናቸው፡፡ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ መሬት በራስዋ ዛቢያ አንድ ሙሉ እንቅስቃሴ ታጠናቅቃለች፡፡ ይህ እንቅስቃሴ የመሬት ሽክርክሪት(Rotation) ይባላል፡፡

በአንድ ዓመት ማለት በ365¼ ቀናት ደግሞ መሬት በፀሐይ ዙሪያ የምታደርገውን እንቅስቃሴ ታጠናቅቃለች፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ዙሪት (Revolution) ይባላል፡፡ ሁለቱ የመሬት እንቅስቃሴዎች በአንድ ተመሳሳይ ጊዜ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ መሬት በራስዋ ዛቢያ ላይ የምታደርገው እንቅስቃሴ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ይከናወናል፡፡ ይህም ማለት በሃያ አራት ሰዓት በዛቢያዋ ላይ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ አንድ ሙሉ ሽክርክሪት ታካሂዳለች (ምስል 2.6 ተመልከቱ)፡፡





*ምስል 2.6 የመሬት እንቅስቃሴ አቅጣጫ*

## ◈ የመሬት መሽከርከር የሚያስከትላቸው ውጤቶች

መሬት በዛቢያዋ ላይ ስትሽከረከር ሦስት ክስተቶች ይፈጠራሉ።
እነሱም፦ 1. የቀንና የሌሊት መፈራረቅ
2. ፀሐይ በመሬት ዙሪያ የምትንቀሳቀስ መስላ መታየት
3. የነፋስና የባሕር ሞገድ አቅጣጫ መቀየር ናቸው።

### 1. የቀንና የሌሊት መፈራረቅ

በቀንና ሌሊት መካከል ያለው ልዩነት ቀን ላይ ፀሐይ ከአድማስ በላይ ስትታይ ሌሊት ደግሞ ከአድማስ ባሻገር ትሰወራለች። የቀንና ሌሊት ርዝማኔ ከወቅት ወቅትና ከሥፍራ ሥፍራ የተለያየ ነው። የዚህ ልዩነት መንሥኤ የመሬት ዛቢያ የዘመመ (ያጋደለ) በመሆኑ ነው። የመሬት ዛቢያ ባይዘም ኖሮ የቀንና ሌሊት ርዝማኔ በየትኛውም የመሬት አካባቢ 12 ሰዓት ይሆን ነበር። ወቅቶችም አይከሰቱም ነበር (ምስል 2.7 ተመልከቱ)




*ምስል 2.7 ቀጥተኛ የመሬት ዛቢያ*

**ፀሐይ በመሬት ዙሪያ የምትንቀሳቀስ መስላ ትታያለች ስንል ፀሐይ ሥፍራዋን ለቃ በመሬት ዙሪያ አለመዞሯን መግለጻችን ነው።**

### 2. ፀሐይ በመሬት ዙሪያ የምትንቀሳቀስ መስላ መታየት

መሬት በራሷዛቢያ ላይ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ መሽከርከሯ ፀሐይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ በሰማይ ላይ የተንቀሳቀሰች መስላ እንድትታየን ያደርጋል። ይህ ግን በእርግጥ የሚካሄድ እንቅሳቃሴ ሳይሆን መሬት ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ በመሽከርከሯ የሚፈጠርና መስሎ የሚታየን ነው።

### 3. የነፋስና የባሕር ሞገድ አቅጣጫ መቀየር

ሞገድ በነፋስ ምክንያት የሚፈጠር የባህር መናወጥ ነው። የመሬት ሽክርክሮሽ ነፋስና የባሕር ሞገድ አቅጣጫ እንዲቀይሩ ያደርጋል።

## ◈ የመሬት ዙረት ውጤቶች

- መሬት በፀሐይ ዙሪያ መዞርዋ የሚከተሉትን ሁለት ውጤቶች ያስከትላል።
  ሀ) በቀንና ሌሊት ርዝማኔ መካከል ልዩነት መፈጠር።
  ለ) የወቅቶች መከሰትና መለያየት።

### ሀ. የቀንና ሌሊት ርዝመት መለያየት

- በሁሉም ሥፍራዎች የቀንና ሌሊት ርዝመት እኩል አይደለም። ይህ የሚሆነው የመሬት ዛቢያ ወደ አንድ አቅጣጫ ያጋደለ በመሆኑ ነው። የዛቢያው ዝመት ከቀጥተኛና ቋሚ መስመሩ ያለው ርቀት 23½° ነው። ይህ የመሬት ዛቢያ ዝመት ፀሐይ ከምድር ወገብ አንድ ጊዜ በስተሰሜን ሌላ ጊዜ ደግሞ

በስተደቡብ እየተንቀሳቀሰች ያለች መስላ እንድትታይ ያደርጋል፡፡ በቀናት መካከል ያለው የርዝመት ልዩነት በወቅቶች መግባት መውጣት የተነሳ የሚታይ ነው፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች 2.2**

**ክንውን ለ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***


- የመሬት ዛቢያ ምን እንደሆነ አብራሩ፡፡
- መሬት የምታካሂዳቸውን እንቅስቃሴዎች አስረዱ፡፡
- በጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ የመሬት ዑሪትና ሽክርክሪት ውጤቶችን ግለጹ፡፡
- የመሬትን ዑሪትና ሽክርክሪት በማወዳደርና በማነጻፀር አስረዱ፡፡

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- የመሬት ሞዴል አዘጋጁ፡፡ ከዚያም ቀጥተኛ እና ዘመም ያሉ ዛቢያዎችን ባዘጋጃችሁት የመሬት ሞዴል ላይ አሳዩ፡፡

## ለ. የወቅቶች መከሰትና መለያየት

**ወቅት በመሬት ዑሪት አማካይነት በአንድ ሥፍራ የሚታይ የሙቀት፣ የቅዝቃዜ፣ የዝናብና የአየር ግፊት መጠን እንዲሁም የቀንና የሌሊት ርዝመት ለውጥ የሚታይበት ጊዜ ነው፡፡ በመሬት ዑሪት አማካይነት አራት ወቅቶች ይፈጠራሉ፡፡ እነሱም ክረምት፣ መኸር፣ በጋና በልግ ናቸው፡፡ (ምስል 2.8 ተመልከቱ)፡፡**




*ምስል 2.8 የወቅቶች መፈራረቅ*

ወቅቶች በመሬት ዑሪት ምክንያት የሚፈጠሩ ክስተቶች ናቸው፡፡ የቀንና የሌሊት ርዝመት፣ የሙቀትና ቅዝቃዜ መጠን፣ የዝናብና የአየር ግፊት መጠን ከወቅት ወቅት ይለያያል፡፡ ለምሳሌ በክረምት ወቅት የቀኑ ርዝመት ከሌሊቱ ርዝመት ይበልጣል፡፡ የሙቀቱና የቅዝቃዜው እንዲሁም የዝናቡ መጠን ከበጋው ወቅት ይለያል፡፡ ስለዚህም እያንዳንዱ ወቅት የራሱ የሆኑ ባሕርያት አሉት፡፡ አራቱ ወቅቶች የሚከሰቱበትን ጊዜ ከምስል 2.8 ተመልከቱ፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች 2.2**

**ክንውን ሐ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- በሰሜን ንፍቀ ክበብ የክረምት ወቅት መሆኑን የሚያመለክተው ወር የትኛው ነው?
- በክረምትና በጋ ወቅቶች መሐከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- በትልቅ ዝርግ የሥዕል ወረቀት ላይ የመሬትን በፀሐይ ዙሪያ መዞርና የተለያዩ ወቅቶች መፈጠርን በመሣል አሳዩ።

## ◈ የመሬት 23½° ማጋደልና የወቅቶች መፈራረቅ

ለወቅቶች መፈጠር መንስኤው መሬት የምትሽከረከርበት ዛቢያ በፀሐይ ዙሪያ ከምትዞርበት ምሕዋር አንጻር ያዘመመ መሆኑ ነው። የመሬት ዝመት የሰሜን ዋልታ ለግማሽ ዓመት ወደ ፀሐይ አቅጣጫ ዘመም እንዲልና ለተቀረው ግማሽ ዓመት ደግሞ የደቡብ ዋልታ በተራው ወደ ፀሐይ እንዲያጋድል ያደርጋል። ወደ ፀሐይ ያጋደለው ንፍቀ ክበብ የፀሐይን ጨረር የበለጠ በማግኘቱ ረዥም ቀን ይኖረዋል። (ምስል 2.9 ተመልከቱ)።


የሰሜን ንፍቀ ክበብ በክረምት ወቅት ወደ ፀሐይ አቅጣጫ ያጋድላል። በዚህ ተመሳሳይ ወቅት የደቡብ ንፍቀ ክበብ ከፀሐይ ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ያጋድላል።



ወደ ፀሐይ አቅጣጫ የዞረው የመሬትን አካል ተመልከቱ። ከምልከታው የምትደርሱበት ድምዳሜ ምንድን ነው?

*ምስል 2.9 ክረምት በደቡብ ንፍቀ ክበብ*

**ንፍቀ - ክበብ፡- የመሬት ግማሽ ክፍል ማለት ነው። የምድር ወገብ መስመር መሬትን አግድም ሁለት እኩል ቦታ ስለሚከፍላት ሰሜናዊ ንፍቀ ክበብና ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ተብሎ ይጠራል። በተቃራኒው ከሰሜን ወደ ደቡብ ወይም ከደቡብ ወደ ሰሜን በተሰመረ የሀሳብ መስመር መሬት ሁለት እኩል ቦታ ተከፍላለች። ይህ መስመር ትልቁ ሜሪዲያን (prime meridian) ይባላል። ትልቁ ሜሪዲያን መሬትን በምሥራቃዊና በምዕራባዊ ንፍቀ ክበቦች ይከፍላታል።**




*ምስል 2.10 ምሥራቃዊና ምዕራባዊ ንፍቀ ክበብ*

## 2.3 የወቅቶች መፈራረቅ በእርሻና በከብት እርባታ ላይ ያለው ተጽእኖ

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

*ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦*

- ➢ የወቅቶች መፈራረቅ በገበሬዎችና በከብት አርቢዎች ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ላይ ያለውን ተጽእኖ ታስረዳላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- እርሻ
- ከብት እርባታ

### ◈ ወቅቶች በኢትዮጵያ

- በኢትዮጵያ የሚታዩ ወቅቶች መጠሪያ በአማርኛም ሆነ በሌላ የአካባቢያችሁ ቋንቋ ግለጹ፡፡
- በኢትዮጵያ ወቅቶች በሰዎች የአኗኗር ዘይቤ ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ ያሳድራሉ?
- በአካባቢያችሁ ገበሬዎች የእርሻ ሥራ የሚጀምሩት መቼ ነው?
- በአካባቢያችሁ ብዙ ጊዜ የውኃ እጥረት የሚታየው መቼ ነው?
- የውኃ እጥረቱ የሚፈጠረው በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

በሞቃታማ የሐሩር ክልል አካባቢዎች የሙቀት መጠን ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ የዓመቱ ወቅቶች የሚከፈሉት ከሙቀት መጠን በሚፈጠር ልዩነት በመነሳት ነው፡፡ ስለዚህ በሐሩር ክልል ሁለት ወቅቶች ብቻ

ይኖራሉ፡፡ እነርሱም እርጥብ ዝናባማ እና ደረቅ ወቅቶች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያም በበጋና በክረምት ወቅቶች መካከል ብዙም የሙቀት መጠን ልዩነት በማይታይባቸው ሥፍራዎች ተመሳሳይ አከፋፈል ይታያል፡፡ በኢትዮጵያ አራት ወቅቶች አሉ፡፡

**ሠንጠረዥ 2.1 የወቅቶች አከፋፈል በወራትና በንፍቀ ክበቦች ሲታይ**

| ሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ | | ደቡባዊ ንፍቀ-ክበብ | |
|---|---|---|---|
| ሰኔ<br>ሐምሌ<br>ነሐሴ | ክረምት - (Summer) | ሰኔ<br>ሐምሌ<br>ነሐሴ | በጋ (ሐጋይ) (winter) |
| መስከረም<br>ጥቅምት<br>ኅዳር | መኸር - (Autumn) (መፀው) | መስከረም<br>ጥቅምት<br>ኅዳር | በልግ (ጸደይ) (Spring) |
| ታኅሳስ<br>ጥር<br>የካቲት | በጋ - (Winter) (ሐጋይ) | ታኅሳስ<br>ጥር<br>የካቲት | ክረምት (Summer) |
| መጋቢት<br>ሚያዚያ<br>ግንቦት | በልግ - (Spring) (ጸደይ) | መጋቢት<br>ሚያዚያ<br>ግንቦት | መኸር (Autumn) |

ኢትዮጵያን በተመለከተ ክረምት እና በጋ የተገላቢጦሽ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ክረምት በኢትዮጵያ ዝናባማና ቀዝቃዛ ሲሆን በጋ ደግሞ ደረቅ ወቅት ነው፡፡

## ◈ የወቅቶች መፈራረቅ በእርሻ ሥራ ላይ ያለው አሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖ

- **በቆላማ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የትኛው የዝናብ ወቅት የበለጠ ጠቀሜታ አለው?**

በኢትዮጵያ ዓመቱ በአራት ወቅቶች ይከፋፈላል፡፡ ከአራቱ ወቅቶች ሦስቱ ርጥበት አላቸው፡፡ የክረምት ወቅት በአብዛኛው የኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢዎች ከፍተኛ ርጥበት አላቸው፡፡ በቆላማና በምሥራቁ ዝቅተኛ አካባቢዎች ማለትም በሰሜን ምሥራቅ አካባቢ የመኸርና የበልግ ወቅቶች ከፍተኛ ርጥበት አላቸው፡፡

በአምባ ምድሮችና በደጋ አካባቢ የሚገኙ የኢትዮጵያ አራሽ ገበሬዎች ኑሮ በክረምት ዝናብ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የክረምት ዝናብ ከሌሎቹ ወቅቶች የበለጠ ከፍተኛና እርጥበታማ ወቅት ነው፡፡ ገበሬዎች በርካታ ሰብሎችን የሚያመርቱት በክረምት ወቅት ሲሆን ይህ ወቅት በሰሜን ንፍቀ ክበብ ሌሎች አካባቢዎች ሰመር (Summer) የተሰኘው ነው፡፡ ወቅቶቹ የሚከሰቱባቸው ጊዜያት የተለያዩ ቢሆንም በመኸርና በበልግ የሚጥል አነስተኛ ዝናብ በጣም ወሳኝ የሚሆኑባቸው አካባቢዎች አሉ፡፡ ከመኸር ይልቅ የበልግ ወቅት የደጋና ቆላማ የሆኑ ሰፊ ሥፍራዎችን ይሸፍናል፡፡ ስለዚህ ከክረምት ቀጥሎ የበልግ ወቅት ለኢትዮጵያ ገበሬዎች ጠቃሚ ወቅት ነው፡፡ በዚህ ወቅት የሚፈጠር የዝናብ እጥረት የገበሬዎችንና የከብት አርቢዎችን የኑሮ መሠረት ሊያናጋ ይችላል፡፡

በአሁኑ ወቅት የወቅቶች የሙቀትና የርጥበት መጠን እየተዛባ ይታያል፡፡ ይህም የዝናብ ወቅት መዛባትን ያስከትላል፡፡ በዓለም ደረጃ የሙቀት መጠን መጨመርና በተለይም በተለያዩ ሥፍራዎች የተፈጥሮ አካባቢዎች መጎዳት ለዝናብ ወቅት መዛባት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡

## ◈ የወቅቶች መፈራረቅ በከብት እርባታ እንቅስቃሴ ላይ ያስው አሉታዊና አዎንቲዊ ተጽእና

- ከብት አርቢነት ማለት ምን ማለት ነው?
- በከብት አርቢዎች አካባቢ መሠረታዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በምን ላይ የተመሠረተ ነው?
- ከብት አርቢዎች በከብት እርባታ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ላይ እንዲመሠረቱ ያደረጋቸው ምንድን ነው?
- የከብት እርባታ እንቅስቃሴ በስፋት የሚታይባቸው አካባቢዎችን ዘርዝሩ፡፡

ኑሮአቸውን ከብት፣ በግ፣ ፍየልና ግመል በማርባት ላይ የመሠረቱ የማኅበረሰብ አባላት **ከብት አርቢ ማኅበረሰብ** በመባል ይጠራሉ፡፡ በምሥራቅ አፍሪካ በርካታ ከብት አርቢ ማኅበረሰቦች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ማኅበረሰቦች መካከል በምሥራቅ አፍሪካ ታዋቂው ማኅበረሰብ ማሣይ ይባላል ፡፡




ምስል 2.11 ከብት አርቢ

የከብት እርባታ ሥራ በስፋት የሚካሄደው በደረቅ ሣራማና ከፊል በረሃነት ባለባቸው ሥፍራዎች ነው፡፡ በዚህ አካባቢ የሚገኝ አፈር ለምነት የጎደለው በመሆኑ ለእርሻ ሥራ አይመችም፡፡ ነገር ግን በአካባቢው የሚበቅሉት እፅዋት ለከብት እርባታ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ይመቻል፡፡ ስለዚህም የከብት እርባታ በደረቅ ሣራማና ከፊል በረሃማ አካባቢዎች ተስፋፍቶ ይታያል፡፡



ምስል 2.12 የከብት አርቢዎች ልጅ ከከብት ጋር

ከከብት እርባታ የተለያዩ የሥጋና የወተት ተዋጽኦዎች እንዲሁም ቆዳና ሌጦ ይገኛል፡፡ ከብት አርቢዎች ብዙውን ጊዜ ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ሕይወታቸውን ይመራሉ፡፡ እንቅስቃሴያቸው ለእንስሶቻቸው አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በርካታ ከብት አርቢዎች ወቅቶችን በመከተል ሣርና ውኃ ፍለጋ ከሥፍራ ሥፍራ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በኢትዮጵያ ከብት አርቢዎች በስፋት የሚገኙት በደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅ እና በሰሜን ምሥራቅ የአገሪቱ አካባቢዎች ነው፡፡




ምስል 2.13 የከብት አርቢዎች መገኛ በኢትዮጵያ

የአፈሩ ዓይነት ምርት ሊሰጥ በሚችልባቸው አንዳንድ ሥፍራዎች የከፊል ከብት አርቢነት ሕይወት የሚመሩ አሉ፡፡ የዚህ ዓይነት ማኅበረሰብ ኑሮ የተመሠረተው በከብት ማርባትና በእርሻ ሥራ ላይ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ከብት አርቢዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ በመኖሪያ ሥፍራቸው ጉልህ የአየር ጠባይ ለውጥ እስካልታየ ድረስ ቤት ሠርተው ይኖራሉ፡፡ በአጠቃላይ በከብት አርቢዎች ወይም በከፊል ከብት አርቢዎች አኗኗር ላይ የዝናብ መጠን መዛባት ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

ስለዚህ በከብት እርባታ ላይ ኑሮአቸውን የመሠረቱ ማኅበረሰቦች በአካባቢአቸው የሚገኙ ወንዞችን በመገደብና በመጥለፍ የመስኖ እርሻ በመጀመር የተረጋጋ ሕይወት እንዲኖራቸው ማገዝ ይቻላል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 2.3

**ክንውን**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ክረምት(summer) ሲሆን በሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ የሚኖረው ወቅት ምን ይባላል?
- ንፍቀ ክበብ ማለት ምን ማለት ነው?
- ወቅቶች በእርሻና በከብት አርቢነት እንቅስቃሴ ላይ የሚያስከትሉአቸውን ተጽእኖዎች አብራሩ፡፡
- ከብት አርቢነት ማለት ምን ማለት ነው?
- በኢትዮጵያ እርጥበታማና ደረቅ ወቅቶችን በማወዳደርና በማነጻፀር አስረዱ፡፡
- የደረቅ ወቅት በግጦሽ መሬቶች ላይ የሚያስከትላቸውን ተጽእኖዎች በቡድን ተወያዩ፡፡
- ከፊል በረሃማነት ባለው አካባቢ የከብት አርቢነት ሥራ ለምን ከእርሻ ሥራ የበለጠ ጠቃሚ እንደሆነ ተከራከሩ፡፡

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- የኢትዮጵያ ንድፍ ካርታ ከሳላችሁ በኋላ ከብት አርቢ ሥፍራዎችን አሳዩ፡፡

**የቡድን ሥራ**

- ስለ ከብት አርቢነት መረጃ አሰባስባችሁ የጽሑፍ ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ውይይት አቅርቡ፡፡

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

***መስፈርት፡-*** በመሬት ሳይ በሁለት ነጥቦች መካከል ያለ ርቀት በካርታ ሳይ የሚገለጽበት ንጽፅራዊ መለኪያ ነው፡፡

***ምሕዋር፡-*** መሬት በፀሐይ ዙሪያ በምትዞርበት ወቅት ተከትላ የምትጓዝበት የሐሳብ መስመር ነው፡፡

***ሽክርክሪት፡-*** መሬት በራሱዋ ዛቢያ ሳይ በሃያ አራት ሰዓታት ውስጥ የምትፈጽመው እንቅስቃሴ ነው፡፡

***ቅርፅ፡-*** አንድ ነገር የሚኖረው ገጽታ ወይም እይታ ነው፡፡

***ንድፍ ካርታ፡-*** መረጃ በመሰብሰብና መስፈርት በመወሰን በዝርግ ወረቀት ሳይ በግለሰብ የሚሠራ የአንድ አካባቢ ንድፍ ነው፡፡

***አቅጣጫ፡-*** የአንድ ተንቀሳቃሽ ግለሰብ ወይም ነገር የፍሰት መስመር ነው፡፡

***እርሻ፡-*** መሬትን በማረስ የሚከናወን ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡

***ከብት እርባታ፡-*** ከብቶች በማርባት ሳይ የተመሠረተ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡

***ካርታ፡-*** በመሬት ሳይ የሚታዩ ነገሮች በዝርግ ወረቀት ሳይ አሳንሶ በሥዕል መልክ የሚያቀርብ መረጃ ነው፡፡

***ወቅት፡-*** የሙቀት፣ የቅዝቃዜ፣ የዝናብ መጠን፣ የነፋስ አቅጣጫ ተለይቶ የሚታወቅበት ባህላዊ የዓመቱ ጊዜ አከፋፈል ነው፡፡

***ዙረት፡-*** መሬት በፀሐይ ዙሪያ በ$365\frac{1}{4}$ ቀናት ውስጥ የምትፈጽመው እንቅስቃሴ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

- መገኛን በመሬት ላይ ወይም በካርታ ላይ ወይም በንድፍ ካርታ ላይ ማሳየት ይቻላል፡፡
- መስፈርት በካርታ ላይ እና በመሬት ላይ ባለ ርቀት መካከል ያለ ጥመርታ ወይም ንጽፅር ነው፡፡
- ንድፍ ካርታ መስፈርት በመጠቀም በተሰባሰበ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የሚቀርብ የአንድ ውሱን አካባቢ ንድፍ (Plan) ነው፡፡
- የመሬት ቅርፅ ሞላላ ክብ ነው፡፡
- የመሬት ዛቢያ ከቀጥተኛ ቋሚ መስመር በ23 $\frac{1}{2}°$ ያጋደለ ነው፡፡
- የመሬት እንቅስቃሴዎች ሽክርክሪትና ዙሪት ይባላሉ፡፡
- መሬት በፀሐይ ዙሪያ በምትዞርበት ወቅት ተከትላ የምትንቀሳቀስበት የሐሳብ መስመር ምሕዋር ይባላል፡፡ ምሕዋር ሞላላ ቅርጽ አለው፡፡
- የመሬት መሽከርከር ከሚያስከትላቸው ውጤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የቀንና ሌሊት መፈራረቅና ፀሐይ በመሬት ዙሪያ የምትንቀሳቀስ መስላ መታየት ናቸው፡፡
- የመሬት ዙሪት የቀንና ሌሊት ርዝማኔ መለያየትና የወቅቶች መፈጠርን ያስከትላል፡፡
- ወቅቶች በእርሻ ሥራና በከብት አርቢዎች ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሐሰት" በማለት ምላሽ ስጡ።**

1. የአንድን ነገር መገኛ በአካባቢው ከሚገኝ ሌላ ነገር ጋር በማነጻፀር ማወቅ ይቻላል።
2. አቀጣጫ የአንድ እንቅስቃሴ ፍሰት የሚታይበት መስመር ነው።
3. መሬት ሁለት ንፍቀ ክበብ አላት።
4. ወቅት የመሬት ዙሪት ውጤት ነው።
5. አብዛኛው የኢትዮጵያ አራሽ ገበሬዎች ኑሮ በክረምት ዝናብ ላይ የተመሠረተ ነው።

**ለ. በ «ሀ»ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት በ «ለ» ሥር ከቀረቡት መግለጫዎች ጋር አዛምዱ።**

| | ሀ | ለ |
|---|---|---|
| ___________ | 1. ሉል | ሀ. የቀንና ሌሊት መፈራረቅ |
| ___________ | 2. ዛቢያ | ለ. የአጭር ጊዜ የዝናብ ወቅት |
| ___________ | 3. ሽክርክሪት | ሐ. የሐሳብ መስመር |
| ___________ | 4. ዙሪት | መ. የወቅቶች መፈራረቅ |
| ___________ | 5. ፀደይ (በልግ) | ሠ. የመሬት ቅርጽ ወካይ |
| | | ረ. ንፍቀ ክበብ |
| | | ሰ. ፍጹም ክብ |
| | | ሸ. ሰንደቅ |

**ሐ. ለሚከተለው ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ ፊደሉን በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ አስፍሩ።**

___________1. መሬት ሞላላ ክብ ቅርጽ እንዳላት ተቀባይነት ያገኘው መቼ ነው?

ሀ. ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከአንደኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ
ለ. ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከሁለተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ
ሐ. ከክርስቶስ ልደት በፊት ከሁለተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ
መ. ሰዎች መሬትን ካወቁ ጀምሮ

___________2. ትክክለኛውን የመሬት ቅርጽ የሚያሳየው ሞዴል ምን ይባላል?

ሀ. የመሬት ፎቶግራፍ ሐ. ሉል
ለ. ንድፍ ካርታ መ. ካርታ

___________3. የመሬት ዛቢያ ከቀጥተኛ ቋሚ መስመር ምን ያህል የዲግሪ ልኬት ልዩነት አለው?

ሀ. $30^\circ$ ለ. $20½^\circ$ ሐ. $23½^\circ$ መ. $22½^\circ$

______4. የመሬት የሽክርክሪት ውጤት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የቀንና ሌሊት መፈራረቅ
ሐ. የቀንና የሌሊት ርዝመት መለያየት
ለ. ፀሐይ መሬትን የምትዞር መምሰል
መ. የውቅያኖስና የነፋስ አቅጣጫ መቀየር

______5. የመሬት ሽክርክሪት አቅጣጫን የሚያሳዩ ጥንድ ቃላት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ምሥራቅ-ምዕራብ
ሐ. ምዕራብ-ምሥራቅ
ለ. ምሥራቅ-ደቡብ
መ. ሰሜን-ምሥራቅ

*መ. በባዶ ሥፍራ ላይ ተገቢ ቃላት ወይም ሐረጋትን በመሙላት ምላሽ ስጡ።*

1. በመሬት ላይ የሚታዩ ነገሮችን መስፈርት ተጠቅሞ በነጭ ዝርግ ወረቀት ላይ የሚያቀርብ ሥዕላዊ መግለጫ ______ ይባላል።
2. የመሬት ቅርጽ ______ ነው።
3. የካርታው መስፈርት 1ሣ.ሜ ለ 1ኪ.ሜ ተብሎ ከቀረበ ______ ላይ የ1ሣ.ሜ ርቀት ______ ላይ የ 1 ኪ.ሜ ርቀትን ይወክላል ማለት ነው።
4. መሬት በዛቢያዋ ላይ በየ24 ሰዓቱ አንድ ጊዜ የምትፈጽመው እንቅስቃሴ ______ ይባላል።
5. መሬት በፀሐይ ዙሪያ ስትዞር የምትከተለው የሐሳብ መስመር ______ በመባል ይታወቃል።

*ረ. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶች ስጡ።*

1. የካርታ ጠቀሜታዎችን ተናገሩ።
2. ንድፍ ካርታ ምንድን ነው?
3. ስለ መሬት ቅርጽና እንቅስቃሴዎች አጭር ማብራሪያ ስጡ።
4. የመሬት ዛቢያ ከቀጥተኛ ቋሚ መስመር ማጋደል ምን ያስከትላል?
5. በመሬት ሽክርክሪትና ዙሪት የሚፈጠሩ ክስተቶች ምንድን ናቸው?
6. በኢትዮጵያ የሚታዩ ወቅቶችን ዘርዝሩ።
7. ወቅቶች በእርሻና በከብት ርቢ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ ምንድን ነው?

## ፍተሻ

*የምታውቋቸውን ክንውኖች በመለየት በያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን (✓) ምልክት አኑሩ፡፡*

1. የካርታን ጠቀሜታ አብራራለሁ፡፡ ☐
2. ንድፍ ካርታ እንዴት እንደሚዘጋጅና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እገልጻለሁ፡፡ ☐
3. የትምህርት ቤቴን መገኛ አቅጣጫዎች የሚያሳይ ንድፍ ካርታ አዘጋጃለሁ፡፡ ☐
4. የመሬትን ቅርጽና እንቅስቃሴ አይነቶችን እለያለሁ፡፡ ☐
5. የመሬት እንቅስቃሴ የሚያመጣውን ለውጥ(ውጤት) አብራራለሁ፡፡ ☐
6. የወቅቶች መፈራረቅ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ (በእርሻና በከብት እርባታ) ያለው አሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖ አነፃፅራለሁ፡፡ ☐

# ምዕራፍ ሦስት

# አካባቢያችን

*ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች*

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ዋና ዋና እፅዋትና የዱር አራዊትን ታውቃላችሁ፣ ተገቢውን ጥበቃም ታደርጋላችሁ፡፡
- ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በአካባቢያችሁ በሚገኙ እፅዋትና የዱር አራዊት ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽእኖ ትገነዘባላችሁ፡፡

## 3.1 ዋና ዋና የእፅዋት ዓይነቶችና የዱር እንስሳት

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋና እፅዋትና የዱር አራዊትን ትለያላችሁ፡፡
- በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና የዱር እንስሳትን ስም ትዘረዝራላችሁ፡፡
- በአፍሪካ ቀንድ በሁሉም ሀገሮች የሚገኙ እንስሳትንና በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙትን ትለያላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- የተፈጥሮ እፅዋት
- የዱር እንስሳት

### ◈ የእፅዋት ዓይነቶች

- እፅዋት ምንድናቸው?

እፅዋት በምድር ላይ በተፈጥሮ የሚገኙ ወይም ሰዎች ተክለው የተንከባከቧቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሣር፣ ቁጥቋጦዎችና ልዩ ልዩ ዛፎች በአጠቃላይ እፅዋት ይባላሉ፡፡

### ◈ ደን

- ደን ምንድን ነው?
- የተለያዩ የደን ዓይነቶችን ዘርዝሩ?
- በደንና በሣር ምድር እፅዋት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
- የበረሃ እፅዋት ምንነትን ግለጹ፡፡

**ደን በአብዛኛው ዛፎችና ሌሎች እንጨታማ እፅዋት ዓይነቶች የሚታዩበት የተክሎች ስብስብ ነው። ደን ሰፋ ያለ አካባቢን ሊሸፍን ይችላል። በተፈጥሮ ደን በአንድ አካባቢ ራሱን በራሱ ለረጅም ዘመናት ማቆየት ይችላል።**

ቀጥሎ ስለ አፍሪካ ቀንድና ኢትዮጵያ እፀዋት ትማራላችሁ። በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ የተለያዩ የደን ዓይነቶች ይገኛሉ። እነዚህ የተለያዩ ደኖች የሚገኙት የተለያየ የመሬት ከፍታና የአየር ንብረት ባላቸው አካባቢዎች ነው።

## ◈ በኢትዮጵያ የሚገኙ እፅዋት

- በኢትዮጵያ የሚገኙ የእፅዋት ዓይነቶችን ዘርዝሩ?
- የእፅዋት ዓይነት በተለያየ ሥፍራ የተለያየ እንዲሆን የሚያደርገው ምንድን ነው?
- ደን ምንጠራ የሚያስከትለው አካባቢያዊ ጉዳት ምንድን ነው?

### 1. የከፍተኛ ተራራ እፅዋት

- የከፍተኛ ተራራ እፅዋት በየትኛው የኢትዮጵያ አካባቢ ይገኛሉ?
- የከፍተኛ ተራራ እፅዋት ምን ዓይነት ተክሎች አሉት?
- ለከፍተኛ ተራራ እፅዋት ጥቂት ምሳሌዎችን ጥቀሱ?

የከፍተኛ ተራራ እፅዋት ከአውሮፓው የከፍተኛ ሥፍራ እፅዋት (Alpine vegetation) ጋር ተመሳሳይነት አለው። በኢትዮጵያ የከፍተኛ ሥፍራ እፅዋት የሚገኙት ከሦስት ሺ ሜትር በላይ ከፍታ ባላቸውና ውርጫማ የአየር ንብረት በሚታይባቸው ቦታዎች ነው። የከፍተኛ ሥፍራዎች እፅዋት በአገሪቱ መካከለኛ፣ ሰሜንና በደቡብ ምሥራቅ ከፍተኛ ሥፍራዎች ለምሳሌ በራስ ደጀን፣ በጉና፣ በጭላሎና በባሌ ከፍተኛ አካባቢዎች ይገኛል።

### 2. ደን

- ደንን ከሣር ምድር እፅዋት ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?

ደን ከፊል-በረሃማ (semi-arid) እና ውርጭማ ከሆኑ አካባቢዎች በስተቀር በየትኛውም በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ክልል ይገኛል። ደን ከ 450 እስከ 3500 ሜትር ከፍታ ባላቸው አካባቢዎችና ከ200 እስከ 2200 ሚሊ ሜትር ዓመታዊ የዝናብ መጠን በሚያገኙ አካባቢዎች ይገኛል። በኢትዮጵያ በስፋት የሚገኝ የደን ዓይነት በሁለት ይከፈላል።

## ◈ በከፍተኛ ምድር የሚገኙ ደኖች

በከፍተኛ አካባቢ የሚገኙ የደን ዓይነቶች የሚከተሉትን የዛፍ ዓይነቶች ሊይዙ ይችላሉ። ከደን ዓይነቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የዝግባ፣ የጥድ፣ የቀርከሀ፣ የወይራና የኮሶ ዛፎች ናቸው።





*ምስል 3.1 የከፍተኛ አካባቢ ደኖች*

## ◈ በዝቅተኛ ምድር የሚገኙ ደኖች

- የዝቅተኛ መሬት ደኖች ቅጠለ-ረገፍና በወንዝ ዳርቻ የሚበቅሉ እፅዋት (gallery reverine vegetation) ተቀላቅለው ይታዩበታል፡፡ በወንዞች ዳርቻ የሚበቅሉ እፅዋት በስፋት የሚገኙት በአዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌና ገናሌን በመሳሰሉ ወንዝ ዳርቻዎች ነው፡፡ በወንዝ ዳርቻ የሚገኙ የዛፍ ዝርያ ዓይነቶች ሾላንና ዋርካን ያጠቃልላሉ፡፡



*ምስል 3.2 በወንዝ ዳርቻ የሚገኙ እፅዋት*

- በደረቅ መሬቶች ለየት ያሉ ዛፎችና እሾህማ ቁጥቋጦዎች ይገኙባቸዋል፡፡ የእነዚህ ዓይነት እፅዋት የዝናብ መጠን እስከ 1000 ሚ.ሜ ድረስ ባለባቸው ሥፍራዎች ይበቅላሉ፡፡ በደረቅ መሬቶች የግራር ጫካ በስፋት ይታያል፡፡
- በስፋት ከሚታዩት ተክሎች አንጻር የኢትዮጵያን ደኖች ቅጠለ-ሰፋፊና ቅምብብማ በማለት በሁለት ዓበይት ክፍሎች መክፈል እንችላለን፡፡

## ◈ ቅጠለ-ሰፋፊ ዝናባማ ደን

- **ቅጠለ-ሰፋፊ ዝናባማ ደን ምን ዓይነት ደን ነው?**
- **ቅጠለ-ሰፋፊ ደኖችን በየትኛው የኢትዮጵያ አካባቢ እናገኛለን?**

ቅጠለ-ሰፋፊ ዝናባማ ደን የምድር ወገብ ደን ናቸው፡፡ የተለያየ ጠንካራ እንጨት ያላቸው ዛፎች ይገኙበታል፡፡ የዚህ ዓይነት ደን በኢትዮጵያ ከፍተኛ መሬት ላይ በስፋት ይገኛል፡፡ በተለይም የዚህ ዓይነት ደን በአብዛኛው የሚገኘው ከባድ ዝናብ በሚያገኙ የሀገሪቱ የደቡብ ምዕራብ ከፍተኛ መሬቶች ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ደን ካላቸው አካባቢዎች ዋና ዋናዎቹ ወለጋ፣ ከፋ፣ ኢሉባቦርና ገሙ-ጎፋ ናቸው፡፡ ደኖቹ በስፋት የሚታዩት ከባሕር ጠለል በላይ ከ1500 ሜ እስከ 1800 ሜትር ከፍታ ባላቸው አካባቢዎች ነው፡፡ በዚህ አካባቢ የጫካ ቡና እንደ ተፈጥሮ ደን ይበቅላል፡፡ በደኖቹ የሚገኙ ዋና ዋና የዛፍ ዓይነቶች ወይራ፣ ቀረሮ፣ ዋንዛ፣ ጥቁር እንጨት፣ ብሣና፣ ብርብራ፣ የጫካ ቡና፣ ሐረጉችና በለሴ ናቸው፡፡



ምስል 3.3 ቅጠለ-ሰፋፊ ዝናባማ ደን

## ◈ ቅምብብማ ደኖች (Coniferous forest)

- ቅምብብማ የሚባሉት ምን ዓይነት ደኖች ናቸው?
- በቅምብብማ ደን ከሚገኙ ዛፎች የጥቂቶቹን ስም ዘርዝሩ።
- እነዚህ ደኖች ቅምብብማ (coniferous) የሚል መጠሪያ ለምን ተሰጣቸው?
- በኢትዮጵያ ቅምብብማ ደኖች የሚገኙባቸውን ሥፍራዎች ዘርዝሩ።
- የቅምብብማ ደን ዛፎች ዓይነት በመኖሪያ አካባቢያችሁ ካሉ ስማቸውን ዘርዝሩ።

ቅምብብማ ደኖች ከለምለም ደኖች ክፍል ይመደባሉ። በቅምብብማ ደን ውስጥ የሚታዩ ዛፎች ገር እንጨት ዓይነት ናቸው። ባለገር እንጨት ካላቸው ዛፎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ጥድና ዝግባ ናቸው። የጥድ ጫካዎች በአገራችን የሚገኙት በአንዳንድ የሸዋ አምባ-ምድር አካባቢዎችና ከፍታቸው ከ2000 ሜትር በላይ በሆኑ የአርሲና የባሌ ከፍተኛ ሥፍራዎች ነው። የዝግባ ጫካዎች ደግሞ በጥቂት የሐረርጌ፣ አርሲ፣ ባሌና የወለጋ ከፍተኛ ሥፍራዎች ይገኛሉ። ዝግባና ጥድ በቅምብብማ ደኖች የሚበቅሉ ዓይነተኛ የዛፍ ዝርያዎች ናቸው። ለእነዚህ ዛፎች ዕድገት ምቹ የከፍታ መጠን ከባሕር ጠለል በላይ 1500 ሜትር ነው።

**ቅምብብ ዘር ለሚሸከሙ ልቃቂት መሰል ቅርጽ ላላቸው ተክሎች የተሰጠ የወል መጠሪያ ነው። ቅምብብማ ዛፎች በተፈጥሮ ባሕርያቸው ዘር ተሸካሚ ልቃቂት መሳይ አካል አላቸው።**



ምስል 3.4 ቅምብብማ ዛፍ

### 3. በሣር የተሸፈነ (ሣርማ) ዛፍ ምድር - Savanna Grassland

- በሣር የተሸፈነ ምድር በየትኞቹ አካባቢዎች ይገኛል?
- በሣር በተሸፈነ ምድር ምን ዓይነት እፅዋት ይገኛሉ?

ሣርማ የዛፍ ምድር በከፍተኛም ሆነ ዝቅተኛ ምድሮች በአጠቃላይ የከፍታ መጠናቸው ከባሕር ጠለል በላይ ከ250 እስከ 2300 ሜትር ባሉት አካባቢዎች ሁሉ ይገኛል፡፡ እነዚህ ሥፍራዎች ከ200 እስከ 1400 ሚሊ. ሜትር የሚደርስ መለስተኛ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ያገኛሉ፡፡ ሣርማ የዛፍ ምድሮች በገሳ ሣር የተሸፈኑ ተራራማ ሥፍራዎች፣ ዛፎች ተበታትነው የሚበቅሉበት የሣር ምድር፤ ወይም የሣርና የቁጥቋጦ ምድሮችን ያጠቃልላል፡፡

ሣርማ የዛፍ ምድር በሦስት ዐበይት ዓይነቶች ይከፋፈላል፡፡ እነርሱም፡- (1) የጥድ ዛፎች ሣርማ ምድር፣ (2) የግራር ዛፎች ሣርማ ምድር (3) ቅልቅል ቅጠለ-ረገፍ ዛፎች ሣርማ ምድር ናቸው፡፡ የግራር ዛፎች ምድር ግራርና ቁጥቋጦች ተቀላቅለው የሚበቅሉበት ሣርማ መሬት ነው፡፡ ቅጠለ-ረገፍ ዛፎች በቅልቅል የሚበቅሉበት ሣርማ የዛፍ ምድር ደግሞ በደረቅ-ሞቃት ወቅት ቅጠላቸውን የሚያራግፉ እንደሾላና ዋርካ የመሳሰሉ ዛፎች የሚበቅሉበት የሣር ምድር ነው፡፡



ምስል 3.5 የግራር ዛፍ

## 4. የከፊል-በረሃና የጠፍጥሻ (Steppe) እፅዋት

- የከፊል በረሃ እፅዋት ምንድን ናቸው?
- ጠፍጥሻ እፅዋት ምን ዓይነት ናቸው?

የከፊል በረሃ እፅዋት አካባቢ በበረሃ እፅዋት (xerophytes) የተሸፈነ ነው። በዚህ አካባቢ በብዛት የሚገኙት እፅዋት አንድ ላይ እጅብ ብለው የሚበቅሉ ሣሮች፣ ቸፍርጐች፣ እሾሃማ ቁጥቋጦዎች፣ ቁጥቋጦ የግራር ዛፍ ዝርያዎች፣ ቴምር ዛፎችና ቁልቋል ናቸው። የበረሃ እፅዋት የአየር ንብረቱ በጣም ሞቃትና ደረቅ በሆነ አካባቢ የሚበቅሉ ናቸው። እነዚህ እፅዋት የሚበቅሉበት አካባቢዎች ከባሕር ጠለል በላይ እስከ 1400 ሜትር ከፍታ አላቸው። እነዚህ አካባቢዎች የሚያገኙት ዓመታዊ አማካይ የዝናብ መጠን ደግሞ ከ250 ሚሊሜትር በታች ነው።

የበረሃና የከፊል-በረሃ እፅዋት በቆላማ የአገራችን አካባቢዎች በተለይም በሰሜን-ምዕራብ፣ በሰሜን ምሥራቅ (አፋር ዝቅተኛ ሥፍራዎች)፣ በደቡብ ምሥራቅ (ኦጋዴን) እና በደቡብ የአገሪቱ ድንበር በስፋት ይበቅላሉ።

### ◈ በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ እፅዋት

የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተለያዩ እፅዋት የሚገኙበት ነው። ዋና ዋናዎቹ የእፅዋት ዓይነቶችም የከፍተኛና የዝቅተኛ ምድሮች እፅዋትና የከፊል-በረሃ እፅዋት ተብለው ይጠራሉ።

**የክለሳ ጥያቄዎች 3.1**

**ክንውን ሀ**

***ሀ. በዕውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- በኢትዮጵያ የከፍተኛ ተራራ እፅዋትን ዘርዝሩ።
- ስለ ኢትዮጵያ የዝቅተኛ ምድር ደኖች አጭር ማብራሪያ አቅርቡ።
- ቅጠለ-ሰፋፊ ደኖች በየትኛው የኢትዮጵያ አካባቢ ይገኛሉ?
- በኢትዮጵያ ቅጠለ-ሰፋፊ ደኖችና ቅምብብማ ደኖች መካከል ስላለው ልዩነት አስረዱ።

***ለ. የሚሠሩት ተግባራት***

***የቡድን ሥራ***

- ከቤተ መጽሐፍት አግባብ ያላቸው መጽሐፍት በማሰባሰብ:-
  - በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ የሚገኙ የደን ዓይነቶችን ዘርዝሩ።
  - ደንን ከሣር ምድር ልዩ የሚያደርገው ምን እንደሆነ አጭር ማብራሪያ በጽሑፍ አቅርቡ።
  - ቅጠለ ሰፋፊ ዝናባማ ደንን አስመልክቶ አጭር የጽሑፍ ማብራሪያ አቅርቡ።
  - ስለዱር እንስሳት ምጣኔ ሃብታዊ ጠቀሜታ የጽሑፍ ማብራሪያ ስጡ።

## ለ. የዱር እንስሳት

- የዱር እንስሳት ምንድን ናቸው?
- ስለ ዱር እንስሳት ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ማብራሪያ ስጡ።

የዱር እንስሳት የምንለው ለማዳ ያልሆኑ በተፈጥሮአዊ አካባቢ የሚገኙ እንስሳትን ነው፡፡ የዱር እንስሳት የየራሳቸው መካነ-ሕይወት (habitat) አላቸው፡፡ ሁሉም በተወሰነ ሥነ ምኅዳር ውስጥ አንዱ በሌላው ላይ ጥገኛ በመሆን ይኖራሉ፡፡ እያንዳንዱ ክልል ወይም ሀገር የራሱ የሆኑ የዱር እንስሳት አሉት፡፡ የዱር እንስሳቱ ዓይነት በየክልሉ ወይም በየሀገሩ የአየር ንብረትና በሚገኙበት መልክዓ ምድር ልዩነት መሠረት ይለያያል፡፡ ከዚህ አንጻር በአጠቃላይ ለአፍሪካ ቀንድ ናሙና የሚሆን የኢትዮጵያን የተለያዩ የዱር እንስሳት እናጠናለን፡፡

## ◈ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት

- የተለያየ የአመጋገብ ልምድ ያላቸው የዱር እንስሳት በአንድ ሥነ-ምኅዳራዊ አካባቢ የሚኖሩት ስምንድን ነው?
- ዝርያቸው ሊጠፋ በአደገኛ ሁኔታ ላይ ከሚገኙ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት መካከል ጥቂቱን ጥቀሱ፡፡
- የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ለአገሪቱ ያላቸው ጠቀሜታ ምን እንደሆነ አስረዱ፡፡

ኢትዮጵያ የተለያየ የአየር ንብረትና የእፅዋት ክልሎች ያሏት በመሆኑ በዓይነታቸውና በቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የዱር እንስሳት አሏት፡፡ ከኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ሀብት መካከል 7 የአጥቢ ዝርያዎች 25 የአእዋፍ ዝርያዎች ብርቅዬ ወይም የሀገሪቱ ብቸኛ ሀብት ናቸው፡፡ ብርቅዬ የሚባሉት የዱር እንስሳት ከኢትዮጵያ በስተቀር በየትኛውም የዓለም አካባቢ የማይገኙ ናቸው፡፡

ከሁሉም በበለጠ በርካታ የዱር እንስሳት የሚገኙት በምዕራቡና በደቡቡ የሀገሪቱ ክፍል ነው፡፡ ለምሳሌ የኦሞ-ማጎ ብሔራዊ ፓርኮችና የጋምቤላ ብሔራዊ ክልል በዱር እንስሳት ሀብታቸው እጅግ የበለፀጉ ናቸው፡፡ በተጨማሪ የሰሜን ተራሮች፣ የአርሲ-ባሌና ሐረርጌ ከፍተኛ ሥፍራዎች የተለያዩ የዱር እንስሳት የሚገኙባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡

በርካታ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት የሚገኙበትን መካነ ሕይወት በሚከተሉት ዋና ዋና መደቦች ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡


### 1. በሁሉም የአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የዱር እንስሳት (common wild animals)

አንዳንድ የዱር እንስሳት በሁሉም የአፍሪካ ቀንድ አካባቢዎች ሊገኙ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ጅብ በሁሉም የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሊገኝ ይችላል፡፡ ቀበሮ ደግሞ በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ የሚገኝ የዱር እንስሳ ነው፡፡


ጅብ


ቀበሮ

*ምስል 3.6 የትም ተገኝ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት*




ቀጭኔ




የዱር አህያ



የሜዳ አህያ



ዝሆን



አጋዘን



ሣላ




አውራሪስ

ምስል 3.7 እፅዋት በል የዱር እንስሳት



አንበሣ



ነብር



አቦሸማኔ

ምስል 3.8 ሥጋ በል የዱር እንስሳት

## ◈ አዕዋፍ

- አዕዋፍ ምንድን ናቸው?
- ስለ አዕዋፍ መካነ ሕይወት ወይም ምቹጌና ስለ አኗኗር ዘይቤያቸው ተወያዩ።

ኢትዮጵያ የራሷ የሆኑ ብርቅዬና በፍልሰት የሚገቡ በርካታ አዕዋፍ አሏት። እነዚህ አዕዋፍ በቀለማ ቀለም የተዋቡ ናቸው። የኢትዮጵያ አዕዋፍ በብዛት የሚገኙት በስምጥ ሸለቆ ደኖችና የውኃ አካላት ነው። የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ከአውሮፓና ከእስያ ፈልሰው ለሚመጡ የአዕዋፍ መንጋ መልካም የበጋ ወቅት ማሳለፊያ ናቸው።



ነጭ ፔሊካን



ፍላሚንጎ



ዝይ



አሣ ወጊ


ምስል 3.9 ውብ የኢትዮጵያ አዕዋፍ

## 2. በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ እንስሳት (Endemic Animals)

ብርቅዬ እንስሳት ማለት በአንድ ውስን መልክአምድራዊ አካባቢ ብቻ ተገድቦ የሚኖር የእንስሳት ዝርያ ማለት ነው፡፡

ብርቅዬና ብቸኛ አጥቢዎች በየትኛውም አካባቢ በአናሳ ቁጥር ይገኛሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ኀዳጥ (rare) እንስሳት ይባላሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ብርቅዬ አጥቢዎች በኢትዮጵያ ከፍተኛ ሥፍራዎች እጅግ አነስተኛ በሆነ ቁጥር ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

- **ዋልያ** በሰሜን ተራሮች ይገኛል፡፡



ምስል 3.10 ዋልያ

- **ኒያላ** በባሌ ተራሮች ሣርማ ዛፍ ደኖች ይገኛል፡፡



ምስል 3.11 ኒያላ

- **ጭላዳ ዝንጀሮ** በሰሜን ተራራዎች ይኖራል፡፡



ምስል 3.12 ጭላዳ ዝንጀሮ

- **ምኒልክ ድኩላ** የሚገኘው በመካከለኛ ኢትዮጵያ ገመገም (ከፍተኛ ሥፍራ) እና በባሌ ከፍተኛ ሥፍራዎች ነው፡፡




ምስል 3.13 የምኒልክ ድኩላ

- **የስዌይን ቆርኬ** የሚገኘው በነጭ ሣር ብሔራዊ ፓርክና በሰንቀሌ መናኸሪያ ነው፡፡



ምስል 3.14 የስዋይን ቆርኬ

- **የሰሜን ቀበሮ** በሰሜን ገመገምና በባሌ ከፍተኛ ሥፍራዎች ይገኛል፡፡



ምስል 3.15 ሰሜን ቀበሮ

➢ **የዱር አህያ** በአፋርና በአገሪቱ ደቡብ ምሥራቅ ከፍተኛ ሥፍራዎች ይገኛል፡፡



*ምስል 3.16 የዱር ስህያ*

## 3. ዝርያቻው ሊጠፉ የተቃረቡ እንስሳት (Endangered Animals)

- በኢትዮጵያ ዝርያቸው ሲጠፋ የተቃረቡ እንስሳትን ዘርዝሩ፡፡
- ይህን ችግር ለመቅረፍ ምን መደረግ እንዳለበት ሐሳብ አቅርቡ፡፡

የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ሀብት በቁጥርም ሆነ በዓይነቱ እጅግ አስፈሪ በሆነ ፍጥነት እያነሰ ነው፡፡ እንዲያውም ጥቂት የእንስሳት ዝርያዎች ጨርሶ ሊጠፉ ተቃርበዋል፡፡ ለምሳሌ ብርቅዬና ብቸኛ እንስሳት፣ እንደ ዋልያ፣ የሰሜን ቀበሮ፣ ኒያላ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ ስለመጣው የዱር እንስሳት መጥፋት የሚከተሉት ምክንያቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ሀ) በእርሻ መሬቶች መስፋፋት እንዲሁም በከተሞችና ኢንዱስትሪዎች ፈጣን ዕድገት የተነሣ በደን መመንጠር የዱር እንስሳት ምቹ ወይም መካነ - ሕይወት መውደሙ፣

ለ) የእንስሳቱን ሥጋ፣ ቆዳ፣ ፀጉር፣ ቀንድና ጥርስ ለማግኘት ሲባል የሚፈጸም ሕገ-ወጥ አደን፣

ሐ) የግጦሽ መሬቶችን የማስፋፋት ተግባር የዱር እንስሳትን ምቹ (መካነ - ሕይወት) እያጠበበ መምጣቱ፣

መ) በየጊዜው የሚከሰት ሰደድ እሳት፣

ሠ) የድርቅ በየጊዜው መደጋገም፣ በውኃና ምግብ ላይ እጥረት መፍጠር በምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች 3.1

**ክንውን ለ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- የዱር እንስሳት ምን ማለት እንደሆነ ትርጉሙን ስጡ፡፡
- አንዳንድ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ሊጠፉ የተቃረበበት ምክንያት ምንድን ነው?
- ዝርያቸው ሊጠፉ የተቃረቡ እንስሳትን ባሉበት ሁኔታ እንዲቀጥሉ ከተተወ ምን የሚከተል ይመስላችኋል?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- የኢትዮጵያን ካርታ በጥንቃቄ ከተመለከታችሁ በኋላ የኒያላ፣ ዋሊያና ሰሜን ቀበሮ መገኛን አሳዩ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኝ ብሔራዊ ፓርክና ቤተ አራዊት (Zoo) ጐብኙና ከኃላፊዎች ጋር ቃለ ምልልስ በማካሄድ ለክፍላችሁ ዘገባ አቅርቡ፡፡
- ዝርያው ሊጠፋ ከተቃረበ ስለ አንድ እንስሳ ምንጭ ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ ዘገባ በመጻፍ ለክፍላችሁ ተራ በተራ አቅርቡ፡፡

## 3.2 የዱር እንስሳትና እፅዋት የሚሰጡት ጥቅም

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የእፅዋትና የዱር እንስሳት ጠቀሜታን ታስረዳላችሁ፡፡
- ለዱር እንስሳት የተፈጥሮ መኖሪያቸው ጥበቃ ማድረግ ያለው ጥቅም ታብራራላችሁ፡፡
- እፅዋትንና የዱር እንስሳትን መንከባከብ ለምን ጠቃሚ እንደሆነ በዙሪያችሁ ለሚገኙ ማኅበረሰቦች ታስረዳላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- የተፈጥሮ ሚዛን
- አርሶ አደር
- ቱሪዝም
- ማኅበረሰብ

### ◈ በዱር እንስሳትና እፅዋት መካከል ተፈጥሮአዊ ሚዛንን መጠበቅ

- በዱር እንስሳትና በእፅዋት መካከል ያለው ትስስር ምንድን ነው?
- በዱር እንስሳትና በእፅዋት መካከል የተፈጥሮ ሚዛን እንዴት ይጠበቃል?
- በአንድ በተወሰነ ሥነ-ምኅዳር ውስጥ በሚገኙ የዱር እንስሳትና እፅዋት መካከል ያለው ተፈጥሮአዊ ትስስር ምንድን ነው?
- በአካባቢያችሁ በሚገኝ በአንድ በተወሰነ ሥነ-ምኅዳር ውስጥ በሚኖሩ ሕይወት ባላቸውና ሕይወት በሌላቸው ነገሮች መካከል ስለሚታይ የእርስ በርስ መስተጋብር አብራሩ፡፡

በማንኛውም ሥነ-ምኅዳር ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸው ነገሮች አብረው ይኖራሉ፡፡ ሕይወት ያላቸው ነገሮች በተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ አካባቢዎች የሚኖሩ ተክሎችና እንስሳት ናቸው፡፡ ሕይወት የሌላቸው ደግሞ በተመሳሳይ ሥነ-ምኅዳር የሚኖሩ ግዑዝ የሆኑ ነገሮችን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው እፅዋት በአንድ በተወሰነ አካባቢ በተፈጥሮ በቅለው የሚታዩ ተክሎች ናቸው፡፡ የአንድ አካባቢ እፅዋት ደን፣ የሣር ምድር ወይም ቁጥቋጦዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ደኖች ዛፍ ተንጠልጣይ ለሆኑ ቀላል እንስሳት ምቹ መኖሪያ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ደኖች ለእንስሳቱ ምግብና መጠለያ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

ሣርማ ምድሮች ለብዙ ዓይነት የዱር እንስሳት መካነ ሕይወት ናቸው፡፡ የእንስሳቱም ዓይነት ትላልቅና ትናንሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ከትናንሽ እንስሳት መካከል እንደ ጥንቸል፣ አይጥ፣ እባብና የተለያዩ አዕዋፍን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከትላልቅ እንስሳት ደግሞ አጋዘን፣ ቀጭኔ፣ የሜዳ አህያ፣ አውራሪስ፣ አንበሣ፣ ተኩላ፣ አነርና ቀበሮ ይገኙበታል፡፡

ከተክሎች ጋር በንጽጽር ሲታይ በመሬት ላይ ከሚገኙ ሕይወት ካላቸው ነገሮች መካከል እንስሳት እጅግ አነስተኛውን ክፍል ይሸፍናሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንስሳት የተፈጥሮ አካባቢዎችን ይዘት ለመወሰንም ሆነ ጠብቆ ለማቆየት እጅግ ጠቃሚ የሆነ ድርሻ አላቸው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 3.2

**ክንውን ሀ**

***ሀ. በእውቀት ላይ  የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- ዛፎች በአንድ አካባቢ ምቹኔ ወይም መካነ ሕይወት በመሆን፣ የመሬት መሸርሸርን በመከላከልና የአፈር ርጥበት ጠብቆ ከማቆየት አንጻር ያላቸውን ጠቀሜታ ግለጹ፡፡
- ተክሎች የአንድ አካባቢን አየር ንብረት እንዴት መቆጣጥር እንደሚችሉ አስረዱ፡፡

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት /የቡድን ሥራ/***

- በአካባቢያችሁ ደን ላይ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በውስጡ የሚታዩ የዛፍ ዓይነቶችን መለያ ከሰጣችሁ በኋላ የአካባቢያችሁ ማኀበረሰብ በደን ሀብቱ ላይ ያለውን አጠቃቀም ገምግሙ፡፡ ማህበረሰቡ አካባቢውን በአግባቡ ወይም አለ አግባብ መጠቀሙን መለየት አለባችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኝ ሣርማ ምድር ላይ ጥናት በማካሄድ በተክሎች፣ በእንስሳትና ግዑዝ በሆኑ እንደ አፈር ባሉ መካከል ስላለው ትስስርና የእርስ በእርስ ቁርኝት አጭር ዘገባ አቅርቡ፡፡
- የአካባቢአችሁን ሥነ-ምኀዳር እንዴት መንከባከብና መጠበቅ እንደምትችሉ እንደዚሁም የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ በቡድን ተከፋፍላችሁ ተወያዩበት፡፡

## ◈ አርሶ አደሮችና የዱር እንስሳት ተስማምተው መኖር

- የአርሶ አደሮች አካባቢና በአካባቢያቸው በተጓዳኝነት የሚገኝ ሀብት ምን እንደሆነ አስረዱ፡፡
- አርሶ አደሮች ምን ያህል ከዱር አንስሳት ጋር የተጣጣመ አኗኗር እንዳላቸው ግለጹ፡፡

የአርሶ አደሮች ኑሮ ዘለቄታ የሚወሰነው የተፈጥሮ አካባቢን በአግባቡ መጠቀም ሲችሉ ነው፡፡ የተፈጥሮ አካባቢ ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች አጠቃሎ እንደሚይዝ ቀደም ሲል ተምራችኋል፡፡ ሕይወት ያላቸው ነገሮች  እፅዋትና  እንስሳትን ያጠቃልላል፡፡  ውኃ፣ አፈር፣ አለትና የመሳሰሉት ሕይወት የሌላቸው የተፈጥሮ ሀብት ናቸው፡፡

አርሶ አደሮች የዱር እንስሳቱ የተፈጥሮ ሀብቶች መሆናቸውን ተቀብለው ለአካባቢው ሕያውነት አስፈላጊ መሆናቸውን መረዳት አለባቸው፡፡ እነዚህ እንስሳት በጥንቃቄ ከተያዙ ወደ አካባቢው ሰዎች በመምጣት እንዲጎበኙ ስለሚያስችል የአካባቢው ነዋሪዎች ከገቢው ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ከዚህም በላይ አርሶ አደሮቹ እንስሳቱ የሚኖሩበትን አካባቢ በተንከባከቡ ቁጥር የአካባቢው ተፈጥሮአዊ ሚዛን ይጠበቃል፡፡ ይህ በመሆኑም የአፈር ለምነት የጠበቃል፡፡ የከርሰ ምድር ውኃ መጠን ከፍ ይላል፣ የዝናብ መጠን አስተማማኝ ይሆናል፣ የአፈሩ ለምነትና ርጥበት ይጠበቃል፡፡ ይህ ደግሞ የአርሶ አደሩን ገቢ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

## ◈ ቱሪዝም ለማኀበረሰቡ፣ ለዱር እንስሳትና አርሶ አደሮች ያለው ጠቀሜታ

- እፅዋትና የዱር እንስሳት ከቱሪስት መስሕብነታቸው አንጻር ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ ቀንድ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ አስረዱ፡፡
- ቱሪዝም ለኢትዮጵያ ባለው ጠቀሜታ ላይ በቡድን ሆናችሁ ሐሳብ ተለዋወጡ፡፡
- በሰዎች ፍላጐትና በዱር እንስሳት መካከል ሚዛን በመጠበቅ ሁለቱ አብረው በሰላም እንዴት መኖር እንደሚችሉ አስረዱ፡፡

በኢትዮጵያ በርካታ ጥበቃ የሚደረግላቸው የተፈጥሮ አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ጥበቃ የሚደረግላቸው የተፈጥሮ አካባቢዎች ብሔራዊ ፓርኮችና መናኸሪያዎች ወይም ቤተአራዊት (sanctuary) ተብለው ይጠራሉ፡፡ በእነዚህ ጥበቃ በሚደረግላቸው ሥፍራዎች በዓይነታቸው በርካታ የሆኑ የዱር እንስሳት ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ በብሔራዊ ፓርኮችና መናኸሪያዎች መጠበቅ የተነሳ ለቱሪዝም ዕድገት እጅግ የተመቻቸ ሁኔታ አለ፡፡ የብሔራዊ ፓርኮቹና የመናኸሪያዎቹ የእንክብካቤና ጥበቃ ተግባራት አርሶ አደሮችን ጨምሮ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በሙሉ ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡ በተፈጥሮ አካባቢው የሚገኙ እንስሳትም በእኩል ደረጃ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤ ምክንያቱም ምቹ ሁኔታዎቻቸውን የሚረብሽ ነገር ባለመኖሩና በእንክብካቤና በጥበቃ የተያዘ በመሆኑ ነው፡፡

## ውስን ጥናት

### የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ

የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ በርካታ ማራኪ ከሆኑ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ካላቸው ቦታዎች አንዱ ነው፡፡ የፓርኩ አጠቃላይ ስፋት 179 ስኩዌር ኪ.ሜ ያህል ነው፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ በምዕራባዊ የሰሜን ከፍተኛ ሥፍራዎች በአማራ አምባ-ምድር ላይ ይገኛል፡፡ ፓርኩ እ.ኤ.አ በ1978 የዓለም ቅርስ በመሆን በዩኔ ተመዝግቧል፡፡ ፓርኩ በዓመት ከ2000 በላይ የውጭ ቱሪስቶችና በርካታ የሀገር ውስጥ ጉብኚዎችን ያስተናግዳል፡፡



ምስል 3.17 የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ

የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ገጸምድር በዓለም ላይ እጅግ አስደናቂ ከሆኑት መካከል አንዱ ነው፡፡ የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ከፍተኛው የተራራ ጫፍ የራስ ደጀን ተራራ ነው፡፡ ከባሕር ጠለል በላይ 4,620 ሜትር ከፍታ አለው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 3.2

**ክንውን ለ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች***

- ሥነ ምኅዳር ምንድን ነው?
- የተፈጥሮ ሚዛን ለመጠበቅ ተክሎችና የዱር እንስሳት በአንድ አካባቢ እንዴት ጎን ለጎን መኖር እንዳለባቸው ግለጹ፡፡
- እፅዋትና የዱር እንስሳት በኢትዮጵያ በቱሪስት መስህብነት ያላቸውን አስተዋጽኦ አስረዱ፡፡
- ኢትዮጵያ ከቱሪዝም እንዴት የበለጠ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችል ግለጹ፡፡
- የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በቱሪስቶች በስፋት የሚጎበኘው ለምንድን ነው?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት /የቡድን ሥራ/***

- ምንጮችን በማፈላለግ በእፅዋትና በዱር እንስሳት መካከል ስላለው የርስ በርስ መስተጋብር አጭር የጽሑፍ ዘገባ አቅርቡ፡፡

# 3.3 ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በእፅዋትና በዱር እንስሳት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተፅዕኖ

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በአካባቢያችን በሚገኙ እፅዋትና የዱር እንስሳት ላይ የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽእኖ ተንትናችሁ ታስረዳላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- የእፅዋት መመናመን
- የተፈጥሮ አካባቢ የመሸከም አቅም
- ሰደድ እሳት

## ◈ የእፅዋት መጥፋት

- የእፅዋት መመናመን እንዴት ይከሰታል?
- የእፅዋት መመናመን የሚያስከትላቸው ተጽእኖዎች ምንድን ናቸው?
- በአካባቢያችሁ የተመናመነ ደን ወይም የሣር-ምድር ካለ እንዴት እንደተመናመነ አስረዱ።
- የእፅዋት መመናመን ለመገደብ፣ የእንስሳት ፍልሰትን ለመቆጣጠር የደን ሀብት መሳሳትን ለመከላከል ምን መደረግ እንዳለበት ሐሳብ አቅርቡ።

በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት የተጋረጡባቸው የተፈጥሮ አካባቢ ችግሮች ያደጉ ሀገራት ከሚያጋጥሙዋቸው ችግሮች ይለያሉ። በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት የተፈጥሮ አካባቢ ችግሮች መነሻ ኋላ ቀርነትና ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ነው። በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ከሚችለው በላይ መሄዱን የሚያመለክቱ መረጃዎች አሉ።

በፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የተነሣ በኢትዮጵያ የተፈጥሮ አካባቢ የመሸከም አቅም አሽቆልቁሏል። ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ተጨማሪ የተፈጥሮ ሀብት ጥያቄን ያስነሣል። በሀብት አጠቃቀም ምጣኔም ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት የቴክኖሎጂ ዕድገት ኋላ ቀር በመሆኑ ተጨማሪ የሀብት ፍላጎት፣ ኋላቀር የመሬት አጠቃቀም፣ ሌሎች ሀብቶችንም ያላግባቡ የመጠቀም ሁኔታ በስፋት ይቀጥላል። የዚህ ዓይነቱ ኋላቀርና ባሕላዊ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ጉዳት ከማስከተል ያለፈ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ የለውም።

## ◈ የዱር እንስሳት መሰደድ

- የዱር እንስሳት መሰደድ ምንን ይገልጻል?
- የዱር እንስሳት የሀገር ቅርስ አካል በመሆናቸው ብቻ ከጥፋት እንዲድኑ መጠበቅ አያስፈልግም ትላላችሁን?
- የዱር እንስሳት ለቀው ከተሰደዱበት አካባቢ ላይ ምን ዓይነት ሁኔታ የሚከሰት ይመስላችኋል?
- በአካባቢያችሁ ኅብረተሰቡ የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ እንዲጠቀም ምን ዓይነት ምክር ትለግሳላችሁ?

የዱር እንስሳት የሚረብሻቸው ባዕድ ነገር እስካልተፈጠረ ድረስ በአንድ ሥነ-ምኅዳር ውስጥ ላልተወሰነ ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ። የተፈጥሮ ምቹጌያቸው የወደመ የዱር እንስሳት አካባቢውን ለቀው ወደ ሌላ አካባቢ ይሰደዳሉ። የተፈጥሮ ምቹጌዎች በተፈጥሮአዊ ወይም በሰዎች አማካኝነት ሊወድሙ ይችላሉ። ስለዚህ እንስሳትን በቀድሞ መኖሪያቸው እንዲቆዩ ለማድረግ ምቹጌያቸው ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል።

## ◈ የደን ሀብት መመናመን

- በአካባቢያችሁ የደን ሀብት አጠቃቀም  ምን ይመስላል?
- የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ የመጠቀም ፋይዳ ምንድን ነው?

በአገራችን ቀደም ሲል በደን የተሸፈኑ መሬቶች በሚያስፈራ ሁኔታ ደኖቹ ተመንጥረው አልቀዋል፡፡ ደኖች የሚመነጠሩት ተጨማሪ የእርሻ መሬቶችን ለማግኘትና ለአዳዲስ ሠፈራዎች የቤት ግንባታ ለማካሄድ ነው፡፡ ስለዚህ ደን ለቤት ግንባታ፣ ለማገዶ፣ የቤትና የቢሮ ቁሳቁሶችን ለመሥራትና ለሌሎች መሠረተ ልማት ሲባል ይመነጠራል፡፡

ደኖች በሰደድ እሳትም ሊወድሙ ይችላሉ፡፡ በደረቅ ወቅት ሙቀት ስለሚጨምር በሰበቃ አማካኝነት ሰደድ እሳት ሊነሣና ደኖችን ሊያወድም ይችላል፡፡ ሰዎች በጊዜ ደርሰው ካልተከላከሉ የሰደድ እሳት ደንን ያወድማል፡፡ ተደጋጋሚ ድርቅም በአንድ ሥነ-ምኅዳር አካባቢ የሚገኘውን የአፈር ርጥበትና ውኃማ አካላትን ስለሚያደርቅ በደን ሽፋን ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡



*ምስል 3.18 የደን ሽፋን የተመነጠረበት ዓይነተኛ መሬት*

### የክለሳ ጥያቄዎች3.3

**ክንውን**

***ሀ. በእውቀት ላይ  የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በእፅዋትና በዱር እንስሳት ሀብት ላይ እንዴት ተጽእኖ ያሳድራል?
- በእፅዋት ሀብት መመናመንና በዱር እንስሳት መሰደድ መካከል ያለውን ትስስር አስረዱ፡፡
- የእፅዋት ሀብት መመናመንን እንዴት መቆጣጠር እንችላለን?
- የዱር እንስሳት መጠለያ ሥፍራቸውን ለቀው ወደ ሌላ ሥፍራ የሚሰደዱበት ምክንያት ምንድን ነው?
- ለደን ሀብት መመናመን ምክንያት በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ፡፡

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት /የቡድን ሥራ/***

- በሚከተሉት ርዕሶች ላይ አጭር ጽሑፍ አቅርቡ፡፡
    - የእፅዋት መመናመን
    - የዱር እንስሳት ስደት

# 3.4 የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የዱር እንስሳትና እፅዋትን እንዴት መንከባከብ እንደምትችሉ ታስረዳላችሁ፡፡
- የዱር እንስሳትንና እፅዋትን የመንከባከቢያ ዘዴዎችን ትገልጻላችሁ፡፡
- የመንከባከቢያ ዘዴዎቹን ከአካባቢያችሁ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ የዱር እንስሳትንና እፅዋትን ለመጠበቅ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ በንቃት ትሣተፋላችሁ፡፡
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት ለሚሰጡት ጥቅም አድናቆታችሁን ትገልፃላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ጥበቃ
- ድነና
- መልሶ ድነና
- ሕገወጥ አደን

## ድነና፣ መልሶ ድነና፣ የደን ቃጠሎን መቆጣጠር

- የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ ምንድን ነው?
- የተፈጥሮ እፅዋትንና የዱር እንስሳትን መንከባከብ ጠቀሜታው ምንድን ነው?

**የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ ማለት ተክሎችን እና እንስሳትን ከጥፋት በመከላከል በዘላቂነት በአግባቡ መጠቀም ማለት ነው፡፡**

በአገራችን እየተፈጠረ ያለውን የደን መመንጠር ችግር ለመፍታት የሚከተሉትን የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ ዘዴዎችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡

## ድነና

- ድነና ምንድን ነው?
- የድነና ሥራ በየት አካባቢ ሊፈፀም ይችላል?
- የድነና ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ድነና ማለት አንድን አካባቢ ወደ ደንነት መለወጥ ማለት ነው፡፡ የድነና ሥራ የሚከናወነው ቀደም ሲል ዛፍ ባልተተከለባቸው ሥፍራዎች ነው፡፡ የዚህ ተግባር ዋና ግብ የአንድን አካባቢ የተፈጥሮ ሚዛን መጠበቅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአንድ አካባቢ ሥነ-ምኅዳር ውስጥ የደን ሽፋን ለመጨመር ያስችላል፡፡ የደን ሽፋን ሲጨምር የተሰደዱ የዱር እንስሳት ተመልሰው እንዲመጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ አፅዋፍም መጠለያ ያገኛሉ፡፡ በድነና ሂደት የተለያየ ዝርያ ያላቸውና በአጭር ጊዜ የሚደርሱ፣ ዕለታዊ ፍላጎትን የሚያሟሉና ምጣኔ ሀብታዊ ጠቃሜታ ያላቸው ዛፎች ሊተከሉ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በእፅዋቱ ወደ አካባቢው የሚለቀቅ የእርጥበት መጠን

ስለሚጨምር በአካባቢው ምቹ የአየር ንብረት እንዲፈጠር ይረዳል፡፡ ከዚህም ሌላ እፅዋቱ ለአካባቢው ገፀ-ምድር ተጨማሪ ውበት ይሰጣሉ፡፡

## ◈ መልሶ ድነና

- መልሶ ድነና ማለት ምን ማለት ነው?
- መልሶ ድነና ለምን ያስፈልጋል?

- መልሶ ድነና ማለት ቀደም ሲል ተመንጥሮ የተራቆተን የደን መሬት መልሶ በደን የመሸፈን ሂደት ነው፡፡ ይህ ተግባር የሚፈጸመው ቀደም ሲል በደን በተሸፈነ መሬት ላይ የዛፍ ችግኞችን በመትከል ነው፡፡ መልሶ ድነና ቀደም ሲል ተመንጥሮ የተራቆተ ደንን መልሶ እንዲያቆጠቁጥና እንዲለማ ያደርጋል፡፡ ይህ ተግባር የዱር እንስሳት ምቹጌዎችን መልሶ ለመፍጠር ያስችላል፡፡
  በተጨማሪም የአፈር መሸርሸርን ይከላከላል፡፡
- የአካባቢውን የአየር ንብረት ሚዛናዊ ያደርጋል፡፡
- በደን ሀብት መሳሳት የተነሣ የጠፋው የአካባቢ ገጸምድር ውበት እንዲመለስ ያደርጋል፡፡

## ◈ የደን ቃጠሎን መቆጣጠር

- ሰደድ እሳት ምንድን ነው?
- የሰደድ እሳት መንሥኤ ምንድን ነው?
- ሰደድ እሳትን እንዴት መቆጣጠር ይቻላል?

ሰደድ እሳት በአንድ አካባቢ ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየተዛመተ የሚቀጣጠል እሳት ነው፡፡ ሰደድ እሳት ከሰዎች እውቀት ውጭ በእፅዋትና ደን ላይ የሚነሣ እሳት ነው፡፡ በደረቅ ሞቃት ወቅት በጫካ ውስጥ በሚፈጠር ሰበቃ ወይም ፍትጊያ እሳት ሊቀጣጠል ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደዋዛ በሚወረወር እሳቱ ያልጠፋ የሲጋራ ቁራጭ ወይም ተቀጣጣይ ነገር ሰደድ እሳት ሊቀጣጠል ይችላል፡፡ በወቅቱ መቆጣጠር ካልተቻለ ከፍተኛ የሕይወትና የተፈጥሮ ሀብት ውድመትን ያስከትላል፡፡



ምስል 3.19 በደን የተሸፈነ አካባቢ በሰደድ እሳት ሲወድም

## ◈ ሕገ ወጥ የሆነ አደንን ማስቀም

- ሕገ ወጥ አደን ምን ማለት ነው?
- ሕገ ወጥ አደንን እንዴት መከላከልና ማስቀም ይቻላል?
- ሕገ ወጥ አደንን መከላከል ስላለው ጠቀሜታ ተወያዩ፡፡

ሕገ ወጥ አደን ያለምንም ፈቃድ የዱር እንስሳትን የመግደል ተግባር ነው፡፡ ሕገ ወጥ አደን የዱር እንስሳት በሚገኙባቸው ሥፍራዎች የሚፈፀም የወንጀል ተግባር ነው፡፡ የሕገ ወጥ አደን መንሥኤዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ላይ አግባብነት ያለው ሥልጠና ካለማግኘት ሊነሣ ይችላል፡፡ ከጠባብ የግል ፍላጎትም ይመነጫል፡፡ ስለዚህ ሕገ ወጥ አደንን ለማስወገድ የአካባቢ እንክብካቤ ትምህርት ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡ በአካባቢ እንክብካቤ ትምህርት አማካኝነት የተፈጥሮ አካባቢ ሀብቶችን በአግባቡ የመጠቀምና የማስተዳደር ግንዛቤ በሕዝቡ መካከል መፍጠር ይቻላል፡፡ ሰዎች ለተፈጥሮ አካባቢያቸው የሚቆረቆሩ ወገንተኛ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ሁኔታ የተፈጥሮ ሀብትን በጥንቃቄ ለመጠቀም ያስችላል፡፡ በተጨማሪም የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ መለወጥና የሕዝብ ብዛት ዕድገትን መቆጣጠር አስፈላጊ ነው፡፡

## ◈ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፓርኮችና ተንከባካቢ ተቋማት

- ብሔራዊ ፓርኮች ምንድን ናቸው?
- የብሔራዊ ፓርኮች ማቋቋም አስፈላጊነት ምንድን ነው?
- ብሔራዊ ፓርኮችን ማቋቋም ጠቃሚ ነው ወይም አይደለም በማለት በቡድን ሆናችሁ ተከራከሩ።

የተፈጥሮ ሀብትን ዘላቂነት ባለው መልኩ ለመጠቀም የሚከተሉትን የጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች መተግበር አስፈላጊ ነው።

- ብሔራዊ ፓርኮችን፣ መናኸሪያዎችንና የተከለለ የዱር እንስሳት ጥበቃ ሥፍራዎችን ማቋቋም፣
- በብሔራዊ ሕግ አማካኝነት የዱር እንስሳት ጥበቃን ማጠናከር፣
- ሕገ ወጥ አደንን የሚከለክል ጠንካራ ሕግ ማወጅ፣
- በዱር እንስሳት የተፈጥሮ ምቹኋዎች ላይ ጥበቃ ማካሄድ፣
- በየመኖሪያ ሥፍራው ኅብረተሰቡ አካባቢውን መጠበቅ እንዲችል የአካባቢ ጥበቃ ትምህርትና የአቅም ግምባታ ሥራ ማካሄድ፣
- የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ የተዘረጋባቸውን ቦታዎች በአግባቡ መቆጣጠርና ማስተዳደር እጅግ ጠቃሚ ናቸው።

## ◈ ብሔራዊ ፓርኮች

ብሔራዊ ፓርክ በአንድ ሥነ-ምኅዳር አካባቢ የሚገኝ የተፈጥሮ እፅዋትንና የዱር እንስሳትን ለመንከባከብ የተከለለና ጥበቃ የሚደረግለት ሥፍራ ነው። በኢትዮጵያ የሚከተሉት ብሔራዊ ፓርኮች ይገኛሉ።

1. የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣
2. አብጃታ-ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ፣
3. አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ፣
4. የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣
5. የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ፣
6. ማጎ ብሔራዊ ፓርክ፣
7. ነጭ ሣር ብሔራዊ ፓርክ፣
8. ኦሞ ብሔራዊ ፓርክ
9. ያንጉዲ-ራሣ ብሔራዊ ፓርክ ናቸው።



አብጃታ-ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ



አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ



የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ

*ምስል 3.20 በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሔራዊ ፓርኮች*

## ◈ መናኸሪያዎች (sanctuaries)

- መናኸሪያ ማለት ምን ማለት ነው?
- በብሔራዊ ፓርኮችና መናኸሪያዎች መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ምንድን ነው?
- መንግሥታት መናኸሪያዎችን ማቋቋምን በአማራጭነት የሚወስዱበት ምክንያት ስምን ይመስላችኋል?



ሰንቀሌ የቆርኬ መናኸሪያ



ባቢሌ የዝሆን መናኸሪያ

*ምስል 3.21 በኢትዮጵያ የሚገኙ የዱር እንስሳትና አዕዋፍ የሚጠበቁበት ሥፍራ*

መናኸሪያ የዱር እንስሳትና አዕዋፍ የሚጠበቁበት ሥፍራ ነው፡፡ እንስሳትና አዕዋፍ ደኅንነታቸው የሚጠበቅበት የፓርክ ዓይነት ነው፡፡ መናኸሪያዎች ውስጥ የዱር እንስሳትንና አዕዋፍን ለማደን ፍቃድ ያላቸው ሰዎች ቢሆኑም እንኳን አደን ፈጽሞ አይፈቀድላቸውም፡፡ ለዚህ ዋናው ምክንያት አደን ክልክል በመሆኑ ነው፡፡

በብሔራዊ ፓርኮች የዱር እንስሳት አደን ይፈቀዳል፡፡ የሚታደኑት የዱር እንስሳት ግን እድሜያቸው የገፉና አቅመ ደካማ የሆኑት ናቸው፡፡ ቁጥራቸው አስተማማኝ የሆነው የዱር እንስሳትም ሊታደኑ ይችላሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ይህ ዓይነቱ አደን የሚከናወነው በቱሪስቶች ነው፡፡

በኢትዮጵያ በርካታ የዱር እንስሳት መናኸሪያዎች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ ባቢሌ የዝሆን መናኸሪያ፣ ቁኔ-ሙታረ የኒያላ መናኸሪያ፣ ሰንቀሌ የቆርኬ መናኸሪያና ያቤሎ መናኸሪያ ናቸው፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች 3.4

**ክንውን**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ ምንድን ነው?
- በድነናና በመልሶ ድነና መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ፡፡
- ሕገ ወጥ አደንን ማገድ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?
- ከብርቅዬና ብቸኛ የኢትዮጵያ እንስሳትና አዕዋፍ መካከል የጥቂቶቹን ስም ዘርዝሩ፡፡
- በኢትዮጵያ የተፈጥሮ አካባቢንና የዱር እንስሳትን ለመጠበቅ ከተቋቋሙ ድርጅቶች መካከል የጥቂቶቹን ስም ጥቀሱ፡፡

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

**የቡድን ሥራ**

- የዱር እንስሳትን ማደን በተመለከተ በሚኖረው ጥቅምና ጉዳት በቡድን ሆናችሁ ተከራከሩ፡፡
- ሕገ-ወጥ አደንንና የደን ጭፍጨፋን የሚቃወሙ ፖስተሮች በማዘጋጀት በአካባቢአችሁ ለጥፉ፡፡

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

***ሕገ ወጥ ሕደን***፡- ያለምንም ሕጋዊ ፈቃድ የዱር እንስሳትን ለግል ጥቅም መግደል፡፡

***መልሶ ድነና***፡- ደን ተመንጥሮ በወደመበት ሥፍራ ዛፎችን ተክሎ ዳግመኛ በደን ማልበስ፡፡

***መመናመን***፡- ቀስ በቀስ እያለቀ መሄድ፡፡

***ማኅበረሰብ***፡- ተመሳሳይ ፍላጎት ወይም ባህል ወይም ቋንቋ ወይም ሃይማኖት ወይም አስተሳሰብ ወይም ፍልስፍና የሚጋሩ ወይም በአንድ አካባቢ ወይም የሥራ ቦታ የሚኖር ሕዝብ፡፡

***ሰደድ እሳት***፡- ከሰዎች እውቀት ውጭ በእፅዋትና ደን ላይ የሚነሣና ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየተዛመተ የሚቀጣጠል እሳት ነው፡፡

***ቅምብብማ(Coniferous)***፡- ዘር ተሸካሚ ልቃቂት መሳይ አካል ያላቸው ዛፎች የወል መጠሪያ ነው፡፡ ለምሳሌ ጥድ እና ዝግባ ቅምብብማ ዛፍ ናቸው፡፡

***ቅጠለ ረገፍ ዛፍ(Decidous)***፡- በሞቃት ወይም ዝናብ አልባ በሆነ ወቅት በአካላቸው የሚገኝ እርጥበትን ጠብቆ ለማቆየት ሲሉ ቅጠሎቻቸውን የሚያራግፉ ዛፎች የወል መጠሪያ ነው፡፡ ለምሳሌ ሾላ ቅጠለ ረገፍ ዛፍ ነው፡፡

***ተሪዝም***፡- ለጥናት ወይም ለመዝናናት ወይም ለመደሰት የሚደረግ ጉዞ፡፡

***ብርቅዬ እንስሳት***፡- በአንድ ውስን መልክአ ምድር አካባቢ ብቻ ተገድቦ የሚኖር የእንስሳ ዝሪያ ማለት ነው፡፡

***ችፍርግ***፡- ቁመቱ አጭር ከመሆኑ የተነሳ ብዛት ያላቸው ቅርንጫፎቹ መሬት ላይ ተኝተው የሚታዩ ጠንካራ ሆኖ ውልግድግድ ያለ ግንድ ያለው አነስተኛ የእፅዋት አይነት ነው፡፡

***አርሶ አደር***፡- በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማራ ዜጋ(ገበሬ)፡፡

***እንክብካቤ***፡- ብልህ የሆነ የሀብት አጠቃቀም፡፡

***የእፅዋት መመናመን***፡- የእፅዋት ዓይነት ወይንም ብዛት በአካባቢው ቀንሶ መታየት፡፡

***ገጸ ምድር***፡- የምድር ገጽታ፣ መልክአ ምድር ወይም የመሬት አቀማመጥ ማለት ነው፡፡ ገጸ ምድር ተራራማ፣ ሸለቋማ ወይም ሜዳማ ሊሆን ይችላል፡፡

***ጠፍጥሻ(Steppe)*** ፡- መሬቱ ለምነት የጐደለውና ዛፍ አልባ የሆነ በሣር የተሸፈነ ለጥ ያለ ምድር ማለት ነው፡፡

***ጥበቃ***፡- የተፈጥሮ አካባቢ እንዳይበላሽ ወይንም እንዳይጐዳ ዛፎችን በመትከል፣ የእፅዋት ጭፍጨፋን በማስቆም፣ የአካባቢ ብክለትን በመቀነስ የሚደረግ እንክብካቤ፡፡

***የተፈጥሮ ሚዛን***፡- በተፈጥሮ ነገሮች መካከል የመጣጣም ሂደት፡፡

***የተፈጥሮ አካባቢ የመሸከም አቅም***፡- በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችና እንስሳትን ሲመግብ ወይንም ሲያኖር የሚችል የተፈጥሮ ሀብት ክምችት

***የተፈጥሮ እፅዋት***፡- ያለ ሰው ጣልቃ ገብነት በተፈጥሮ በቅለው የሚገኙ ሣር፣ ቁጥቋጦዎችና ልዩ ልዩ ዛፎች፡፡

***የዱር እንስሳት***፡- በደን፣ በሣርማ ምድሮችና በበረሃ የሚኖሩ እንስሳት፡፡

***ድነና***፡- ደን ባልነበረበት ሥፍራ ላይ ዛፎችን በመትከል በደን ማልበስ፡፡

***ፍልሰት***፡- ከአንድ የመኖሪያ ሥፍራ ወደ ሌላ የመኖሪያ ሥፍራ መንቀሳቀስ፡፡

# ማጠቃለያ

- በአንድ አካባቢ ያለ ሰው ልጅ ጣልቃ ገብነት በተፈጥሮ በቅለው የሚገኙ ሣር፣ ቁጥቋጦዎችና ልዩ ልዩ ዛፎች በጥቅሉ የተፈጥሮ እፅዋት በመባል ይታወቃሉ፡፡
- በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋናዎቹ የእፅዋት ዓይነቶች የከፍተኛና የዝቅተኛ ምድር እፅዋት፣ የበረሃና የከፊል-በረሃ እፅዋት በመባል ይታወቃሉ፡፡
- በኢትዮጵያ የሚገኙ የተፈጥሮ እፅዋት ዓይነቶች የከፍተኛ ተራራ እፅዋት፣ ደኖችና የከፊል በረሃና የጠፍጥሻ እፅዋት ይባላሉ፡፡
- የዱር እንስሳት ለማዳ ያልሆኑ እንስሳት ሲሆኑ በተለያዩ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡ በኢትዮጵያ በተለያየ የአየር ንብረት ክልል የተለያዩ የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት ይገኛሉ፡፡
- እነዚህ በኢትዮጵያ የሚገኙ የዱር እንስሳት የትም ተገኝ፣ ብርቅዬና ሊጠፉ የተቃረቡ አእዋፍ ይባላሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ከሚገኙ ብርቅዬና ብቸኛ እንስሳት  ዋሊያ፣ ኒያላ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ፣ ቀይ ቀበሮ ወይም የሰሜን ቀበሮ፣ የምኒልክ ድኩላና የስዋይን ቆርኬ ይጠቀሳሉ፡፡ ብርቅዬና ብቸኛ አእዋፍም ይገኛሉ፡፡
- ዝርያቸው ሊጠፋ የተቃረቡ እንስሳትም በኢትዮጵያ ይገኛሉ፡፡ ዋልያና የሰሜን ቀበሮ  በዚህ ሁኔታ ላይ የሚገኙ የዱር እንስሳት ናቸው፡፡
- በኢትዮጵያ ለዱር እንስሳት መጥፋት በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል የእርሻ መሬቶች መስፋፋትና የከተሞችና የኢንዱስትሪዎች ፈጣን እድገት፣ ሕገወጥ አደን፣ የግጦሽ መሬቶችን ማስፋፋት፣ በየጊዜው የሚከሰት ሰደድ እሳትና የድርቅ በየጊዜው መደጋገም ናቸው፡፡
- በዱር እንስሳትና በተፈጥሮ እፅዋት መካከል የተፈጥሮ ሚዛን ካልተጠበቀ የአካባቢው ሥነ ምኅዳር ይዛባል፡፡
- አርሶ አደሮች የተፈጥሮ አካባቢአቸውን በአግባቡ ሲይዙ የዱር እንስሳት መካነ ሕይወት ስለሚጠበቅ በአርሶ አደሮችና በዱር እንስሳት መካከል ጤናማ መስተጋብር ይኖራል፡፡ መስተጋብሩ በምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታና በአካባቢ ጥበቃ ይገለጻል፡፡
- የተፈጥሮ አካባቢ በአግባቡ በተጠበቀበት ቱሪዝም  ለማኅበረሰቡ፣ ለዱር እንስሳትና ለአርሶ አደሮች ጉልህ ጠቀሜታ አለው፡፡
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገትበእፅዋትና በዱር እንስሳት ላይ ተጽእኖ ያስከትላል፡፡ የእፅዋት መመናመን ስለሚከሰት የዱር እንስሳት ይሰደዳሉ፡፡ በተጨማሪም የደን ሀብት መመናመን በአካባቢው አየር ንብረት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያስከትላል፡፡
- የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት የማያቋርጥ እንክብካቤ ይፈልጋሉ፡፡ በድነና፣ በመልሶ ድነናና ሰደድ እሳትን በመቆጣጠር የተፈጥሮ እፅዋትን መንከባከብ ይቻላል፡፡ የዱር እንስሳትንም በብሔራዊ ፓርኮችና በመናኸሪያዎች እንዲጠለሉ ማድረግ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ አለው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉ ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት ምላሽ ስጡ።**

1. ደን በአብዛኛው ዛፎችና ሌሎች የእፅዋት ዓይነቶች የሚታዩበት የተክሎች ስብስብ ነው።
2. ቅጠል-ረገፍና በጉብታ ሥፍራ የሚበቅሉ እፅዋት የዝቅተኛ መሬት ደኖች ናቸው።
3. ቅጠለ ሰፋፊ ዝናባማ ደኖች የምድር ወገብ ደኖች ናቸው።
4. ቅምብብማ ደኖች ከሣር ምድር ዛፎች የሚመደቡ ለምለም ደኖች ናቸው።
5. ሣርማ የዛፍ ምድር ከ250 እስከ 2300 ሜትር ከፍታ ባላቸው አካባቢዎች ይገኛል።

**ለ. በ«ሀ»ዓምድ ሥር የተሰጡትን ስያሜዎች በ«ለ» ሥር ከተሰጡት መግለጫዎች ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| _________ 1. የከፊል በረሃና የበረሃማ አካባቢ እፅዋት | ሀ. የሣር ምድር ደኖች |
| _________ 2. የከፍተኛ ሥፍራ እፅዋት | ለ ሾላና ዋርካ |
| _________ 3. ለምለም ደን | ሐ. ጅብና ቀበሮ |
| _________ 4. የትም ተገኝ | መ. ወይራና ኮሶ |
| _________ 5. የባሌ ተራሮች ብርቅዬ እንስሳ | ሠ. ሰርዶ መሰል ሣር |
| _________ 6. ዝርያቸው ሊጠፉ የተቃረበ | ረ. ግራርና ቁልቋል |
| | ሰ. ዝግባና ጥድ |
| | ሸ. ዋልያና የሰሜን ቀበሮ |
| | ቀ. ኒያላ |
| | በ. ግራርና ሾላ |

**ሐ. ለሚከተሉ ጥያቄዎች ከተሰጡት ስያሜዎች አማራጮች መካከል ትክለኛውን መልስ በመምረጥ ፊደሉን በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ጻፉ።**

_____________ 1. ከሚከተሉት አንዱ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ውጤት ነው።

ሀ. የደን ሀብት መመናመን　　ሐ. የውኃ ፍሰት መጎልበት

ለ. የአፈር ለምነት መጠበቅ　　መ. የሣር ምድር መስፋፋት

_____________ 2. ከሚከተሉት አንዱ የተፈጥሮ እፅዋት እንክብካቤ ዘዴ ነው።

ሀ. ዛፎችን መቁረጥ　　ሐ. የሣር ምድርን ለግጦሽ ማዋል

ለ. ድነና　　መ. የዱር እንስሳትን ማደን

_____________ 3. በኢትዮጵያ ቅጠለ - ሰፋፊ ዝናባማ ደኖች ከሚገኙባቸው ሥፍራዎች ውስጥ ይጠቀሳል፦

ሀ. ሲዳማ　　ለ. ወለጋ　　ሐ. ሐዋሳ　　መ. አሰላ

_____________ 4. በኢትዮጵያ የቅጠለ-ሰፋፊ ደን ዛፎች ከሚባሉት አንዱ በመሆን ይታወቃል፡፡

ሀ. ጥድ ለ. ብሳና ሐ. ዝግባ መ. ዋርካ

_____________5. ከሚከተሉት ብርቅዬና ብቸኛ የዱር እንስሳት አንዱ በባሌ ዞን ይገኛል?

ሀ. ዋልያ ለ. ኒያላ ሐ. የስዋይን ቆርኬ መ. የምኒልክ ድኩላ

_____________6. ከሚከተሉት አንዱ በኢትዮጵያ ዝርያው ሊጠፋ የተቃረበ የዱር እንስሳ ነው፡፡

ሀ. የሰሜን ቀበሮ ለ. አውራሪስ ሐ. ድኩላ መ. ሰስ

____________7. ትላልቅና ትናንሽ የዱር እንስሳት በብዛት የሚገኙት _________ ነው፡፡

ሀ. በደን ውስጥ ለ. በሣርማ ምድሮች ሐ. በተራራ ጫፎች መ.ሀ ና ለ

___________8. ከሚከተሉት አንዱ በኢትዮጵያ ከቅጠለ-ሰፋፊ ዝናባማ ደኖች ጋር ይበቅላል?

ሀ. የጫካ ቡና ለ.ተምር ሐ. አበካዶ መ. ዘይቱና

### መ. በእያንዳንዱ ባዶ ሥፍራ ላይ ተገቢ ቃላት ወይም ሐረጋት ሙሉ፡-

1. ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸ ነገሮች በማንኛውም __________________ አብረው ይኖራሉ፡፡
2. በመሬት ላይ ከሚገኙ ሕይወት ካላቸው ነገሮች መካከል በንጽፅር ሲታይ ____________ እጅግ አነስተኛውን ክፍል ይሸፍናሉ፡፡
3. የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ስፋት _____________ ስኩዌር ኪሎ ሜትር ነው፡፡
4. በኢትዮጵያ ዝርያቸው ሊጠፋ የተቃረቡ እንስሳት ተብለው የሚታወቁት _______ እና ______ ናቸው፡፡

### ሠ. ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች አጫጭር ምላሽ ስጡ፡፡

1. የተፈጥሮ አካባቢ እንክብካቤ (ጥበቃ) ዘዴዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለአንድ የተፈጥሮ አካባቢ እንዴት አደገኛ እንደሚሆን አስረዱ፡፡
3. በአንድ በተወሰነ ሥነ-ምኅዳር ውስጥ በሚገኙ እንስሳት፣ ተክሎችና ሕይወት በሌላቸው ነገሮች መካከል ምን ዓይነት ትስስር እንዳለ አብራሩ፡፡

### ረ. የቡድን ሥራ

1. በቅርብ ወደሚገኝ አንድ አካባቢ ጉዞ በማድረግ ከሚከተሉት ተግባራት አንዱን መርጣችሁ አከናውኑ፡፡
   - በአካባቢያችሁ የሚታዩ የዛፍ ዓይነቶች በዝርዝር በመመዝገብ ለክፍል መምህራችሁ አቅርቡ፡፡ ከዚያም ዛፎች እንዴት በአካባቢያችሁ ሊያድጉ እንደሚችሉ ተወያዩበት፡፡
   - ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የሚያስከትላቸውን ምጣኔ ሀብታዊና አካባቢያዊ ተጽእኖዎችን በአካባቢያችሁ ከሚታየው ሁኔታ ጋር በማዛመድ አጭር ማስታወሻ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅረብ ተወያዩበት፡፡
   - የዱር እንስሳት ስደትን እንዴት መግታት እንደሚቻል የሚገልጽ አጭር ማስታወሻ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## ፍተሻ

*የምታውቋቸውን ክንውኖች በመለየት በያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን (✓) ምልክት አኑሩ፡፡*

1. በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዋና ዋና እፅዋትንና የዱር አራዊትን እለያለሁ፡፡ ☐
2. በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና የዱር እንስሳትን ስም እዘረዝራለሁ፡፡ ☐
3. በአፍሪካ ቀንድ በሁሉም ሀገሮች የሚገኙ እንስሳትንና በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙትን እለያለሁ፡፡ ☐
4. በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት ጥቅም አስረዳለሁ፡፡ ☐
5. ለዱር እንስሳት የተፈጥሮ መኖሪያቸው ጥበቃ ማድረግ ያለውን ጥቅም አብራራለሁ፡፡ ☐
6. የዱር እንስሳትንና እፅዋትን መንከባከብ ለምን ጠቃሚ እንደሆነ በዙሪያዬ ለሚገኙ ማህበረሰቦች አስረዳለሁ፡፡ ☐
7. ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በአካባቢያችን በሚገኙ እፅዋትና የዱር እንስሳት ላይ የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽእኖ ተንትኜ አስረዳለሁ፡፡ ☐
8. የዱር እንስሳትንና እፅዋትን እንዴት መንከባከብ እንዳለብኝ አስረዳለሁ፡፡ ☐
9. የዱር እንስሳትንና እፅዋትን የመንከባከቢያ ዘዴዎችን እገልፃለሁ፡፡ ☐
10. የመንከባከቢያ ዘዴዎቹን ከአካባቢዬ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ የዱር እንስሳትንና እፅዋትን ለመጠበቅ በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ በንቃት እሣተፋለሁ፡፡ ☐

ምዕራፍ
አራት

# ሕዝባዊ ጉዳዮች

*ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች*

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦**

- በኢትዮጵያ ለኤች አይቪ/ኤድስ የሚያጋልጡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሚያመጡትን አሉታዊ ተጽእኖ ታብራራላችሁ::
- ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር ያለውን ተጽእኖ ትተነትናላችሁ::
- የመልካም አስተዳደርና የሕፃናት መብት መከበር መገለጫዎችን ትገልፃላችሁ::
- የአደጋ መከላከያና የጥንቃቄ መርሆዎችን ትገነዘባላችሁ::

## 4.1 ሕዝብ ነክ ጉዳዮች

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ለኤች.አይ ቪ. /ኤድስ የሚያጋልጡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ማብራሪያ ትሰጣላችሁ::
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለምሳሌ ጠለፋ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ንቅሳት የሚያመጡትን አሉታዊ ተጽእኖ ተንትናችሁ ታስረዳላችሁ::
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለጎዳና ተዳዳሪነትና ያለአሳዳጊ መቅረት መንስኤ እንዴት ሊሆን እንደሚችል በመገንዘብ ታብራራላችሁ::

**ቁልፍ ቃላት**

- ጉጂ ልማዳዊ ድርጊት
- ቫይረስ
- ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት

### ◈ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

- **ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምንድን ነው?**

ኤች.አይ.ቪ. እና ኤድስ የተሰኙት ቃላት የቫይረስና የበሽታ መጠሪያ ስሞች ናቸው። ኤች.አይ.ቪ. የቫይረስ መጠሪያ ሲሆን ኤድስ ደግሞ የበሽታ መጠሪያ ነው። በአጭሩ ቫይረሱና በሽታው በአንድነት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሚል መጠሪያ ይታወቃል። ቫይረሱ ደማቸው ውስጥ የሚገኝ ሰዎች ምንም ዓይነት ውጭያዊ የበሽታ

ምልክቶች ሳይታይባቸው ከቫይረሱ ጋር ለረዥም ዓመታት መኖር ይችላሉ። ነገር ግን የተለያዩ የበሽታ ምልክቶች መታየት ከጀመሩ የኤድስ ደረጃ መድረሳቸውን ያመለክታል። ይህም ማለት ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው ሰዎች ለተለያዩ በሽታዎች በቀላሉ ተጋላጭ ይሆናሉ ማለት ነው።

ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ በአፍሪካ ቀንድ በፍጥነት በመዛመት ላይ የሚገኝ በሽታ ነው። በአካባቢው በርካታ ሰዎችን ከሚገድሉ በሽታዎች መካከልም አንዱ ነው።

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ፈጽሞ ለማዳን ወይም ከደም ውስጥ ቫይረሱን ሊያጠፋ የሚያስችል መድኃኒትም ይሁን የመከላከያ ክትባት እስካሁን አልተገኘም። ነገር ግን ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎች ለሌላ በሽታ እንዳይጋለጡና የቫይረሱ ዕድገት እንዳይጨምር የሚከላከል መድኃኒት መኖሩ ይታወቃል።

## ◈ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊት ምንድን ነው?


ስለ ልማዳዊ ድርጊቶች ጉጂ መሆንና ያለመሆን ጉዳይ ከማንሣታችን በፊት ልማዳዊ ድርጊቶች ራሳቸው ምን እንደሆኑ በግልጽ መታወቅ አለባቸው። ልማዳዊ ድርጊቶች የአንድ ኅብረተሰብ ባህል አካል ናቸው። ልማዳዊ ድርጊቶች በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ለዘመናት በስፋት የተለመዱ ከኑሮ ጋር የተያያዙ ነገሮች የማከናወኛ መንገዶች ናቸው። ልማዳዊ ድርጊት ከሕጻናት አስተዳደግ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አንድን የታመመ ሕጻን ለመፈወስ የሚደረግለት ሕክምና ሊሆን ይችላል። ልማዳዊ ድርጊት ከጋብቻ ሥርዓት አፈጻጸም ጋር የተያያዘም ሊሆን ይችላል።


- በመኖሪያ አካባቢያችሁ በስፋት የሚታወቁ ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?
- ከልማዳዊ ድርጊቶቹ ጉዳት የሚያስከትሉ የትኞቹ ናቸው? ጉዳት የማያስከትሉትስ?
- ልማዳዊ ድርጊቶች ጉዳት የሚያስከትሉና የማያስከትሉ በማለት ለምን እንደፈረጃችሁ አብራሩ።
- አንድን ልማዳዊ ድርጊት ጉጂ የሚያስብለው ምን ዓይነት ሲሆን ነው?

ልማዳዊ ድርጊቶች የአንድ ኅብረተሰብ ባህል አካል ናቸው ብለናል። ባህል ደግሞ የሰዎች የመኖር ጥረቶች ድምር ውጤት ነው። በሕይወት ለመቆየት የሚከናወኑ ተግባራትና ዘዴዎች አጠቃላይ ድምር ነው። በተመሳሳይ መልኩ ልማዳዊ ድርጊቶችም ለመኖር ሲባል የሚከናወኑ ተግባራትና ዘዴዎች ናቸው። በሌላ አነጋገር ማንኛውም ድርጊት ድርጊቱ በውስጡ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ማኅበረሰብ እይታ አንጻር፣ ለአጠቃላዩ ማኅበረሰብ ደኅንነት ተብለው የሚፈፀሙ ናቸው። ነገር ግን አንዳንድ ድርጊቶች በተደራጊ ግለሰቦችም ሆነ በአጠቃላዩ ማኅበረሰብ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ። ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ድርጊቱ የሚፈጸምባቸውን ግለሰቦች ጤና የሚያቃውሱ፣ ዘላቂ ሕመም ወይም ሞት ሊያስከትሉ ይችላሉ። የዚህ ዓይነት ውጤት ያላቸው ድርጊቶች በአጠቃላዩ ማኅበረሰብ ላይ ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ሕይወት ላይ ጫና ይፈጥራሉ።

ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በአብዛኛው በተሳሳተ እምነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ነገር ግን ማኅበረሰቡ የችግር መፍትሔና ማስተካከያ ናቸው በማለት ሊፈጽማቸው ይችላል። ይሁንና መፍትሔ ተብለው የሚፈጸሙ ድርጊቶች ራሳቸው በተሳሳተ እምነት ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው የተፈለገውን ለውጥ ሊያመጡ አይችሉም። ይልቁንም ድርጊቱ የሚፈጸምበትን ግለሰብም ሆነ በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራሉ። በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ በርካታ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳሉ ታወቃላችሁን? በአካባቢው በስፋት ከሚታወቁ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል ዋና ዋናዎቹን ከሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልከቱ።

| ተ.ቁ | ጉጂ ልማዳዊ ድርጊት | የጉጂ ልማዳዊ ድርጊቱ አፈፃፀም ማብራሪያ |
|---|---|---|
| 1 | ጠለፋ | ልጃገረዶችን ያስፈቀዳቸው ለግዴታ ጋብቻ በኃይል አፍኖ የመውሰድ ድርጊት ነው:: ጠለፋ ከልጃገረዶችም ሆነ ከወላጆቻቸው ፍላጐት ውጭ የሚፈጸም ድርጊት ነው:: ጠለፋ የሰብአዊ መብት ጥሰት ከመሆኑም በላይ በተጠላፊዋ ላይ አካላዊ ጉዳት፣ የሥነ ልቦና ስብራት፣ የትምህርት ማቋረጥ፣ ያልተፈለገ እርግዝና እንዲሁም በመራቢያ አካላት ላይ የሚታይ የጤና ችግርና ኤች አይ ቪ/ኤድስን ሊያስከትል ይችላል:: |
| 2 | እንጥል መቁረጥ ወይም መግጠጥ | በተለምዶ እንጥል ተብሎ የሚጠራው በጉሮሮ መግቢያ ላይ የሚገኘው አካል ትክክለኛ መጠሪያው ቀሰብ ክፍክድ (ክፍት-ክድን) ነው:: ከምላሳችን ወረድ ብሎ በጉሮሮ ቀዳዳ መግቢያ ላይ ይገኛል:: ይህ አካል እጅግ ጠቃሚ የሆነ ተግባር በሰውነታችን ውስጥ ይፈጽማል:: ማንኛውንም ምግብና ፈሳሽ በምንውጥበት ጊዜ ቀሰብ ክፍክድ ዝቅ ይልና የሆነ ቀዳዳ ይዘጋል:: ያ ቀዳዳ የመተንፈሻ ቱቦ በመሆኑ የምንውጠው ምግብም ሆነ ፈሳሽ በቀዳዳው እንዳይገባ ያደርጋል:: ነገር ግን ከተሳሳተ እምነት በመነሣት ይህ ጠቃሚ አካል ይቆረጣል ወይም ይግጠጣል:: |
| 3 | ያለዕድሜ ወይም ያላቻ ጋብቻ | ወንድም ሆነ ሴት የጋብቻ ዕድሜያቸው ከመድረሱ በፊት በጋብቻ ሲጣመሩ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች አሉ:: ይሁንና ብዙውን ጊዜ ወንዶች በጉልማሳነት ዕድሜ ያሉ ሲሆኑ ይችላሉ:: በየትኛውም መልኩ የበለጠ ተጐጂ የምትሆነው ሴቷ ናት:: በሴቶች ልጆች ላይ የትምህርት ማቋረጥ በወሊድ ጊዜ ሊከሰት የሚችል የጤና ችግር ሊያጋጥም ይችላል:: |
| 4 | የሴት ልጅ ግርዛት | ከሴት ልጅ ብልት ላይ በመቁረጥ ወይም በመስፋት የሚፈፀም ልማዳዊ ድርጊት ነው:: ይህ ድርጊት የሚፈጸመው የወጣት ልጃገረዶች ፀባይ ይታረማል ከሚል የተሳሳተ እምነት ነው::ይሁን እንጂ የሴት ልጅ ግርዛት በጋብቻ ሕይወትና በወሊድ ጊዜ ከፍተኛ የሕመም ስሜትና የጤና ቀውስ ሊፈጥር ይችላል:: |
| 5 | ግግ ወይም ወተቴ ጥርስ ማስወጣት | ገና በተወለደ ሕፃን ላይ ድድን በመቁረጥ ወይም በመጠቅጠቅ የሚፈፀም ጉጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው:: ድርጊቱ የሚፈፀመው ሕጻናት እንዲታመሙ ያደርጋል ከሚል ከተሳሳተ እምነት ነው:: |
| 6 | የአካል ላይ ጠባሳዎች (Tatoo) | በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ (ፊት፣ እጅ፣ ጀርባ ወይም በሌላ አካል) የሚገኝ ቆዳ በመቁረጥ ወይም በማቃጠል ሊጠፋ የማይችል ጠባሳ የመፍጠር ጉጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው:: ንቅሳትም ሌላው የተለመደ የአካል ላይ ጠበሳ ነው:: የአካል ላይ ጠባሳዎች ኤች.ኤ.ቪ/ኤድስን ጨምሮ ሌሎች በደም ንኪኪ ሊተላለፉ ለሚችሉ በሽታዎች የመጋለጥ አጋጣሚ ይፈጥራሉ:: |





*ምስል 4.1 በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ከሚታዩ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች*

## ◈ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት

- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች ምንድን ናቸው?
- ራሳችሁን እንዴት ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መጠበቅ ትችላላችሁ?

*ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚተላለፈው በአራት ዋና ዋና መንገዶች ነው፡፡*
*እነርሱም፡-*

- ጥንቃቄ የጐደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም፣
- የደም ልገሣ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ያልተመረመረ ደም በመስጠት፣
- ቅድመ ወሊድ፣ በወሊድ ጊዜና ከወሊድ በኋላ ቫይረሱ በደሟ ውስጥ ካለ እናት ወደ ልጅ፣
- በደም የተበከሉ ስለታም ነገሮችን በጋራ መጠቀም ናቸው፡፡

በማኀበራዊ ሕይወት ውስጥ በስፋት የሚፈጸሙ ነገር ግን ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የማያጋልጡ በርካታ ድርጊቶች አሉ፡፡ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ካለባቸው ሰዎች ጋር አብሮ በመኖር፣ በመጨባበጥ፣ በመቀመጥ ወይም በመጫወት ቫይረሱ አይተላለፍም፡፡ በተጨማሪም የጋራ ሽንት ቤት በመጠቀም፣ የጋራ የመመገቢያ ቁሳቁስ በመጠቀምም ሆነ በትንኝ ንክሻ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አይተላለፍም፡፡ ስለዚህ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው ወገኖቻችንን ማግለል አይገባም፡፡ ራሳችሁን ከቫይረሱ ለመጠበቅ ከደም ንክኪ መራቅ፣ ሥለታም ነገሮችን በጋራ ከመጠቀምና ከሌሎች የቫይረሱ መተላለፊያ መንገዶች ራሳችሁን መጠበቅ አለባችሁ፡፡

## ◈ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት መንስኤ

በአሁኑ ጊዜ በርካታ ጋብቻዎች የሚፈጸሙት ከጤና ምርምራ በኋላ ነው፡፡ ይህ የሚከናወነው ተጋቢዎች ከቫይረሱ ነፃ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በጠለፋ ጋብቻ ላይ ይህ ቅድመ ሁኔታ አይከናወንም፡፡ ያለዕድሜ ወይም ያላቻ ጋብቻም ተመሳሳይ ባሕርይ አለው፡፡ ምክንያቱም ያላቻ ወይም ያለ ዕድሜ ጋብቻ የሚፈጸምባቸው ማኀበረሰቦች ዘንድ የጤና ምርመራ አስተሳሰብ ሊኖር አይልችም፡፡ ስለዚህ ጠለፋም ሆነ ያለዕድሜ ጋብቻ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የማጋለጥ ዕድላቸው በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

የተቀሩት ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አንድ ተመሳሳይ ባሕርይ ይጋራሉ፡፡ ሁሉም ድርጊቶች የሰዎችን ቆዳ በመብጣት ወይም በመብሳት የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ ድርጊቶቹን ለመፈጸም ንጽሕና የጐደላቸውን ቁሳቁሶች፣ የደም ንክኪ ያላቸውን ቁሳቁስ በጋራ የመጠቀም ሁኔታ በስፋት ይታያል፡፡ አንድን ቁሳቁስ ለተለያዩ ግለሰቦች በጋራ መጠቀም ለቫይረሱ የመጋለጥ አጋጣሚን ከፍተኛ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ የሚደረግ ትግል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመዋጋት አካል ተደርጐ መወሰድ አለበት፡፡

## ◈ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት የሚያስከትለው ተጽእኖ

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን እንደ ጤና ችግር ብቻ አድርጐ መቁጠር የተሳሳተ ነው፡፡ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ በዓለማችን በከፍተኛ ደረጃ ገዳይ ከሆኑ በሽታዎች አንዱ ነው፡፡ ለቫይረሱ ተጋላጭ የሆኑት ደግሞ ወጣትና ጐልማሳ፣ የተማረና የሰለጠነ የማኀበረሰቡ ክፍል ነው፡፡ እነዚህን ሰዎች ማጣት በሀገር የምጣኔ ሀብት ዕድገት ላይ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው ሰዎች ዋጋቸው ውድ የሆኑ መድኃኒቶች ያስፈልጋቸዋል፡፡ የወላጆች ሞት ሌላ ማኀበራዊ ችግር ይፈጥራል፡፡ በርካታ ሕጻናት አንድ ወይም ሁለቱንም ወላጆች እንዲያጡ ያደርጋቸዋል፡፡ እነዚህ ወላጅ ያጡ ሕጻናት ለመኖር የማኀበረሰቡን ድጋፍ ይሻሉ፡፡ ይህ ደግሞ በማኀበረሰቡ ላይ የምጣኔ ሀብት ጫና ይፈጥራል፡፡ የማኀበረሰብ ድጋፍ ከሌለ ወላጅ ያጡ ሕጻናት ለጐዳና ሕይወት ይጋለጣሉ፡፡ በአጭሩ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የአፍሪካን ቀንድ ምጣኔ ሀብታዊና ማኀበራዊ ልማትን የሚያደናቅፍ ዋነኛ ችግር ነው፡፡

**ውስን ጥናት**

**ጎዳና ተዳዳሪነት**

በከተማ ጎዳናዎች፣ በበረንዳዎችና በየጥጋጥጉ እየተጠለሉ በልመና፣ በጉልበት ሥራና የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶችን በመፈጸም የሚኖሩ ወንዶችና ሴቶች ጎዳና ተዳዳሪ ይባላሉ። ጎዳና ተዳዳሪነት በትላልቅ የኢትዮጵያ ከተሞች ጉልቶ የሚታይ ችግር ነው። የጎዳና ተዳዳሪነት መንሥኤ የተለያየ ነው። ዋናው ግን ያለ ወላጅና ያለ ረዳት መቅረት ናቸው። ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ያለ ወላጅና ያለ ረዳት የሚያስቀር ገዳይ በሽታ በመሆኑ ለጎዳና ተዳዳሪነት መንስኤ ይሆናል።

ጎዳና ተዳዳሪዎች መሠረታዊ ፍላጐታቸውን ለማሟላት የሚያስችል ገቢ የላቸውም። ለብዙ የጎዳና ተዳዳሪዎች ልመና ዋና የገቢ ምንጭ ነው። ለአንዳንዶች ደግሞ ሌብነትና ዘረፋ የገቢ ምንጭ ተደርጐ ይወሰዳል። ጎዳና ተዳዳሪነት ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች አደገኛ ሕይወት ነው። በልመና ያገኟቸውን ሳንቲሞች በጉልበተኛ ወንዶች ይነጠቃሉ። ለአስገድዶ መደፈርም ይጋለጣሉ። በአጠቃላይ ጎዳና ተዳዳሪነት ሀገርንና ሕዝብን የሚጐዳ ማኅበራዊ ችግር ነው። በአሁኑ ጊዜ መንግሥት ከለጋሽ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር በመሆን ጎዳና ተዳዳሪነትንና ልመናን ከሀገራችን ለማጥፋት ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ሁላችንም ጎዳና ተዳዳሪነትንና ልመናን ለማጥፋት የድርሻችንን ልንወጣ ይገባል።

**የክለሳ ጥያቄዎች 4.1**

**ክንውን**

***ሀ. በዕውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?
- ልማዳዊ ድርጊቶችን ጉጂ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ የሚታዩ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለይታችሁ ዘርዝሩ
- በኤች.አይ.ቪ. እና ኤድስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
- ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ በምን ዓይነት መንገድ ይተላለፋል?
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንዴት የምጣኔ ሀብትና የማኅበራዊ ችግሮች ምንጭ ይሆናል?
- ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ የሚያስችሉ ምን ዓይነት የመፍትሔ ሐሳብ ታቀርባላችሁ?
- ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ የሚደረግ ጥረት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመዋጋት አካል ተደርጐ የሚወሰደው ለምንድን ነው?
- ጎዳና ተዳዳሪነት ምን ማለት ነው?
- የጎዳና ተዳዳሪነት መንሥኤ ምንድን ነው?
- ጎዳና ተዳዳሪዎች መሠረታዊ ፍላጐታቸውን በምን መልኩ ሊያሟሉ ይችላሉ?
- በጎዳና ሕይወት ከወንዶችና ከሴቶች የበለጠ የሚጎዳው ማን ነው? ለምን?
- ጎዳና ተዳዳሪነትን ጨርሶ ማስወገድ ይቻላል ወይም አይቻልም በማለት ተከራከሩ።

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

***ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ በአካባቢያችሁ የሚታዩ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በየወገናቸው ለይታችሁ ዘርዝሩ።***

| *ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች* | |
|---|---|
| *ከጋብቻ ሥርዓት ጋር የተያያዙ* | *ከልጅ አስተዳደግ ጋር የተያያዙ* |
| | |

## 4.2 ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና አሉታዊ ተጽእኖዎቹ

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

➢ በኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር እድገት ለአርሻ መሬትና ለማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት እንዴት ምክንያት ሲሆን እንደሚችል ትገልጻላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ማህበራዊ ግልጋሎቶች

### ◈ የማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት

- **ማህበራዊ ግልጋሎቶች ምንድን ናቸው?**

መንግሥት ለዜጎቹ በሞላ በጋራ የሚያቀርባቸው አገልግሎቶች ማህበራዊ ግልጋሎቶች ይባላሉ፡፡ ማኀበራዊ ግልጋሎቶች በዓይነታቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ የጤና አገልግሎት አንድ ማኀበራዊ ግልጋሎት ነው፡፡ የጤና አገልግሎት ለማቅረብ ሆስፒታሎችንና ጤና ጣቢያዎችን፣ ጤና ኬላዎችና ክሊኒኮችን መገንባትና የጤና አገልግሎቱን የሚሰጡ ባለሙያዎችን ማሠልጠን ያስፈልጋል፡፡ ሌላው ማኀበራዊ ግልጋሎት ትምህርት ነው፡፡ ይህን ማኀበራዊ ግልጋሎት ለማበርከት ትምህርት ቤቶችን መገንባት፣ መምህራንን ማሠልጠንና፣ የመማሪያ መጽሐፍትን ማዘጋጀትና ማሳተም ያስፈልጋል፡፡ የመኖሪያ ቤት፣ የንፁሕ ውኃና የኃይል አቅርቦቶችም ማኀበራዊ ግልጋሎቶች ናቸው፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች 4.2**

**ክንውን ሀ**

**በአሁኑ ወቅት የሚገኘውን የትምህርት ቤታችሁን ማኀበረሰብ ብዛት ከአሥር ዓመታት በፊት ወይም ትምህርት ቤታችሁ ሥራ ሲጀምር ከነበረው ብዛት ጋር አወዳድሩ፡፡**

- ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ለመሙላት አስፈላጊ የሆነ መረጃ ከት/ቤታችሁ አስተዳደር አሰባስቡ፡፡
- ባሰባሰባችሁት መረጃ ውጤት ላይ የተማሪዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መሄድ በሚያስከትለው ጫና ላይ ተወያዩበት፡፡

| የማኀበረሰቡ ዓይነት | አጠቃላይ ብዛት | | ጭማሪው በመቶኛ ሲሰላ |
|---|---|---|---|
| | ከአሥር ዓመታት በፊት | በአሁኑ የትምህርት ዘመን | |
| የተማሪዎች አጠቃላይ ቁጥር | | | |
| የመምህራን አጠቃላይ ቁጥር | | | |
| የመማሪያ ክፍሎች አጠቃላይ ቁጥር | | | |

## ◈ ፈጣን የሕዝብ ዕድገት እንዴት የማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት ይፈጥራል?

የሕዝብ ብዛት ማለት በአንድ አገር ውስጥ በአንድ የተወሰነ ወቅት የሚኖሩ ሁሉም ሰዎች ቁጥር ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በ1976 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 42,184,952 ነበር፡፡ ይህ ቁጥር በ2001 ዓ.ም. ወደ 80,713,434 አሻቅቧል፡፡ ይህም ማለት በ24 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በእጥፍ አድጓል ማለት ነው፡፡ በ24 ዓመታት ውስጥ ግን ተመሳሳይ የምጣኔ ሀብት ዕድገት በኢትዮጵያ አልነበረም፡፡ በዚህ የተነሣ የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት ተጨማሪውን ሕዝብ የመሸከም አቅም አይኖረውም፡፡ ይህ ደግሞ የማኀበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት ያስከትላል፡፡ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት እንዴት የማኀበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት ይፈጥራል?

የማኀበራዊ ግልጋሎቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልገው ወጪ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ የትምህርትና የጤና ግልጋሎቶችን እንደ ምሳሌ በመውሰድ ማየት እንችላለን፡፡ የጤና ግልጋሎት ለማቅረብ ሆስፒታሎችን መገንባት፣ ሐኪሞችን ማሠልጠንና መድኃኒት ማቅረብ ይጠይቃል፡፡ የትምህርት ግልጋሎት ማስፋፋትም እንደዚሁ ከፍተኛ ወጭ ይጠይቃል፡፡ ትምህርት ቤቶችን መገንባት፣ መምህራንን ማሠልጠንና የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍት ማቅረብ ይጠይቃል፡፡ ለዚህም ሀገሪቱ ከፍተኛ በጀት መመደብ አለባት፡፡ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መኖር ደግሞ ችግሩን ያባብሰዋል፡፡ ለምሣሌ በኢትዮጵያ ሁኔታ በ1976 ዓ.ም ለነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የቀረቡ ማኀበራዊ ግልጋሎቶች በ2001 ዓ.ም ለነበረው ሕዝብ ፈጽሞ በቂ አይሆኑም፡፡ የሕዝብ ብዛት በእጥፍ እንጻደገው ሁሉ የሚቀርቡ ማኀበራዊ ግልጋሎቶችም በእጥፍ መጨመር አለባቸው፡፡ ነገር ግን የሀገሪቱ የሕዝብ ብዛት ከሀገሪቱ የምጣኔ ሀብት ጋር ተመሣሣይ ዕድገት የለውም፡፡ ስለዚህ ሀገሪቱ በቂ ማኀበራዊ ግልጋሎቶችን ለማቅረብ ትቸገራለች፡፡ ከዚህ የተነሣም የማኀበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት ይፈጠራል፡፡

## ◈ የእርሻ መሬት እጥረት

- **ፈጣን የሕዝብ ብዛት ዕድገት ለምን የእርሻ መሬት እጥረትን ያስከትላል?**

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ቀደም ሲል ከጠቀስነው ሐሳብ መነሳት እንችላለን፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ከ40 ሚሊዮን ወደ 80 ሚሊዮን አድጓል ብለናል፡፡ ይህ ማለት ከ24 ዓመታት በፊት 40 ሚሊዮን የመሸከም አቅም ለነበራት ሀገር ሌላ 40 ሚሊዮኖች ተጨምረዋል፡፡ የሕዝብ ብዛት ዕድገት ተጨማሪ የመሠረታዊ ፍላጎት ጥያቄ ያስነሣል፡፡ ከመሠረታዊ ፍላጐቶች አንዱ የመጠለያ ሥፍራ ወይንም የማምረቻ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህም ፈጣን የሕዝብ ብዛት ዕድገት የመሬት ጥበትና ሌሎች በርካታ ችግሮችን ያስከትላል፡፡ ከችግሮቹ አንዱ የእርሻ መሬቶች መቀነስ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የምግብ እጥረት ያስከትላል፡፡ የመሬት ጥበት የአካባቢ መራቆትን ያስከትላል፡፡ መሬት ለማግኘት ሲሉ ሰዎች የደን ዛፎችን በአስከፊ ሁኔታ ይጨፈጭፋሉ፡፡ የመሬት መራቆት ደግሞ መሸርሸርና ድርቅ በማስከተል ወደ ረሃብ አደጋ ይመራል፡፡ ስለዚህ ፈጣን የሕዝብ ዕድገት በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ላይ ጫና የሚፈጥሩ ውስብስብ ችግሮች ያስከትላል፡፡የሕዝብ ዕድገት ጫና በኢትዮጵያ ሁለት ዓበይት ችግሮችን አስከትሏል፡፡ እነርሱም የማኀበራዊ ግልጋሎቶችና የእርሻ መሬት እጥረት ናቸው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 4.2

**ክንውን ለ**

***ሀ. በዕውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- የሕዝብ ብዛት ምንድን ነው?
- ማኅበራዊ ግልጋሎት ምንድን ነው?
- ከማኅበራዊ ግልጋሎቶች ዋና ዋናዎቹን ለይታችሁ ዘርዝሩ፡፡
- ፈጣን የሕዝብ ብዛት ዕድገት የማኅበራዊ ግልጋሎቶች እጥረትን እንዴት ሊያስከትል ይችላል?
- የመሬት ጥበት እንዴት ወደ ረሃብ ሊያመራ እንደሚችል ግለጹ፡፡

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- በ1976 ዓ.ም እና በ2001 ዓ.ም. የነበረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝብ በ2001 ዓ.ም. በስንት መቶኛ ዕድገት እንዳሳየ ተናገሩ፡፡

## 4.3 መልካም አስተዳደር፣ የሕፃናት መብትና ደህንነት

*የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የትምህርት ቤታችሁን ሕግጋት፣ ደንቦችንና አላማዎች ትገልፃላችሁ፡፡
- የመልካም አስተዳደር መገለጫዎችን ታብራራላችሁ፡፡
- የግልጸኝነት፣ ተጠያቂነት፣ የሀላፊነትና ከሙስና የፀዳ አሰራር ትርጉም ትገልፃላችሁ፡፡
- የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና የባህል ድርጅት ለሕፃናት መብት ጥበቃ እንደሚያደርግ ታስረዳላችሁ፡፡
- መሰረታዊ መብቶቻችሁን ታብራራላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ ሲከሰቱ የሚችሉ ከባድ አደጋዎችን ትለያላችሁ፡፡
- የጥንቃቄ ደንቦችን ፅፋችሁ ታብራራላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ሰዎች እራሳቸውን እንዴት ከአደጋ መከላከል እንደሚችሉ የምክር አገልግሎት ትሰጣላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ግልጽነት
- ተጠያቂነት
- አደጋ
- የሕግ የበላይነት
- ሙስና
- ደህንነት

## ◈ መልካም አስተዳደር

**የሚከተለውን ለመሥራት ሞክሩ።**

የሚከተሉት የትምህርት ቤታችሁ ኃላፊዎች የሚያከናውኑአቸውን ሥራዎች ተናገሩ፣

- ርዕሰ መምህር
- ምክትል ርዕሰ መምህር
- የክፍል ኃላፊ መምህር

የትምህርት ቤታችሁን የተማሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ተጠቅማችሁ ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ።

- በደብተራችሁ በአንድ ገጽ ላይ የተማሪዎችን መብቶች ዘርዝሩ።
- በሌላኛው ገጽ ላይ ደግሞ የተማሪዎችን ግዴታዎች ዘርዝሩ።
- ደንቡ ሚዛናዊ ይመስላችኋልን? በደንቡ በብዛት የተገለጸው መብትን ወይንም ግዴታን የሚያሳይ መሆናቸውን አረጋግጡ።
- የደንቦችና መመሪያዎች ዓላማ ምንድን ነው?

## ◈ በአካባቢያችሁ ምን ዓይነት ተቋማት ይገኛሉ?

በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ተቋማት መካከል ታዋቂዎቹ ትምህርት ቤት፣ የወረዳ አስተዳደርና ፖሊስ ጣቢያ ናቸው። እነዚህ ተቋማት ለአካባቢያችሁ ሰዎች የተለያዩ አገልግሎት ይሰጣሉ። ትምህርት ቤቶች የማስተማር አገልግሎት ይሰጣሉ። የወረዳ አስተዳደር መኖሪያ ቤት ወይም ለመኖሪያ ቤት መገንቢያ የሚሆን መሬት ወይም የእርሻና የግጦሽ መሬት ለኗሪዎች ያቀርባል። ፖሊስ ጣቢያ የአካባቢያችሁን ሰላምና ደኅንነት ያስከብራል። ትምህርት ቤት ከተቀሩት ተቋማት የበለጠ ለእናንተ የቀረበ በመሆኑ ሥራዎቹን እንዴት እንደሚያከናውን እንመልከት።

ትምህርት ቤት ለአካባቢያችሁ ሰዎች የመማር ዕድል ለመስጠት የተዘጋጀ ማኅበራዊ ተቋም ነው። የትምህርት ቤት ዐቢይ ተግባር የመማር ማስተማር ሥራ ማከናወን ነው። ይህ ሥራ በደንብና መመሪያ ላይ ተመሥርቶ ይከናወናል። የትምህርት ቤት ሥራዎች የሚከናወኑት በክፍል ኃላፊ መምህራንና የተለያየ የትምህርት ዓይነቶች በሚያስተምሩ መምህራን ነው። በአስተዳደራዊ አገልግሎት ውስጥ የተለያዩ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ባለሙያዎችም አሉ። እነዚህ ደግሞ ርዕሰ መምህር፣ ምክትል ርዕሰ መምህር፣ ገንዘብ ከፋይ፣ የመዝገብ ቤት ሠራተኞችና የጥበቃ ሠራተኞች ናቸው። በተጨማሪም ከትምህርት ቤቱ አገልግሎት የሚያገኙ ተማሪዎችን እናገኛለን። በት/ቤት ቆይታቸው ወቅት የተማሪዎችን ሥነ-ሥርዓት የሚያስከብሩ ደንቦችና መመሪያዎች አሉ። ደንቦችና መመሪያዎች የእያንዳንዱ ተማሪ ሰላምና ደኅንነት የሚያስከብሩ ሕጎች ናቸው። ተማሪዎች ጥቃት እንዳይደርስባቸው ይከላከላሉ። ስለዚህም የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያ በትምህርት ቤት ውስጥ ጤናማ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲከናወን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

## ◈የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች

- ትምህርት ቤታችሁ ሥራውን እንዴት እንደሚያከናውን ለማወቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።
  - በትምህርት ቤታችሁ ውሳኔዎች እንዴት ይተላለፋሉ?
  - የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ በሚተላለፉ ውሳኔዎችና በሚከናወኑ ተግባራት ላይ መረጃ የሚያገኘው እንዴት ነው?
  - መምህራን የመማር ማስተማር ተግባር የሚያከናውኑት እንዴት ነው?
  - ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች የሚሰጠው በምን መልኩ ነው?
  - የትምህርት ቤቱ ሀብትና ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ምን ይመስላል?

**ከላይ የቀረቡ ጥያቄዎች ስለ መልካም አስተዳደር ምንነት ለማስረዳት ጠቃሚ ናቸው:: ይሁንና መልካም አስተዳደር የታወቁ መሠረታዊ ባሕርያት አሉት:: እነዚህ መሠረታዊ ባሕርያት ት/ቤትን ጨምሮ የትኛውም ተቋም ውስጥ፣ መልካም አስተዳደር አለ ወይም የለም ብሎ ለመወሰን ያስችላሉ:: እነዚህን የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ ባሕርያትን ቀጥለን የምናያቸው ሲሆን ማብራሪያቸው ከትምህርት ቤት ተግባራት ጋር ተያይዞ ቀርቧል::**

## 1. ተጠያቂነት

- ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራን፣ የክፍል ኃላፊ መምህራን፣ የየትምህርት ዓይነቱ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች በሙሉ ለሚያከናውኑት ለማናቸውም ሥራ በሕግና ደንብ ተጠያቂ ናቸው:: የተፈፀመው ተግባር ወይም የተወሰደው እርምጃ ከሕግና ደንብ ውጭ ከሆነ ያስጠይቃቸዋል፤ ያስቀጣቸዋል:: ስለዚህ ተጠያቂነት የመልካም አስተዳደር አንድ ገጽታ ነው::

## 2. ግልጽነት

- የርዕሰ መምህራንም ይሁን በትምህርት ቤቱ በአመራር ቦታ የሚሠሩ ባለሙያዎች የሚወስዱአቸው እርምጃዎች፣ የሚያስተላልፉአቸው ውሳኔዎች በአጠቃላይ የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብና በበላይ ኃላፊዎቻቸው በግልጽ መታወቅ አለባቸው:: ምንም ነገር በሥውር መከናወን የለበትም:: ይህም ሌላው የመልካም አስተዳደር ገጽታ ነው::

## 3. የሕግ የበላይነት

- ማንኛውም ውሳኔና የተግባራት አፈጻጸም ከሕግ፣ ከመመሪያና ደንብ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት:: ስለዚህ የትምህርት ቤት ተግባራት በሚከናወኑበት ወቅት ሕግ፣ ደንብና መመሪያን ተከትሎ ብቻ መፈጸም አለባቸው:: ሁሉም ሰዎች ለሕግ ተገዥ መሆን አለባቸው:: የሕግ የበላይነት የመልካም አስተዳደር ሌላው ገጽታ ነው::

## 4. ሙስናን መዋጋት

- ሙስና ጉጂ ድርጊት ነው:: ሀገርንና ማኅበረሰብን ይጎዳል፣ ዜጐችንም ለጥቃት ይዳርጋል:: ሙስና ብዙ ገጽታዎች አሉት:: ለምሳሌ ፈተና አውጥቶ ያለአግባብ ለተማሪ መስጠት፣ በሥራ ያልተገኘ ውጤት ለተማሪ መጨመር፣ በፈተና ወቅት ተማሪዎች ሲኮራረጁ ችላ ማለት ወይም ሐሰተኛ የተማሪ ውጤት /transcript/ መስጠት በት/ቤት ሊያጋጥም የሚችል የሙስና ገጽታ ነው:: ጉቦ ከሙስና ገጽታዎች መካከል በስፋት የተለመደ ነው:: ለራስ ዘመድ ወይም በቅርብ ለሚታወቅ ግለሰብ ያለአግባብ መብቱ ያልሆነን አገልግሎት መስጠት ሌላው የሙስና ገጽታ ነው:: ብቃት ያላቸው ግለሰቦች እያሉ የራስን ዘመድ በአንድ የመንግሥት ሥራ ላይ ማስቀጠር ሌላው የሙስና ገጽታ ነው:: በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱ መሠረታዊ የመልካም አስተዳደር ገጽታዎች በትምህርት ቤታችሁ የአሠራር ሂደት በግልፅ ከታዩ መልካም አስተዳደር አለ ማለት ነው::

**የክለሳ ጥያቄዎች 4.3**

**ክንውን ሀ**

***ትክክለኛውን የመልካም አስተዳደር ገጽታ በተሰጠው ባዶ ሥፍራ ላይ በመሙላት ምላሽ ስጡ።***

1. *የመምህራን ስብሰባ ውሳኔዎችን የትምህርት ቤቱ ማኀበረሰብ በሙሉ በግልጽ ሊያነብ በሚችልበት የማስታወቂ ሰሌዳ ላይ መለጠፍ የትኛው የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ ገጽታ ነው?*

   ____________________
2. *የተሰጣቸውን ሳምንታዊ ክፍለ-ጊዜ ያባከኑ መምህራን ማብራሪያ እንዲያቀርቡ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ቢጠይቃቸው የትኛውን የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ ገጽታ ይወክላል?*

   ____________________
3. *ሁሉም ተማሪዎች የደንብ ልብሶቻቸውን ለብሰው ወደ ትምህርት ቤቱ ይመጣሉ። ይህ የትኛውን የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ ገጽታ ያሳያል? ____________________*
4. *የትምህርት ቤታችን ማኀበረሰብ በሙሉ ያልተገባ አገልግሎት ለማግኘት ጉቦ መስጠትም ሆነ መቀበልን አጥብቆ ያወግዛል። ይህ የትኛው የመልካም አስተዳደር መሠረታዊ ገጽታ ነው?*

   ____________________

## ◈ የሕፃናት መብት

**• ተማሪዎች ወደ ፊት ምን ለመሆን ትፈልጋላችሁ?**

ይህ ጥያቄ የኀብረተሰብን ውስጣዊ ፍላጐት ያንጸባርቃል። ማንኛውም ኀብረተሰብ የወደፊቱ ማኀበረሰብ የተሻለ ሕይወት እንዲኖረው ይመኛል። ይህን ምኞት የሚያሳኩት እናንተን የመሳሰሉ የዛሬዎቹ ሕፃናት ናቸው። ይሁንና የዛሬዎቹ ሕፃናት ለዚያ ኃላፊነት ብቁ እንድትሆኑ ማኀበረሰቡ እናንተን ሊያዘጋጃችሁ ይገባል። ሕፃናትን ለኃላፊነት ለማብቃት ከሚፈጸሙ ተግባራት መካከል ዋነኛው የሕፃናትን መብት ማስከበር ነው።

**• ሕፃናት ምን መብት እንዳላችሁ ታውቃላችሁ?**

እናንተ ሕፃናት የሀገራችሁ ዜጎች ናችሁ። እንደዜግነታችሁ ለማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ የሚከበሩለት መብቶች ለእናንተም ይከበራሉ። በተጨማሪም ሕፃን በመሆናችሁ ብቻ በተለይ የሚከበሩላችሁ መብቶችም አሉ። ቀጥሎ የተዘረዘሩት የሕፃናት መሠረታዊ መብቶች ናቸው።

- ከተወለዳችሁበት ዕለት ጀምሮ መጠሪያ ስምና ዜግነት የማግኘት መብት አላችሁ፣
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በነጻ ማግኘት፣
- በአካል፣ በአዕምሮና በማኀበራዊ ረገድ ችግር ካለባችሁ የተለየ ትምህርት፣ አያያዝና እንክብካቤ የማግኘት፣
- በአካል፣ በአዕምሮና በማኀበራዊ ረገድ ለዕድገት የሚያስፈልጓችሁን ዕድሎችና ቁሳቁሶች የማግኘት፣
- ከማንኛውም ዓይነት ጭካኔ፣ እንክብካቤ አልባነትና ምዝበራ፣ ከጉልበት ብዝበዛ ነጻ የመሆን፣ ከአካላዊ ቅጣት ነፃ የመሆን፣ ዕድሜያችሁ ለሥራ ሳይደርስ ለከባድ ሥራ አለመቀጠር የሚሉት ከሕፃናት መሠረታዊ መብቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

የሕፃናትን መብት ለማስከበር የቆሙ የተለያዩ ተቋማት አሉ። ዩኔስኮ እና ዩኒሴፍ (UNESCO and UNICEF) የሚባሉ የናንተን መብት ለማስከበር የሚሠሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ናቸው። ዩኔስኮ የተባበሩት መንግሥታ

የትምህርት የሣይንስና የባሕል ድርጅት ሲሆን ዩኒሴፍ ደግሞ የተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ የሕፃናት የአደጋ ጊዜ ፈንድ ወይም ገንዘብ የሚረዳ ድርጅት ማለት ነው፡፡ ከነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የበለጠ ግን የራሳችሁ መንግሥት መብቶቻችሁ እንዲከበርላችሁ አጥብቆ ይሠራል፡፡ በኢትዮጵያ የሕፃናት መብቶች የሕግ ከለላ አላቸው፡፡ ከላይ የዘረዘርናቸው መብቶቻችሁ በሙሉ በ1987 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 36 ተካተዋል፡፡ የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እነዚህ መብቶቻችሁ መከበራቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡

## ◈ ድንገተኛ አደጋና ደህንነት

**በክፍላችሁ ቀጥሎ በቀረቡ ጉዳዮች ላይ በቡድን ተከፋፍላችሁ ተከራከሩበት**

- **አደጋ የሚያጋጥመው ከመኖሪያ አካባቢ ወጣ ሲሉ ብቻ ነው፡፡**
- **አደጋዎች እንዳያጋጥሙ ማድረግ ይቻላል፡፡**

የሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች በሚከናወኑባቸው ሥፍራዎች ሁሉ አደጋዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ አደጋ በመኖሪያ አካባቢ፣ በትምህርት ቤቶች ግቢ ውስጥ፣ በመንገድ ወይም በጉዳና ላይ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ የአደጋ ምንጮችም በዓይነታቸው በርካታ ናቸው፡፡ በአገራችን በገጠሩም ሆነ በከተማዎች ዋና ዋና የአደጋ ምንጮች የሚከተሉ ናቸው፡፡

- የተሽከርካሪዎች አደጋ
- የእሳት አደጋ
- የጐርፍና የውኃ ሙላት አደጋ
- ከቤትም ሆነ ከውጭ እንስሳት ሊያጋጥም የሚችል አደጋና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በየዓመቱ በርካታ ሰዎች በተሽከርካሪ አደጋዎች ይሞታሉ፣ ይቆስላሉ፡፡ ከአደጋው ሰለባዎች ከፊሎቹ እግረኞች ናቸው፡፡ አደጋዎች ከሰዎች ቁጥጥር ውጭ አይደሉም፡፡ ብዙዎቹን አደጋዎች እንዳያጋጥሙ ማድረግ ይቻላል፡፡ ብዙዎች አደጋዎች ካለማወቅና ለሌሎች ደህንነት ካለማሰብ የሚፈጠሩ ናቸው፡፡

## ◈ የመኪና አደጋ

- **ራሳችሁን እንዴት ከመኪና አደጋ መጠበቅ ትችላላችሁ?**

አንድ በስፋት የሚነገር በሁሉም ሥፍራ ራስን ከአደጋ ለመጠበቅ እንደ መመሪያ ሊወሰድ የሚገባ የብልሆች አባባል አለ፡፡ እንዲህ ይላል፡፡

> **እርምጃዎቻችሁን አስተውሉ፣ ጠንቀቅ በሉ፣ አስቡ፣ ከዚያም ፈጽሙ፤**



*ምስል 4.2 የተሽከርካሪ አደጋ*

ይህን አባባል በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በአውራ ጐደናዎች ላይ በእግር በምትጓዙበት ወቅት የሚከተሉትን የትራፊክ ደንቦች ማክበር አለባችሁ፡፡

- ለእግረኛ በተዘጋጁ መንገዶች ላይ ብቻ ተራመዱ፡፡ እነዚህ በሌሉበት የመንገዱን የግራ ጠርዝ ይዞ መጓዝ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ መጓዝ ከፊት ለፊት በእኛ አቅጣጫ የሚመጡ ተሽከርካሪዎችን ለመከታተልና ከሚያስከትሉት አደጋ ራስን ለመጠበቅ ያስችላል፡፡ አውራ ጐዳናዎችን በምታቋርጡበት ወቅት በቅድሚያ የመንገዱን ነፃ መሆን ግራና ቀኙን በጥንቃቄ ማየት አለባችሁ፡፡

- በምንም ሁኔታ የቆመ ተሽከርካሪ ተገን በማድረግ መንገድ ለማቋረጥ አትሞክሩ፡፡ምክንያቱ ከሁለቱም አቅጣጫ የሚመጡ ተሽከርካሪዎችን ርቀትና ቅርበት ለማየት ስለማትችሉ ነው፡፡ ሁልጊዜ በመንገዱ ጠባብ ሥፍራ ለማቋረጥ መጠቀም መልካም ነው፡፡
- ለእግረኞች ማቋረጫ ተብሎ ነጭና ጥቁር ቀለም የተቀቡ ማቋረጫ መስመሮች ካሉ በዚያ መስመር በኩል ማቋረጥ አስፈላጊ ነው፡፡
- ለሰዎች ማቋረጫ የተዘጋጀ የትራፊክ መብራት ካለ መመሪያውን ጠብቃችሁ ማቋረጥ አለባችሁ፡፡ ቀይ የሰው ምስል ከታየ ቁም ማለት ነው፡፡ አረንጓዴ የሰው ምስል ከታየ ደግሞ አቋርጡ ማለት መሆኑን ተገንዝባችሁ ማቋረጥ አለባችሁ፡፡

## የእሳት አደጋ

የእሳት አደጋ ከፍተኛ የሕይወትና ንብረት አውዳሚ ነው፡፡ የእሳት አደጋ በመኖሪያ አካባቢም ሆነ ከዚያ ውጭ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በተደጋጋሚ ለሚከሰቱ የእሳት አደጋዎች መንስኤ የግንዛቤ ማነስና ግድየለሽነት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡ በመኖሪያ አካባቢ ለእሳት አደጋ ምንጭ የሚሆኑ በቀላሉ በእሳት ሊቀጣጠሉ የሚችሉ ነገሮች በጥንቃቄ መያዝ አለባቸው፡፡ ለምሳሌ የነዳጅ ዘይት ውጤቶች፣ ደረቅ ቅጠልና እንጨት በቀላሉ ሊቀጣጠሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህን ነገሮች ከእሳት አርቀን ማኖር ያስፈልጋል፡፡ ከመኖሪያ አካባቢ ለሚነሳ የእሳት አደጋ መነሻ የሚሆኑት በመስክ ላይ ለመዝናናት የሚቀጣጠል እሳት፣ የተቀጣጠለ ከሰል፣ ያለጥንቃቄ የሚወረወር ርችት፣ የተለኮሰ የክብሪት እንጨትና የሲጋራ ቁራጭ ናቸው፡፡ በቀላሉ የሚቀጣጠሉ ነገሮችን በጥንቃቄ በመያዝ ለእሳት አደጋ የመጋለጥ አጋጣሚን መቀነስ ይቻላል፡፡ ሕፃናት ሁልጊዜ ጥንቃቄ መወሰድ አለባቸው፡፡ በቀላሉ የሚቀጣጠሉ ነገሮችን ያለአግባብ መንካት ወይም መገልገል የለባቸውም፡፡ የእሳት አደጋ ከተነሣም የመጀመሪያ እርምጃ መሆን ያለበት ራስን ከሥፍራው በፍጥነት ማራቅ ነው፡፡ ለእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያዎች አስቸኳይ የስልክ ጥሪ ማድረግ ሌላው የመጀመሪያ እርምጃ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ የስልክ ቁጥር በቃል ማጥናት ወይም ሁልጊዜ በቅርብ ቦታ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡ የእሳት አደጋ ሲፈጠር ከአደጋው ለማምለጥ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይጠበቅባችኋል፡፡



ምስል 4.3 የእሳት አደጋ

- የእሳት አደጋ ሲፈጠር አትደንግጡ፡፡
- ከቤት ውስጥ በመስኮት ዘላችሁ አትውጡ፡፡
- በቤት ውስጥ ያለውን ዕቃ ከእሳት ለማዳን አትሞክሩ፡፡
- ልብሳችሁ በእሳት ከተያያዘ ፈጽሞ መሮጥ የለባችሁም፡፡ ምክንያቱም ሩጫ እሳቱን ሊያባብሰው ይችላል፡፡ ስለዚህ ቀስ ብላችሁ በመሬት ላይ በመተኛት ወደፊትና ወደ ኋላ ተንከባለሉ፡፡ ከዚያም የተቃጠለውን ሰውነት ለማቀዝቀዝ በውኃ መንከር፣ ያስፈልጋል፡፡ እንደዚሁም የእሳት አደጋን እርዳታ ለማግኘት ስልክ ደውሉ፡፡
- ዘውትር በቤት ውስጥ ያልተለመደ ጭስ ወይም እሳት ካያችሁ የእሳት አደጋን እርዳታ ለማግኘት ስልክ ደውሉ፡፡
- በእሳት መሐል ከገባችሁ መቆምና መንከባለል እንዳለባችሁ አትዘንጉ፡፡

- የተላጡ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች ከመንካት መቆጠብ፤ ሁኔታውንም ወዲያው ለአዋቂዎችና ለባለሙያዎች ማሳወቅ፡፡
- ሶኬት በምንሰካበትና በምንነቅልበት ወቀት ጥንቃቄ ማድረግ፡፡

## የጐርፍና የውኃ ሙላት አደጋ

የጐርፍና የውኃ ሙላት ሌሎች የአደጋ ምንጮች ናቸው፡፡ በዝናብ ወቅት አነስተኛ ወንዞች በጐርፍ ተሞልተው ደራሽ የውኃ ሙላት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ በመንገድ ዳርና ዳር በአፈር መሸርሸር የተፈጠሩ ጥልቅ ቦዮች በጐርፍ ሊጥለቀለቁ ይችላሉ፡፡ የዚህ ዓይነት ነገሮች ከሚያስከትሉት አደጋ ራስን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የጐርፍና የወንዝ ውኃ ሙላት በአብዛኛው ጊዜያዊና በአጭር ጊዜ የሚከሰሙ አደጋዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን ሲያጋጥሙ ከፍተኛ ውድመት ያስከትላሉ፡፡ የጎርፍ አደጋ ሲያጋጥማችሁ የሚከተሉትን እርምጃዎች ወስዱ፡፡ የጐርፍና የውኃ ሙላት ሲያጋጥማችሁ እስኪጎድል ድረስ መጠበቅ አለባችሁ፡፡ ጎርፍ ካለበት አካባቢ ወደ ከፍተኛ አካባቢ መሸሽ ወይም ዛፍ ላይ መውጣት እንጂ በጎርፍ አጠገብ መጫወት አይገባም፡፡

## የእንስሳት ትንኮሳ

ውሻን የመሳሰሉ የቤት እንስሳት አደገኞች ናቸው፡፡ ንክሻቸው የእብድ ውሻ በሽታ (rabies) ሊያስከትል ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነት አደጋ ሲያጋጥም በፍጥነት የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ድመትን መቆንጠጥ በጥፍሯ ሰውነታችሁን ልትቧጥጥ ትችላለች፡፡ ሌሎች የቤት እንስሳትም በአግባቡ ካልተያዙ አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ላም፣ በሬና በግ ተዋጊ ናቸው፡፡ በቅሎ፣ ፈረስና አህያ ይራገጣሉ፡፡ ስለዚህ የሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ባሉባቸው ሥፍራዎች በሙሉ አደጋ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ የጥንቃቄ መመሪያዎችን ተግባራዊ ካደረጋችሁ ከብዙዎቹ አደጋዎች ማምለጥ ትችላላችሁ፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 4.3

**ክንውን ለ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- መልካም አስተዳደር ምን ማለት ነው?
- የመልካም አሰተዳደር ዐበይት ገጽታዎች ምንድን ናቸው?
- ከሕፃናት መሠረታዊ መብቶች ቢያንስ ሦስቱን ተናገሩ፡፡
- በመኖሪያ አካባቢ የእሳት አደጋ ምንጮች ምንድን ናቸው?
- በመኖሪያ አካባቢም ሆነ ከዚያ ውጭ የሚፈጠር የእሳት አደጋን ለመቀነስ የሚያስችሉ የጥንቃቄ እርምጃዎች ምንድን ናቸው?
- ሁልጊዜ ወደ ትምህርት ቤታችሁ የተሽከርካሪ መንገድ እያቋረጡ ለሚመጡ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ምን ዓይነት የጥንቃቄ ምክር ትሰጣላችሁ?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- በመኖሪያ አካባቢ፣ በትምህርት ቤት ግቢ፣ በመኪና መንገድ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአደጋ ዓይነቶችን በጥንቃቄ ለይታችሁ ዘርዝሩ፡፡
- ለዘረዘራችሁት የአደጋ ዓይነቶች ሊወሰዱ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች በቻርት መልክ አዘጋጁና በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ በግልጽ በሚታይ ሥፍራ ለጥፉ፡፡
- በሁለት ቡድን ተከፋፍላችሁ ከአንደኛው ቡድን አንድ ተማሪ የእሳት አደጋ መፈጠሩን በመግለጽ ጥሪ አድራጊ፣ ከሁለተኛው ቡድን እንደዚሁ አንዲት ተማሪ የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ ሠራተኛን በመወከል የአደጋው አካባቢ የት እንደሆነ እየጠየቀች፡፡ የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች እስኪመጡ ድረስ ምን የጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ እንዳለባችሁ የሚገልጽ የሚና ጨዋታ /role play/ ተጫወቱ፡፡
- በገጠር የመኖሪያ አካባቢ የእሳት ቃጠሎ አደጋ ቢከሰት ሰዎች ምን ዓይነት የመከላከል እርምጃ መውሰድ እንደሚገባቸው አዋቂዎችን ጠይቃችሁ ለክፍላችሁ ዘገባ አቅርቡ፡፡

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

***ሙስና***፡- በሥልጣን ያለ አግባብ መገልገል ወይም ሥልጣንና ውሳኔ የማስተላለፍ ሃላፊነትን ያለአግባብ ለግል ጥቅም ማዋል፡፡

***ማህበራዊ ግልጋሎቶች***፡- መንግሥት ለአጠቃላይ ዜጎቹ በጋራ የሚያቀርባቸው እንደ ትምህርትና ጤና የመሳሰሉ አገልግሎቶች፡፡

***ተጠያቂነት/ሃላፊነት***፡- ማንኛውም ግለሰብ ለሚያከናውናቸው ተግባራት ለበላይ ባለሥልጣን ወይም ደንብ ተገዥ መሆን፡፡

***አደጋ***፡- ሳይታሰብ የሚከሰት ጉዳት፣ ጥፋት፡፡

***ወላጅ ያጡ ሕፃናት***፡- አንድ ወይም ሁለቱም ወላጆች በሞት የተለዩአቸው ሕፃናት፡፡

***ግልጽነት***፡- መንግሥታዊና ሕዝባዊ ተግባራትን ለሌሎች በሚታወቅ መልኩ የማከናወን ሂደት፡፡

***ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች***፡- በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የሚፈጸሙ በግለሰቦችና በአጠቃላዩ ማኅበረሰብ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ድርጊቶች፡፡

***ደህንነት***፡- ከአደጋ መጠበቅ፡፡

***የሕግ የበላይነት***፡- ማናቸውንም ተግባራት ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ተከትሎ የመፈጸም ሂደት፡፡

***ቫይረስ***፡- በዐይን የማይታዩ ጥገኛ በሽታ አምጭ ጥቃቅን ሕዋሳት፡፡

## ማጠቃለያ

- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በአፍሪካ ቀንድ በገዳይነቱ የታወቀ በሽታ ነው፡፡ በአካባቢው በርካታ ውስብስብ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮችን በማስከተል ላይ ይገኛል፡፡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለበሽታው መስፋፋት አስተዋጽዖ ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ማስወገድ አስፈላጊ ነው፡፡
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ሌላው የአካባቢው ችግር ነው፡፡ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ይህን ችግር ለመቅረፍ አልተቻላቸውም፡፡ ምክንያቱም የምጣኔ ሀብታቸው ዕድገት ከሕዝቦቻቸው የዕድገት ፍጥነት ጋር ሊጣጣም ባለመቻሉ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ለሕዝቦቻቸው በቂ የሆኑ ማኅበራዊ ግልጋሎቶችን ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ሁልጊዜ የማኅበራዊ ግልጋሎት ከፍተኛ እጥረት ይታያል፡፡ የሕዝብ ብዛት ዕድገት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ እያስከተለ ያለው ሌላው ጫና የእርሻና የግጦሽ መሬቶች እጥረት ነው፡፡
- መልካም አስተዳደር ተቋማዊ ወይም መንግሥታዊ ተግባራት የሚከናወኑበትን ሂደትና አፈጻጸም ገጽታን ይመለከታል፡፡ መልካም አስተዳደር አራት መሠረታዊ ገጽታዎች አሉት፡፡ እነርሱም ተጠያቂነት፣ ግልጽነት፣ የሕግ የበላይነትና ሁስናን መዋጋት ናቸው፡፡
- ሕፃናት የነገው ኅብረተሰብ ገንቢና ተረካቢ ትውልድ ናቸው፡፡ በየትኛውም ማኅበረሰብ ለሕፃናት ዕድገትና ትምህርት ልዩ ትኩረት የሚሰጠው በዚህ የተነሣ ነው፡፡ ይህ ትኩረት ብዙውን ጊዜ በሁለት መንገዶች ይገለጻል፡፡ አንደኛው የሕፃናትን መሠረታዊ መብቶች ለማስከበር የሚሰጥ ትኩረት ነው፡፡ ሌላው አስፈላጊ የሆኑ የኑሮ ክህሎቶች እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ ከኑሮ ክህሎቶች መካከል አንዱ ከአደጋ ራሳቸውን መጠበቅ እንዴት እንደሚችሉ ማስተማር ነው፡፡ ሕፃናት በአካባቢያቸው ሊያጋጥሟቸው ከሚችሉ አደጋዎች ራሳቸውን እንዴት መከላከል እንዳለባቸው የትምህርታቸው አንዱ ክፍል አድርጉ በማቅረብ እንዲተዋወቁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የዛሬዎቹን ሕፃናት ነገ የሚጠብቃቸውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንዲችሉ ማድረግ የሚቻለው እነዚህን ተግባራት በመፈጸም ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት ምላሽ ስጡ።**

1. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመፈወስ የሚያስችሉ ክትባትና መድኃኒቶች አሉ።
2. ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ብዙውን ጊዜ በተሳሳተ እምነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው።
3. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በመጨባበጥና አብሮ በመቀመጥ ሊተላለፍ ይችላል።
4. በዘመድ ወይም በትውውቅ የሚደረግ የሥራ ቅጥር ሙስና አይደለም።
5. ሕጻናት በሁሉም ዓይነት የሥራ መስክ የመቀጠር መብት አላቸው።

**ለ. በ «ሀ»ሥር የተዘረዘሩትን ስያሜዎች በ«ለ» ሥር ከቀረቡት መግለጫዎች ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| _______ 1. የባሕል አካል | ሀ. የሰውነት ቆዳን መብሳት |
| _______ 2. ቫይረስ | ለ. ጠለፋ |
| _______ 3. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት | ሐ. ወላጅን ማጣት |
| _______ 4. የሰብአዊ መብት ጥሰት | መ. ልማዳዊ ድርጊት |
| _______ 5. ማኅበራዊ ችግር | ሠ ሠርግ |
| | ረ. ኤች.አይ.ቪ |
| | ሰ. የአካል ጉዳት ማጋጠም |
| | ሸ. ያላቻ ጋብቻ |
| | ቀ. ኤድስ |
| | በ. የእሳት አደጋ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛ መልስ ምረጡ።**

________1. ድድ ወይም ወተቴ ጥርስ የማስነቀል ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት የሚፈጸመው በየትኛው የማኅበረሰብ አባል ላይ ነው?

ሀ. ጨቅላ ሕጻናት
ሐ. በዕድሜ የገፉ አዛውንቶች
ለ. ጉልማሣ ወንዶች
መ. ኮረዳ ልጃገረዶች

________2. ከጋብቻ አፈጻጸም ጋር የተያያዘ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት የትኛው ነው?

ሀ. ጠባሣ መፍጠር
ሐ. ጠለፋ
ለ. ድድ መብጣት
መ. እንጥል ማስቆረጥ

________3. ከሚከተሉት ተግባራት መካከል አንዱ ማኅበራዊ ግልጋሎት ከማቅረብ ጋር ግንኙነት የለውም።

ሀ. ለብሔራዊ ምርጫ መራጭ ዜጎችን መመዝገብ፣
ለ. ወባን ለመከላከል የሚያስችል ክትባት ለኗሪዎች መስጠት፣
ሐ. ንፁሕ የመጠጥ ውኃ ማቅረብ፣
መ. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአንድ ቀበሌ ውስጥ መገንባት፣

_______ 4. ከሙስና ገጽታዎች መካከል አንዱ የትኛው ነው?

ሀ. የሕግ የበላይነት | ሐ. ተጠያቂነት
ለ. ጉቦ | መ. ግልፅነት

_______ 5. መንግሥት ለዜጎቹ በሞላ በጋራ የሚያቀርባቸው ምን ዓይነት አገልግሎት ናቸው?

ሀ. ፓለቲካ | ሐ.ባህላዊ
ለ. ምጣኔ ሀብታዊ | መ. ማህበራዊ

## መ. ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች አጫጭር ምላሽ ስጡ፡፡

1. ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የማያጋልጡ ሁለት ሁኔታዎችን ግለጹ፡፡
2. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚተላለፍባቸውን ዋና ዋና መንገዶች ጻፉ፡፡
3. መሠረታዊ የሕፃናት መብቶችን በዝርዝር ጻፉአቸው፡፡
4. የመልካም አስተዳደር ዐበይት መገለጫዎች ምንድን ናቸው?
5. ማኀበራዊ ግልጋሎቶች ምንድን ናቸው?
6. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በአፍሪካ ቀንድ ለሚታይ የምጣኔ ሀብት ችግር እንዴት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል አብራሩ፡፡
7. የሕዝብ ቁጥር መጨመር እንዴት የአካባቢ መራቆት ሊያስከትል ይችላል?
8. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት እንዴት የማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት ያስከትላል?

## ሠ. የሚሠሩ ተግባራት

1. ለመንደራችሁ ሕዝብ ቀጥሎ የተዘረዘሩ ማኀበራዊ ግልጋሎቶች ለማቅረብ መከናወን የሚገባቸውን ተግባራት አንድ በአንድ ዘርዝራችሁ ጻፉ፡፡

   ሀ. የጤና አገልግሎት | ሐ. ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት
   ለ. ትምህርት | መ. ንፁሕ ውኃ

2. ቀጥሎ በቀረቡ የአደጋ ምንጮች ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመቀነስ የሚያስችሉ የጥንቃቄ መመሪያዎችን በዝርዝር ጻፉ፡፡

   ሀ. የተሽከርካሪ አደጋ | ሐ. የጐርፍና የውኃ ሙላት አደጋ
   ለ. የእሣት አደጋ | መ. የተናካሽ እንስሳት አደጋ

## ፍተሻ

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሣጥን ውስጥ አኑሩ።*

1. ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ የሚያጋልጡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ማብራሪያ እሰጣለሁ። ☐
2. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለምሳሌ ጠለፋ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ንቅሳት የሚያመጡትን አሉታዊ ተጽእኖ ተንትኜ አስረዳለሁ። ☐
3. ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ለጎዳና ተዳዳሪነትና ያለ እሳዳጊ መቅረት መንስኤ እንዴት ሊሆን እንደሚችል በመገንዘብ አብራራለሁ። ☐
4. የኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር እድገት ለእርሻ መሬትና ለማህበራዊ ግልጋሎቶች እጥረት እንዴት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል እገልፃለሁ። ☐
5. የትምህርት ቤቴን ሕግጋት፣ ደንቦችንና አላማዎች እገልፃለሁ። ☐
6. የመልካም አስተዳደር መገለጫዎችን አብራራለሁ። ☐
7. የግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ የሀላፊነትና ከሙስና የፀዳ አሰራር ትርጉምን እገልፃለሁ። ☐
8. የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ ሳይንስና የባህል ድርጅት ለሕፃናት ጥበቃ እንደሚያደርግ አስረዳለሁ። ☐
9. መሠረታዊ መብቶችን አብራራለሁ። ☐
10. በአካባቢዬ ሊከሰቱ የሚችሉ ከባድ አደጋዎችን እለያለሁ። ☐
11. የጥንቃቄ ደንቦችን ጽፌ አብራራለሁ። ☐
12. በአካባቢዬ የሚገኙ ሰዎች እራሳቸውን እንዴት ከአደጋ መከላከል እንደሚችሉ የምክር አገልግሎት እሰጣለሁ። ☐